መጽሐፍ ስምንት

አ ጸ ፋ

— 1 —

ፋንቲን ደስ የሚል ራዕይ እያየች ያለእንቅልፍ አደረች ። ከንጋቱ አቅራቢያ ግን እንቅልፍ ወሰዳት ። እሷ ስትሆኝ ሲስተር ሲምፐሊስ መድኃኒት ለመቀመም ወደ ሐኪም ቤቱ ቅጠማ ክፍል ገባች ። ትንሽ ጊዜ እዚያ እንደቆየች ሙሲ ማድሌን ቀስ ብሎ ጉበቡ ከፊቷ ቆመ ። ከመደንገጫ የተነሳ «ውይ!» አሰችና ፣ «እርስዎ ነዎት እንዴ ሙሲ ከንቲባ?» አለችው ።

«ፋንቲን እንዴት ነች?» ሲል ጠየቃት ።

«በትናንትናው ቀን በጣም አሚት ዋለች ። ነገር ግን እርስዎ ልጇን ለማምጣት ወደ ሞንፈርመይ ሕዶዋል ብላ በሳመነች ዛፊ ደህና ነች» አለች ውና ጠቢ..... አሁን እርስዎን ስታይና ልጇን ስታጣ ምን ትል ይሆን?» አለችው

«እግዚአብሔር ያውቃል!»
«ውሸት ለንግራት ግን አንችልም ሙሲ ከንቲባ ።»

ሰዓቱ ሙሉ በሙሉ ነጋ ። የጸሐይ ብርሃን በማድሌን ፊት ላይ አረፈ ። ሲስተሯ ቀና ብላ አየችውና ፤ «በየሱስ.....! ምን ደረሰቦት ሙሲ ከንቲባ? ጸጉርዎ ቃጫ መስሏል» አለችው ።

«በድንገት ሸበትኩ?» አላት ።

ሲስተር ሲምፐሊስ የፊት መስተዋት አልነበራትም ። ነገር ግን ዶክተሩ አንድ ሕመምተኛ መሞት አለመሞቱን ዓይኑ የሚያረጋግጥበት መስተዋት በጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ነበር ። እሱን አውጥታ ሰጠችውና ጸጉሩን ተመለከተው ። «ምን ያረጋል!» አለና ፤ «ለመሆኑ ፋንቲንን ላያት እችላለሁ?» ሲል ጠየቃት ።

@OLDBOOKSPDF

«ለጧን አያስመጠላትም እንዴ ሙሴ ከንቲባ»

«አስመጣላታለሁ እንጂ! ብቻ ልጅቷን ለማስመጣት ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ቀን ያስፈልገኛል »»

«አስከዚያ ድረስ ባታይዎት መምጣትዎን ልታውቅ አትችልም » ብሏ የሚሻላት ይዝው ይመለሳል « ልጂ ከመጣች በኋላ ቢያይዋት ልጂን ያመጧት እርስዎ ነዎት ብላ ማመኗ አይተርም « ይህም ውሸት ከመናገር ያድነናል» አለችው «

ሙሴ ማድሉን ለትንሽ ጊዜ አሰበና «አይሆንም ሲስተር « ላያት እፈ ልጋለሁ « ምናልባትም ኣቻኮል ይሆናል» አላት «

ምን ማለቱ እንደሆነ ባይገባትም «እንደሱ ከሆነ ይግቡ ሙሴ ከን ቲባ» አለችው «

ወደ ፋንቲን ከፍል ገብቶ ጠጋ ብሏት ቆመ « መታረሻውንም ከፈት አደረገው « አተነፋፈሷ ስጋት አሳደረበት « ፊቷ ግን ረጋ ብሎ ይታይ ነበር « የፊቷ ቀለም ወደ ንጣት አድሏቷል « ጉንጮቿ ቀልተዋል « ወር ቃማ ሽፋሽፍቷ በላብ ርሷል « ሰውነቷ ይንቀጠቀጣል « በሕይወት ለመቆ የት ብዙ ጊዜ የቀራት አትመስልም «

ማድሉን ዝም ብሎ ቁሞ አንዴ አሷን « አንዴ በግድግዳው ላይ የተሰ ቀለውን መስቀል አፈራርቆ ይመለከት ገባ « በልቡም ጸለየላት «

ፋንቲን ዓይኗን ከፍታ አየችውና «ኮዜትዬስ» አለችው ፤ ፈገግ ብላ «

— 2 —

«ኮዜትዬስ?» ስትል የጠየቀችው በሙሉ እምነት ፥ በሙሉ እርግ ጠኛነት ፥ በሙሉ እርጋታ ስለነበረ መልስ አጥቶ ዝም አላት « እሷም ቀጠ ለች ፤ «እዚያ ሔደህ እንደነበረ አውቃለሁ « በእንቅልፍ ልቤም ትታየኛ ነበር « ሰረርም ጊዜ ነው ያየሁህ « ሴሲቱን በሙሉ በዓይኔ ስከተልህ ነበ ርክ» አለችውና «ነገር ግን ኮዜትዬ የት አለች? ለምን አምጥተህ አልጋዬ ላይ አላስተመጣሃትም?» ስትል ጠየቀችው «

እንዲህ በጥያቄ ስታጣድፈው ሳለች ዶክተሩ መጥቶ ክፍሉ ውስጥ ገባ « ማድሌን ቀለል አለው «

«ረጋ በይ..... ልጅሽ መጥታለች» አላት ዶክተሩ «

@OLDBOOKSPDF

የሩንቲን ዓይን በብርሃን ተመላ ። ፊቷም እንዲሁ ።

«የት አለች? ወደኔ አምጪታ!»

ጊዜው ገና ነውና አሳት ዶክተሩ ፤ «አንቺ ዘንድ የምናቀርባት አሁን አይደለም ። ትኩሳት አለብሽ ። ልጅሽን ብታያት ርጋታሽን ታጪአለሽ ። ይህ ደሞ ለጤናሽ ጥሩ አይደለም ። መጀመሪያ ከሕመምሽ መፈወስ አለብሽ ።»

«ድኛለሁኮ ዶክተር! ተፈውሻለሁ ። ልጄን ሰማየት አፈልጋለሁ ።»

«አየሽ.....» አሳት ዶክተሩ ፤ «መንፈስሽ ተረብሿል ። በዚህ ሁኔታ እያለሽ ልጅሽን እንድታያት አልፈቅድልሽም ። እሷን ማየትሽ በቂ አይደለም ። ለሷ ብለሽ በሕይወት መቆየት አለብሽ ። ርጋታ ስታገኚ ልጅሽን እኔ ራሴ አመጣልሻለሁ ።»

«ምን ዓይነቱ ናቸው እሷዋ ዶክተር!» አለችና መልሳ ጠበቅ ይቅርታ ያድርጉልኝ ዶክተር ። እንዲህ መናገር ባልተገባኝም ነበር ። ረጋ በዪ ያሉኝ ለኔው አስበው መሆኑ ይገባኛል ። ልጄን ባያት ኖሮ ግን ጉዳት አያደርሰብኝም ነበር ። ይመኑኝ ዶክተር ... ምንም ጉዳት አያሰከትልብኝም ነበር ። ደሞም በየሳቢ ሳያት ነው የቆየሁት ። ክቱናንት ማታ ጀምሮ ዓይኔን ከእሷ የነቀልሁበት ጊዜ ያለም ። እርሰም አይሠንም አሉኝ እንጂ አሁን እኔ ዘንድ ብትመጣልኝ ኖሮ ረጋ ብዬ አንጋግራት ነበር » አለችና ፊቷን ወደ ማድሴን መልሳ ጠጠው ጥሩ ነበር አንዴ መሴ ማድሴን?» ስትል ጠየቀችው ፤ ፈሌደሀ ልጄን ማምጣትህ አንዴት ያለ ደግነት ነው! ብቻ ከዚችዬ እንዴት ነሽ! ጠብሶን ቻለችውን! መቼም እንደማታውቂኝ አውቃለሁ ። እስከዛሬ ድረስ ሬስታኖለች ። ሕጻናትኳ የማስታወስ ችሎታ የላቸውም ። ሕጻን ልጅ ዛፊ አንድ ነገር ያያል ። ነገም ሌላ ነገር ። ከዚህ በላይ አያስታውስም ። ልብሰጅ ጎጴህ ናቸው ለመሆኑ! እነቱናርዴዬ በጽዳት ይይሂት ኖሯል! በቂ ምግብስ ይሰጪት ኖሯል! ሳያት ምን ያህል እንደተቻ ኮልው ብታውቂ ኖሮ! ቆንጆ ሆኖ አገኘሃት ለመሆኑ መሴ ከንቲባ! ልጄ ውብ አይደለችም! ልጄን ለአንድ አፍታ ላያት ቢፈቀድልኝ.....! » አለች ።

ማድሴን እጇን ያዝ አደረጋትና ፤ «ከዚት ውብ ልጅ ነች» አሳት ፤ «በጣምም ደህና ነች ። እሷን የምታዪበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ። አስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን ረጋ በዪ ።»

ፋንቲን ሳሳለችና ፤ «ሞንፈርመይ ደስ የሚል አገር ነው ። አይደለም እንዴ!» አለችው ፤ «በበጋው ወራት ብዙ ሰዎች ለመዝናናት ወደዚያ ይሔዳሉ ። እነቱናርዴዬ ሀብታም ሆነዋል ለመሆኑ! በእነሱ በኩል የሚያልፉ መንገደኞች እንኳ ብዙ አይደሉም ። ማረፊያ ሆቴላቸውም ምግብ ቤት ቢጤ ነው ።»

@OLDBOOKSPDF

ሙሴ ማድሌን ንጹን ያገ እንዳደረጋት ቆየ ። ሉተኩሮ ሲመለከታትም ስጋት አደረበት ። የሚነግራት ነገር ቢኖረውም ልንገራት አልን ገራት ሰ.ል አመነታ ።

ደክተሩ ጉብኙቱን ጨርሶ ሐደ ። ሲስተር ሲምፕሲስ ግን እዚያው ቆየች ።

«እየሰማኋት ነኝ! ወይ አምላኬ! ስትሯራጥ እየሰማኋት ነኝ!» አለች ሩንቲን በድንጣት ። ይህንንም ብላ በጥንቃቄ ታጸዳምጥ ገባች ።

በእርግጥም ከሙጭ ባለው ሚዳ ላይ የአንዲት ሠራተኛ ልጅ ስትሯራጥ ፣ ስትሰት ፣ ስትዘፋጥንም ነበረች ።

«ከዚትዩ ነኝ! ድምጿን አወቀዋለሁ!» አለች ሩንቲን ።

ከተንሽ ጊዜ በኋላ ልጅቲ ርጮ ስለሐደች ድምጿ ጠፋ ። ሩንቲን ግን አሁንም ጆሮዋን አቁማ ታጸዳምጥ ነበር ። «ዶክተሩ ምን ዓይነት ክፉ ሰው ናቸው! ልጂን እንዳላያት ከለከለችኝም አይደለ!» አለች ዝት ባለ ድምጽ ።

ራሲን ትራሱ ላይ አሳረፈችውና መኖጣሯን ተጠራች ፣ ዉአንዴት ደስ ብሎን እንኖር ይሆን! ከሁት ዘራት አንድ ተንሽ የአትክልት ቦታ ይኖ ረናል ። ሙሴ ማድሌን የአትክልት ቦታ እንዲኖረን ታል ገበቶልኝ የለምነ ልጂ በአትክልቱ ቦታ እየተጅራጠች ትጫወታለች ። ግር ላይ ቢራ ቢሮዎችን ታባርራለች ። ልጎይዛቸው ለትሯራጥም ከዚያ ሉግኝቹ እመ ለከታታለሁ ። ከዚያም በኋላ የመጀመሪያ ቁርባን ትቀበላለች ። መቼ ይሆን የመጀመሪያውን ቁርባን የምትቀበልው ?»

በማቱቿ ታስላ ጀመር ። «አንድ ፣ ሁለት ፣ ምስት ፣ አራት ... ሰባት ዓመት ሆኗታል ። ከአምስት ዓመት በኋላ ነጭ ሻሽና የተጌጠ የእግር ሹራብ አድርጋና አምራ የመጀመሪያውን ቁርባን ትቀበላለች ። ይህንን ቀን ላስበው ናላዬ ይዞራልኝ

እንዲሁ ስታነበንብ ቆየችና በድንገት ጭጭ አለች ። ማድሌን እጂን ለቀቃት ።

ሩንቲን ጸጥ ከማለቷ የተነሳ መሆንፈስ ያቆመች መሰለች ። ቀደም ብሎ እንደብርሃን በርቶ የነበረው ገጽታዋ ጨለምለም አለ ። አንዳች የሚያስፈራና የሚያስሸብር ነገር ያየች መሰለች ።

«ወይ አምላኬ! ምን ነካሽ ሩንቲን» አላት ማድሌን ።

መልስ አልሰጠችውም ። ዓይኖቿ በድንገት ባየችው ነገር ላይ ተተክ ለው ቀሩ ። እጂን ዘርግታ ከበስተጀርባው ያለውን እንዲመለከት ምልክት ሰጠችው ።

ማድሌን[illegible]ዞር ብሎ ቢመለከት ግቪር ከዚያ ቆሟል ።

@OLDBOOKSPDF

— 3 —

ለምን መጣ እንዴትስ አደርጎ መጣ ገርሼር

ሙሴ ማድሌን ራሱን አጋልጦ ተከሳሽ ሻማትየ ነጻ ከተለቀቀ ፣ኋላ አታቤ ሕጉ ወድያውኑ ለፖሊስ ተቆጣጣሪው ገርሼር አስቸኳይ መልእክት ልኮ ነበር ። ልዩው መልእክተኛ ከኤም ሱር ኤም በደረሰበት ወቅት ገርሼር ከአልጋው በመነሳት ላይ ነበር ። የደረሰው መልእክት እንዲህ የሚል ነበር ፤

«የኤም ሱር ኤም ከንቲባ ፣ ሙሴ ማድሌን የቀድሞው አሰሪኛ ገና ሻልዣ መሆኑ በዝሬው ችሎት የተረጋገጠ በመሆኑ ተቆጣጣሪው ገርሼር እንዲይዘው ይፅጉ ።»

ገርሼር ይህንን መልእክት ካነበበ በኋላ ሊንድ ያስር አለቃና አራት ተራ ወታደሮችን አስከትሎ ወደ ሕክምናው ክፍል አቅጣጫ አመራ ። ከዚያ ሲደርስ የአስር አለቃውና አራቱ ወታደሮች ከውጭ ሜዳው ላይ እንዲቆዩ አድርጎ እሱ ብቻውን ወደፋንቲን ክፍል አቀና ። ከዚያ ሲደርስ በሩን ቀስ አድርጎ ገፋውና በራፉ ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ባርኤጣውን ደፍ ጠለ ። ግራ እጁን ኮቱ ውስጥ ሸጉጣታለ ። ኮቱ ከታች ጀምሮ እስከአንገት ትጉው ድረስ ተቆልፏል ። ከዘራውን ይዟል ።

ለእንድ ደቂቃ ያህል ሚንም ሳያስተውለው ባለበት ቆየ ። ከዚያ በኋላ ነው ፋንቲን ያየችውና ማነብነቧን አቁማ ጸጥ ብላ የቀረችው ። በእጇ ወደሱ አመልክታ ሚድሌን ሠር ብሎ በተመለከተው ጊዜ ገርሼር የተከነን ነፍስ ያገኘ ዲያብሎስ እንጂ ሌላም አይመስል ነበር ። ያን ያህል ሲረልገውና ሲዝታተለው የነበረውን ግን ሻልዣ በማግኘቱ ከመጠን በላይ የሆነ ደስታ ተሰማው ። ተደም ብሎ ሻማትየ የተባለው ሰው ግን ሻልዣ ነው ብሎ በማመኑ እፍረት ቢሰማውም ቅሉ ከዚያ በፊት ጠፍ ጥሮት የነበረው ሙሴ ማድሌን ግን ሻልዣ ሆኖ በመገኘቱ ከፍተኛ የሆነ የኩራት ስሜት ተሰማው ። «ከመጀመሪያው ጀምሮ በትክክለኛው መንገድ ነበርክ..... ከኔ መዳፍ የሚያመልጥ የለም!» ሲል አሰበ ። ራሱንም የጥቅሀ ፣ የብርሃን ፣ እና የእውነት ሐውልት አድርጎ ቆጠረው ። ወንጀለ ኞችን ፈልፍሎ የማውጣት ተሰጥዎ እንዳለው አመነ ። ተኩራራበትም ። የታላቅነትም ስሜት ተሰማው ።

— 4 —

ፋንቲን ገርሼር የመጣው እሷን ወስዶ ለማሰር መስሏት በፍርሃት ተብረከረከች ። «ሙሴ ማድሌን..... ከዚህ ሰውዬ አድነኝ» ስትል ጮኸች ።

@OLDBOOKSPDF

ማድሌን ተነስቶ ቆሞ ፈአይዘሽ ፋንቲን..... አንቺን ፍለጋ አይደለም የመጣው» አላትና ዓይኑን ወደ ግቪር መልሶ ፤ ሴትን ፍለጋ እንደመጣህ አውቃለሁ» አለው ።

ፈአኮ ፈጠን በልህ አለው ግቪር ዓይኑን ማድሌን ላይ ተክሎ ።

ፋንቲን ዙርያውን ታንኝ ። ሠግቪር እንዲህ የሚናገረው ለማን ነው» ስትል አሰበች ። አውንም ቢሆን እርሷን ወስዶ ለማሠር የመጣ መስሏታል ።

ከዚያ በኋላ ግቪር ሐድ ብሎ የከንቲባውን ማጅራት ሲይዘው ፈሙሴ ከንቲባ!» ስትል ጮኸች ፋንቲን ። ድርጊቱ የዓለም ፍጻሜ መስሎ ታያት ።

ግቪር ድዱን ግልፍጥ ሳቀና ፤ «ከአውን ወዲያ ሙሴ ከንቲባ የሚባል ሰው የለም!» አላት ።

ሠግቪር ....» አለ ማድሌን በዘኩሉ ፤ ማጅራቱን ሰማስሰትት አንዳችም ሙከራ ሳያደርግ ።

«ሙሴ ተቆጣጣሪ እንጂ ግቪር ብለህ አትጥራኝ» ሲል አቋረጠው ።
«ዘቆይታ ሳኑጋግርህ ብትፈትድለኝ.....»

«የምን ቆይታ ነው ደሞ! የምትናገረው ካለህ በግሐድ ፤ ድምጽህን ክፍ አድርገህ ተናገር ።»

«ፈእኑ ብቻ የምትሰማው ጉዳይ ነው ።»
«ምስጢር ከሆነ አትንገረኝ..... አልፈልግም ።»
ፈሦስት ቀን ብትሰጠኝ.....» አለው ዝቅ ባለ ድምጽ ፤ «የዚህችን መከ ረኛ ሴት ልጅ ሒጂ እንዳመጣሳት ሦስት ቀን ብቻ ብትሰጠኝ..... የጠየቅ ኸኝን ዋጋ አከፍልሃለሁ ።»

«ሦስት ቀን ሰጥቸህ ኩበልለህ ልትጠፋ! እንዴት ያለ ቀልድ ነው እባካችሁ! ደሞም የዚህችን ሴትዮ ልጅ ለማምጣቱ ነው ያልከው? ግሩም.....! ግሩም.....!»

ፋንቲን ተንቀጠቀጠች ። «ልጄን ለማምጣት! ልጄ አልመጣችማ!» ስትል ጮኸች ፤ «ሲስተር..... አውነቱን ንገሪኝ ። ልጄ የት ነች! ልጄን አሳይኝ! ሙሴ ከንቲባ.... ሙሴ ከንቲባ!»

ግቪር ተናድዶ መለሱን በእግሩ ድም አደረገውና ፤ «አፍሽን ዝጊ አንቺ ሸርሙጣ!»አላት ፤ «ይገርማልኮ! ወንጀለኛ የሆነ ሰው ከንቲባ የሚሆ ንበት ዘመን..... ሸርሙጣን እንደልዕልት የሚንከባከቡበት ዘመን.....! ይህ ሁኔታ ግን ከአውን ወዲያ አይቀጥልም ። እንለውጠዋለን!» አለ ።

የማድሌንን ክራቫት ፤ ሸሚዝና ማጅራቱን እንደባና አፈፍ አድርጎ ያዘና ዓይኑን ወደ ፋንቲን መልሶ ፤ «ሙሴ ከንቲባ ወይም ሙሴ ማድሌን

@OLDBOOKSPDF

ማለት ቀርቷል ብዬሻለሁ ። ይህ ሰው ግን ቫልጋ ነው..... ቀጣፊ ሴባ..... ወሮበላ..... የቀድሞ አለረሻ..... በመጻፌ ሥር ነው ያለው ። ገባሽ» አለት ።

ራንዛን ከአልጋዋ ቀኖ ብላ ማድሌንን ፣ ጥቩርን ፣ አና ነርስዋን አፈራርቃ ተመለከተች ። ለመናገር እንደፈለገ ሰው አፏን ከፈተች ። ከጉሮሮዋ የሚንገፈገፍ ድምጽ ሬሰቀ ። ጥርሶቿ ተላጭተት ። ጣዕር ይዟት እጆቿን ዘረጋችና ውሃ እንደሚመስደው ሰው አንዳች ነገር ለመያዝ በአካባቢዋ ያለውን ሁሉ በእጅ ትደባብስ ገባች ። ከዚያም ቢኋላ ራሷ ተመልሶ ትራሱ ላይ ሲወድቅ ከራስጌዋ ያለው የአልጋው እንጨት መታት ። ዓይኖቿ ጨለሙ ።

የራንዛን ሕይወት በዚያ ቅጽበት አሰፈች ።

ማድሌን በዚህ ጊዜ ጨምድዶ የያዘውን የጥቩርን እጅ መንጭቆ አስለቀቀና ፣ ወለዚህች ሲትየ ሕይወት ማለፍ ተጠያቂው አንተ ነህ__ ገድ ለሃታለ» አለው ።

«ቢታህ!» አለው ጥቩር ፣ ወኔ እዚህ የመጣሁት ለንትርክ አይደለም ። ዘበኞች ከውጭ ሆነው ይጠብቁሃል ። እና ዝግ ብለህ ተራመድ ። አለዚያ የሚደርስብህን እወቅ!»

ከክፍሉ ጥግ ውሞንትጡ የወላ አንድ የብረት አልጋ ነበር ። ማድሌን ወደዚያ ራመድ ብሎ ሐዲ የብረት ዱላ አነሳና በቱጣ ዓይን ተመለከተው ። ጥቩር መደነላው ሸሸች አሰ ። ማድሌን የብረት ዱላውን እንደያዘ ወደ ሩን ቲን ተጠጠ ፣ ዓይኑን ግን ዘግቶር ባይ ብነለ ፣ «አውን ባታናድደኝ ይሻልሃል!» ሲል ዛተበት ። ጥቩር በዚህ ጊዜ በፍርሃት ተንቀጠቀጠ ። ወጥቶ ዘበኞቹን ለመጥራት ፈለገ ። ነገር ግን ማድሌን በዚህ አጋጣሚ ተጠቅሞ ሸሽቶ እንዳያመልጠው ፈራ ። ስለዚህ ከዘራውን እንደያዘ ዝም ብሎ ቆመ ፣ ዓይኑን ከማድሌን ሳይነቅል ።

ማድሌን ራንዛንን ያስተውል ገባ ፣ በሃሳብ ተውጦ ። ፊቱ ሀዘን ለብ ያለ ። በዚው ሁኔታ ለትንሽ ጊዜ ቆየና ጉንበስ ብሎ ዝቅ ባለ ድምጽ እን ዳች ነገር ተናገረ ። ለራንዛን አስከሬን ምን እንደተናገረ ያወቀ ሰው የለም ።

የራንቲንን ራስ በሁለት እጆቹ ይዞ አመቻችቶ አስተኛው ። ጸጉሯን አስተካከለው ። ዓይኖቿንም ዘጋቸው ። በመጨረሻም እጇን ስሟት ቀና አለና ወደጥቩር እያየ ፣ «በል አውጣ ዝግጁ ነኝ» አለው ።

— 5 —

ጥቩር ማድሌንን ከከተማው ወህኒ ቤት አስገብቶ አሠረው ። ወዲያ ውኑ ሰው ሁሉ ማድሌንን ከዳው ። ሰኤም ሱር ኤም ነዋሪ ሕዝብ የፈጸ መው መልካም ሥራ ሁሉ ተረሳ ። በከተማውም ውስጥ የወሬ ዶፍ ይወ ርድ ጀመር ፤

@OLDBOOKSPDF

«የሁድሞ አስረኛ አንዱነበረ አልሰማህም እንዴ?»
«ማ?»
«ከንቲባው ነዋ!»
«ም—ን? ሙሴ ማድሴን?»
«ታዲያስ!»
«አይደረግም!»

«እረ እንዲያውም ስሙ ማድሴን አልነበረም አሉ! ማን ነበርክ ቢዣ ነው ወይስ ቦጎ? ወይንስ ቡጉ...?»
«የክርስቶስ ያለህ»

«እሳ ተይዘ ታስሯል። በከተማው ወሀኒ ቤት የታሠረው ስጊዜው ነው አሉ። ከዚያ በኋላ ወደ ሌላ ወህኒ ቤት ሲያዛውሩት አያቴርም ይባላል።»

«ወዴሌላ ወህኒ ቤት...?»
«አምን።»

«እኔስ ድሮውንም ቢሆን እጠራጠረው ነበር። እንዲያ ደግነት ማብ ዛት ....! ግንዘቦን እንዲያ መበተን ....! ከበሶቦጀርባው አንዳች ምክን ያት ቢኖረው ነው ብዬ ድሮውኖም ቢሆን እጠረጥረው ነበር።»

ማድሴን በዚህ ሁኔታ ይታማ ጀመር። ስሙን በጥሩ መንፈስ የሚያነ ሱት ቢኖሩ ከሦስት ወይም ከአራት ሰምት አይበልጡም ነበር። ከእነ ዚህ አንዷ አሮጊት ባሪያ ነበረች።

የተያዘ ዕለት ራበሪካው ተበሳጭቶ ዋለ። ሲለተር ፔርፔቱና ሲስተር ሲምፕሊስ ብቻ በራበሪካው የሕከምና ከፍል በሩንቲን አስከሬን አጠ ገብ ቁጭ ብለው ዋሉ።

ምሽት ላይ የማድሴን ዣሪድ ስለሱ ስታስብ ነበረች። በተለምዶ ወደ መኖሪያ ቤቱ ይመለስ በነበረበት ሰዓት ከተቀመጠችበት ተነስታ፣ የክፍሉን ቁልፍ ከጠረጴዛው መሳቢያ አውጥታ፣ የሻማ መያዣ መቅረዙ ንም ይዛ ሌላ ጊዜ ከምታቆይለት ቦታ ወስዳ አኖረችለት። ይህን ማድ ረጓ ምናልባት ቢመጣ ብላ በማሰብ ሳይሆን አይቀርም። ከዚያ በኋላ ወደ ወንበሯ ተመልሳ ቁጭ ብላ ታስብ ጀመር።

ሁለት ሰዓት ያህል ካለፈ በኋላ ከቀን ሕልሟ ነቅታ፣ «ወይ ጉድ! ምንድነው የሠራሁት? ቁልፉን በተለምዶው ቦታ አስቀመጥኩላቸ ውኩ!» አለች።

ልክ በዚህ ሰዓት አንድ ሰውዬ እጁን በክፍሏ መስኮት ለድዶ ቁልፉንና የሻማውን መቅረዝ ወስዶ ሻማውን አበራው፣

ዣሪዲ ዓይኗን አትንታ ተመለከተችና ከመገረም የተነሳ አፏን ከፍታ ቀረች። እንደመረመህም ቃጣት። ነገር ግን ኦልሙሽም። ማን እንደ

@OLDBOOKSPDF

ሆነ ተገነዘበች ። ሙሴ ማድሴን ራሱ ነበር ። ነገር ግን ከወዴት መጣ ? ከሰማይ ወረደ ወይንስ ምድር ተፋችው ?

መናገር ተስኗት ለትንሽ ጊዜ ዝም ብላ ቆየችና « ሙሴ ማድሴን እኔስ እንዲያው ወዴ አስር ቤት .....» ብላ ትንፋሿን ቁርጥ አደረገችው ።

«አምን አስር ቤት ወስደሙኝ ነበር ። የአስር ቤቱን መስኩት ሰብሬ... አምልጩ መምጣቱ ነው ። አውን ወዴ ከፍሌ እወጣለሁ ። አንቺ ግን ሐዲሽ ሲስተር ሲምፕሊስን ጥሪልኝ » አላት ።

ማድሴን በነገረዱ ላይ ሙሉ እምነት ስለነበረው ስለሱ እንዲታወራ አላስጠነቀቃትም ። እሷም የታዘዘችውን ለመፈጸም ወጥታ ሐዲሽ ።

የአጥሩን ዘር እንዴት ከፍቶ እንደገባ ግንም አላወቀም ። የአጥሩን ዋና በር ሳይሆን ትንሹን በር የሚከፍት ቁልፍ ግን ምን ጊዜም ከኪሱ አይጠፋም ነበር ። ነገር ግን አስር ቤት ሲገባ ሳይፈተሽና ቁልፉ ሳይወሰ ደበት እንዴት ቀረ ? ለዚህ ጥያቄ መልስ ያጣ ሰው አልተገኘም ።

ደረጃውን ወጥቶ ወዴ ክፍሉ አመራ ። ቃስ ብሎ ከፈተውና ገባ ። ከዚያም በኋላ የክፍሉን መስኮት ዘጋው ።

ሙርያውን ታየ ። ጠረጴዛው ፣ ወንበሩ ፣ አልጋው..... ሁሉም በየቦታው ናቸው ። ወዴ አራ ከሔደበት ሰዓት ጀምሮ እስከ አውን ድረስ አንዳችም ነገር ዝንጥ ሳይል ቆየው ። ይህን አንኚ ባታጠለው ዘንጣጣፍና ጫፍ የንበሩ የብረት ቃሰቡቶችና ከትንሹ ዣርቬ የተማው ሳንቲም በጠረጴዛው ላይ ነበሩ ። እርግጠ ነኝ ከአመዱ አንስታ እዚያ ላይ ያኖረ ታቸው ።

ቱሪጭ ወረተት አንስቶ ፣ ፈለሰራ ፍርድ ቤት የተገገርከት ስለነዚህ ቀለበቶችና ስለዚህ ሳንቲም ነው የሚል ጽሑፍ አሰፈረበትና ወረቀቱን ፣ ቀለበቶቹንና ሳንቲሙን ዓይን ከሚስብ ቦታ ላይ አስቀመጣቸው ። ከክፍሉ ውስጥ የገባ ማናቸውም ሰው ሊስታቸው አይችልም ነበር ። ሁለቱን መቅ ረዙት በተተረተረ ሽሚዝ ጨርቅ ጠቀለላቸው ። ከዚያም በኋላ ከጋሬ ያል ተሻለ ዳቦ ይገምጥ ጀመር ። ዳቦው ከአስር ቤት ይሀት የመጣ ሳይሆን አይተርም ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ በሩ ተንኳኳና ሲስተር ሲምፕሊስ ገባች ። ገር ጥያለች ። ዓይኖቿ ቀልተዋል ። በእጇ ያለው ሻማ ይንቀጠቀጣል ። ያን ሞን ስታለትስ ነው የዋለችው ።

ሙሴ ማድሴን አንድ ማስታወሻ ጻጽፎ ፤ ሬይሀንን ወረቀት ለሰበ ነው ቁስ ስጠ.ልኝ ሲስተር ሲምፕሊስ» አላት ። ወረቀቱን አሳጠፈ

@OLDBOOKSPDF

ውም ። ሲስተር ሲምፕሊስ መልከት አደረገችው ። ፈልቃነቢው ትችያለሽ አላት ። እሷም አነበበችው ።

ፊሳንብረቱ አደራ ። በተከሰከሰሁበት ጉዳይ ለፍርድ ቤት መከራል ያለበትን ሂሳብና ትናንትና ላረፈችው ምስኪን ሴትዮ የቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ከንብረቱ ወጪ አድርገው ይክፈሉልኝ ። የተቀረው ሀብት ንብረቱ ለድሆች መርጌ ያውሉልኝ» የሚል ነበር ።

ሲስተር ሲምፕሊስ መናገር አቅቷት ከቆየች በኋላ ፤ ፈያልቃደለችውን ሴትዮ አስከሬን ለመጨረሻ ጊዜ ኢየዩትም ሙሌ ከንቲባ» ስትል ጠየቀችው ።

ፊኢልኾልም ። እየፈለጉኝ..... እየተከታተሉኝ ናቸው ። አሷ ዘንድ ብሔድ ይይዙኛል ። እሷም ትረበሻለሽ» አላት ፤ ሩጉቲን በሕይወት እን ዳለች ሁሉ ።

ይህንን ሲል ሳለ ከውጭ ድምጽ ተሰማ ፤ ደረጃውን የሚወጡ ሰዎች ንግግርና የጫማቸው ኮቴ ።

ወፊ ማንም ሰው አሊመጣም ። ከፈለጉ በኢግዚኩቢሔር ስም ሊማ ልልዎት ። ቀኑን ሙሉ ከዚህ ንቅንት አላልኩም» ስትል ነበረች የማድሌን ገረድ ።

«ከፍሉ ውስጥ መብራት አለም አይደሉ እንዴ?» አላት የወንድ ድምጽ ።

ማድሌን ድምጹ የጎቬር መሆኑን ሲረዳ ወዲያውኑ በእጁ የነበረውን ሻማ አጠፋውና ከአንድ ጥግ ሔዶ ተደበቀ ። ሲስተር ሲምፕሊስ ግን በጠ ረጴዛው አጠገብ ተንበርክካ ትጽልይ ገባች ።

በሩ ተከፈተ ። ጎቬር ገባ ። አሮጊቷ ገረድና ጎቬርን ተከትለው የመጡት ሰዎች ግን ከውጭ ቆዩ ።

ሲስተር ሲምፕሊስ አንገቷን ቀና ሳታደርግ ጸሎቷን ቀጠለች ። የእርሷ ሻማ እጅግም ብርሃን የለውም ።

ጎቬር ሲስተሯን ሲያይ ቆም አለ ። ለመንፈሳዊ ሰዎች አድናቆት አለው ። ያከብራቸዋል ። የእውነት ምንጭ ናቸው ብሎም ያምናል ። ሲስተርዋ ተን በርክካ ስትጸልይ በማየቱ ደንግጥ ብሎ ለመመለስም ቃጣው ። ነገር ግን ወደዚያ የመጣው በግዴታ ምክንያት ስለሆነ ምንም ሳይፈጽም በመጣበት አግሩ ለመመለስ አልቻለም ። ሲስተር ሲምፕሊስ የማትዋሽ ንጹህ ሴት መሆኗን ስለሚያውቅ ፤ «እዚህ ክፍል ውስጥ ካላንቺ ሌላ ሰው የለም ሲስተር?» ሲል ጠየቃት ።

@OLDBOOKSPDF

ሲስተር ሲምፕሊስ ቀና ብላ አየችውና ፈግጌም የለም» አለችው ።
«አየሽ ሲስተር..... እኔ ግዳጅ ላይ ነው ያለሁት ። እና ዛሬ ከአስር ቤት አምልጦ የወጣውን ፣ ጥን ቫልጣን አሳየሽውም!»

«አላየሁትም» አለችው ።
ሲስተር ሲምፕሊስ ዋሸችው ፤ ያውም አንድ ጊዜ ሳይሆን ሁለት ጊዜ ። ሕሊናዋን ለሙሴ ማድሌን መስዋዕት ማድረጓ ነበር ።

«እግዚያውስ ይቅርታ.....» አላትና ትታት ወጣ ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ሙሴ ማድሌን ጭጋግ ለብሶ ፣ አንዳች የተጠቀለለ ነገር ይዞ ፣ ከኤም ሱር ኤም ወጥቶ ፣ ወደ ፓሪስ አቅጣጫ ይጓዝ ጀመር ። በመንገድ ያዩት ሁለት ወይም ሦስት ጋሪ ነጂዎች ማንነቱን አረጋግጠዋል ።

ሲስተር ሲምፕሊስ ማድሌን የሰጣትን ማስታወሻ ለሰበካው ቄስ ካደረሰችለት በኋላ ቄሱ በተቀበለው አደራ መሠረት ለፋንቲን የቀብር ሥነ ሥርዓት አዘጋጀላት ። ይሁን እንጂ ገንዘብ መቆጠብ አለብኝ ብሎ ስላመነ በተብሯ ሥነ ሥርዓት ብዙ ወጪ አላደረገም ። ለቁርጩ ድሆች ከሚያደገው ወጪ በላይ አላወጣባትም ። ማንኛውም ድሃ ከሚቀበርበት ቦታ ተቀበረች ። መቃብሯም ከሌሎች መቃብሮች ተለይቶ የሚታወቅ አልነበረም ።

@OLDBOOKSPDF

ክፍል ሁለት

ነገሮች

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አንድ

ኦሪዮን የተባለው መርከብ

— 1 —

ሚን ቫልጣ ከወሀኒ ቤት አምልጦ አልቀረም ። እንደገና ተያዘ ።

ሐምሌ 25 ቀን 1823 ዓ. ም. ታትሞ የወጣው «ድራፓ ብሳ» ወይም ነጭ ባንዲራ የተሰኘው መጽሔት ስለዚህ ጉዳይ ቀጥሎ ያለውን አሰፈረ ፤

«በፖ ደ ካሉ ከፍለ ሀገር አንድ ያልተለመደ ነገር ሆነ ። ከጥቂት ዓመታት በፊት በዚሁ ከፍለ ሀገር መሲ ሚድሌን የተባለ እንግዳ ደራሽ በፈለሰፈው አዲስ ዘዴ ምክንያት የጥቁር መስታወት ጌጥ ሥራ ከነበረበት አዘቅት ወጥቶ ለማኅበራዊና ለመሰፋፋት ቻለ ። ይህ ሰው ራሱን አዘልጽ ከፍለ ሀገሩንም ቁምር ማበልጸግ የሚነድ አይደለም ። አገልግሎቱም ታውቆለት ከንቲባ ሆኖ ተሾመ ። በኋላ ግን ይህ ሰውዬ ሚን ቫልጣ የተባለ የተደጋሞ አስረኛ መሆኑና ሊታመር የቻለውም በ1796 ዓ. ም. በፈጸመው የስርቆት ወንጀል ምክንያት መሆኑ በፖሊሶች ከተቸለ ሊታወቅ ተችሏል ። ሚን ቫልጣ አሁን በድጋሚ ታሥሯል ። በድጋሚ ተይዞ ከመታሠሩ በፊት ግን ቀደም ብሎ በሕጋዊ መንገድ መሮቱ ያከማቸውን ንብረት ከታወቀው በጎ ከላፊት አውጥቶ የወሰደ ይመስላል ። ከሚነበ ያወጣው ንብረት ከሚሸሽ ሚሊዮን ፍራንክ በላይ እንደሆነ ይገመታል ። ሚን ቫልጣ ወደ ተሎ አስር በት ከተመለሰ ወዲህ ይህንን ንብረት የት እንዳስቀመጠው የሚያውቅ ሰው አልተገኘም ።»

«ጠቦርዝል ደ ፓሪ» ወይም የፓሪስ መጽሔት የጨባለው ደሞ በበኩሉ ቀጥሎ ያለውን አከለም አጠቃ ።

«ሚን ቫልጣ የተባለው የቀድሞ አስረኛ እንደገና ተያዘ ። እንደገና ከመያዙ በፊት አውነተኛ ስሙን ደብቆ በሌላ ስም እየኖረ ፣ በሸሚን በኩል ባዘ አትስቀኛ ከተማ ጨርቃ ጨርቅ ከንቲባ ሆኖ ሲሠራ ቆይቷል ። በዚሁ

@OLDBOOKSPDF

ከተማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ሲያነሡድም ነበር ። በኋላ ግን በአቃቤ ሕግ ያልተቆጠበ ጥረት ይህ ሰው ሊጋለጥና ፅፍርድ ሊቀርብ ቻለ ። ውሸማው አንዲት ሴተኛ አዳሪ ነበረች ። እሱ ሲያገ እሷ በደንጋጤ ሞተች ። እሱም ከተያዘበት አምልጦ ምስት ወይም አራት ቀናት ከቆየ በኋላ ፖሊሶች በፓሪስ ከተማ ውስጥ አግኝተው ያዙት ። የተያዘ ውም ከፓሪስ ወደ ሞንፈርመይ ለመሔድ በአንድ የሕዝብ ማመላለሻ ሲሳ ፈር ሰሰ ነው ። ጠፍቶ በቆየባቸው ምስት ወይም አራት ቀናት ውስጥ በባንክ አከማችቶት የነበረውን ሀብት አውጥቶ እንደወሰደ ይነገራል ። ሀብቱ ስድስት ወይም ሰባት መቶ ሺ ፍራንክ እንደሚደርስ ይገመታል ። ሀብቱን አውጥቶ የት እንዳደረሰው የሚያውቅ ሰው እስካሁን አልተገኘም ። የሆነ ሆኖ ይህ ወንበዴ በአውራ ጐዳና ላይ የንጥቂያ ወንጀል ፈጽሚል የሚል ክስ ተመስርቶበታል ። ወንጀሉ ከተፈጸመ ከስምንት ዓመታት በላይ ሆኗል ። ግንዘቡኝም የነጠቀው የሳቮያ ተወላጅ ከሆነ ወጣት ልጅ ነው ። መንበሩ የመከላከያ ክርክር ለማቅረብ ሳያፈቅድ ቀርቷል ።

«የአቃቤ ሕጉ ወኪል እንዳረጋገጠው ተከሳሹ በደቡብ ክፍለ ሀገር የሚገኘው የወንበዴዎች ቡድን አባል ከመሆኑም በላይ የንጥቂያውን ወን ጀል የፈጸመው ብቻውን አይደለም ። ሌሎች ተባባሪዎች አሉት ።

ዣኖን ቫልግ በፈጸመው ወንጀል የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል ። ይግባኝ የሚሰማ መብት ቢኖረውም ይህ ወንጀለኛ ይግባኝ አልጠየቀም ። ሆኖም በዜተክህኔት አማካይነት ጉዳዩ ከንጉሡ ዘንድ ቀርቦ ንጉሡ እንደተ ለመደው ምሕረት አድርገውለት የሞት ቅጣት ብያኔው በዕድሜ ልክ እስ ራት እንዲለወጥ ፈቅደዋል ። በዚህ ምክንያት ዣን ቫልግ ወደ ቱሎ ወህኒ ቤት ተወስዷል» ሲል ያመሥመ መጽሐፉ ።

ዣን ቫልግ ወደ ቱሎ ከተወሰደ በኋላ የቀድሞ መታወቂያ ቁጥሩ ተለውጦ 9430 ሆነ ።

የኤም ሱር ኤም ሀብት ከማድሌን መያዝ በኋላ አከተመ ። የማድሌን ሩብሪክ ተዘጋ ። ሕንጻዎቹ ፈራረሱ ። ሥራተኞቹ ተበታተኑ ። አንጻንዶቹ እስከነአካቴው ከተማውን ለቅቀው ወጡ ። በከተማው ነዋሪዎች መለከል ጥላቻና እጉል ውድድር ተፈጠረ ። ማድሌን የፈጠረው አዲሱ የማምረቻ ዘዴ ተቀየረ ። የምርቱ ጥራት ተጓደለ ። በፈሰ መተማመን ጠፋ ። ገበያው እየጠበበ ሔደ ። ለሠራተኞች የሚከፈለው ደመወዝ እያሽቆለቆለ ወረደ ። ኪሣራ ደረሰ ። በአካባቢው የነበሩትም ሹማረኞች የሚረዳቸው ሰው ሲየው ተቢታቱን ። ባሚሩ ማድሌን ቀደም ብሎ የፈራው ሁሉ ደረሰ ።

— 2 —

በ1823 ዓ. ም. በወርሃ ጥቅምት መጨረሻ ገደማ ላይ ኦሪዮን የተባ ለው ከባድ የመር መርከብ ለአድሳት ወደ ቱሎ ጠረፍ ገፀ ። 1823 ዓ. ም

@OLDBOOKSPDF

ፈረንሳይና አስፓኝ ጦርነት የተዋጉበት ዓመት ነበር ። የጦር መርከቡ ቱሎ ሲገባ የብዙ ሰዎችን መንፈስ ለመሳብ ቻለ ።

ኦሪዮን ለረጅም ጊዜ ተገሳቱሎ የቆየ ነበር ። ከቱሎ ጠረፍ አንዱ ገባ አድሳቱ ወዲያውኑ ተጀመረ ።

መርከቡ በመታደስ ላይ እያለ አንድ ቀን ጠዋት በጣም አስደንጋጭ የሆነ አደጋ ደረሰ ። መርከበኞቹ ከላይ ያሉትን የመርከቡን ማንቀሳቀሻ ሸራዎች ሲያጣጥሩ ሳሉ ከመሐከላቸው አንዱ ፥ ሚዛኑን ስቶ ሸራውን ወጥሮ በያዘው ወጋግራ ላይ ወደቀ ። ሲወድቅ ሳለ ከመርከቡ ምሰሶ ጋር የተያያዘ ገመድ አግኙት በአንድ እጁ ተንጠላጠለ ፥ ቁጥሙም በሁለት እጁ ። ወሬ ለማየት በአካባቢው ተከመልከሉ የነበረው ሕዝብ ከድንጋጤ የተነሳ መተንፈሱን ያቆመ መስለ ።

ሰውዬው እየሩ ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ ። ከሥሩ ያለው ባህር በጣም ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ አዘቅት መስሎ ይታየዋል ። በወንጭፍ ላይ እንደተንጠለጠለ ድንጋይ ይወዛወዛል ።

ሰውዬውን ለማዳን መከራ ማድረግ በጣም አደገኛ በመሆኑ ከባልደረቦቹ መሐከል አንድም መርከበኛ ሊረዳው አልደፈረም ። ሰውዬውም ጉልበቱ እየከዳው ፥ እጅ እግሩም እየተዳከመ ሐዲ ። ከአሁን አሁን ገመዱን ለቅቆ ባህሩ ውስጥ ገብቶ ይሰጥማል የሚል ስሜት ይፈጥራል ። ይህንን ላለ ማየት ብዙ ሰዎች ዓይናቸውን ወደ ሌላ ሲመልሱ ነበሩ ።

በመርከቡ ዕድሳት ላይ ከተሰማሩት መሐከል ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው የቱሎ እስረኞች ነበሩበት ። አደጋ የደረሰበት መርከበኛ ባልደረቦቹ ፈርተው ዝም ሲሉ ከእስረኞቹ መሐከል አንዱ ሰውዬውን ለማዳን መከራ እንዲያደርግ እንዲፈቀድለት ለመነ ። ተፈቀደለት ። እስረኛው ውም በአንድ የመዶሻ ምት እግረ መቁን ሰብሮ ፥ ከመርከቡ ምሰሶ ጋር የተያያዘውን ገመድ ይዞ ምስሶውን ቧጥጦ ይወጣ ጀመር ፤ እንደነበር ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ የመርከቡን ሸራ ወጥሮ ከያዘው ወጋግራ ደረሰ ። ለጥቂት ሰከንዶች ወጋግራውን በዓይኑ የሚለካው መስሎ ዝም ብሎ ቆየ ። በእነዚህ ሰከንዶች ውስጥ ዝግ ብሎ የሚንቀሳቀሰውን ሰውዬ በአደገኛ ሁኔታ ሲመዘመዘው ነበር ። ተመልካቹ ሕዝብ ትንፋሹን ቁርጥ አድርጎ ይመለከተዋል ። በመጨረሻም ሊያድነው የሔደው እስረኛ እንደሚጸልይ ሰው ዓይኑን ወደሰማይ አቀናና እንድ ርምጃ ሔድ አለ ። ከዚያም በኋላ በወጋግራው ላይ እየተረማመደ ሔዶ ከአንዱ ጫፍ ሲደርስ ይዙት የመጣውን ገመድ ወጋግራው ላይ ጎልሮ የገመዱን ሌላ ጫፍ ወደታች ለቀቀው ። ቁጥሙም በዚሁ ገመድ ተንጠላጥሎ ወደታች ይወርድ ጀመር ።

ሕዝቡ ኑሀንም በድንጋጤ ትንፋሹን ቁርጥ አድርጎ ወደላይ አንጋጠጠ ሁለቱን ሰዎች ይመለከታቸዋል ። እስረኛው እየተንጠላጠለ ወርዶ ከመር

@OLDBOOKSPDF

ከበኛው አጠገብ ደረሰ ። መርከበኛው ሰውነቱ ዝሎ ባሕሩ ውስጥ ለመው ደቅ ምንም ያህል ጊዜ አልቀረውም ነበር ። አሰረኛው በአንድ እጁ መርከ በኛውን አስጠግቶ ይህ ፥ እሱን እየጐተተና አሱም ራሱ ወደላይ እየተሳበ ወጥቶ መርከበኛውን ሊያድነው ቻለ ። ጠቅላላው ድርጊት እንደተጣምር የሚቆጠር ነበር ።

የተሰበሰበው ሕዝብ አፎይታ ተሰምቶት ለአሰረኛው በኃይል አጨ በጨበለት ። ተጥሎም ፣ ዛይህ አሰረኛ ይፈታ...! ይህ አሰረኛ ምሀረት ማግ ኘት ይገባዋል.....ህ አያሰ ይጩጩህ ጀመር ።

አሰረኛው ከነበረበት ከፍታ ወርዶ መርከበኛውን ከባልደረቦቹ ከተላቀለው በኋላ ወደ ራሱ ጭፍራ አመራ ። ሕዝቡ በዓይኑ ይከተለዋል ። አሰረኛው ከአንድ ቦታ ሲደርስ አራሱ እንደነረበት ሁሉ ተንበርክዶ ። ተገን ጸግዶም አለተረ ። ባህሩ ውስጥ ተወርውሮ ወደቀ ። ተመልካቹም ሕዝብ ይጫ.ጫህ ጀመር ።

አደገኛ አወጸደቅ ነው የወደቀው ። አልገፀዚራ የተባለው መርከብ ከአሮዮን መርከብ አልፍ ብሎ ቆም ነበር ። አሰረኛው የወደቀው በሁለቱ መርከቦች መሐከል ነበር ።

ወዲያወኑ አራት ሰዎች ጀልባ ውስጥ ገብተው አሰረኛውን ይፈልጉት ጀመር ። ነገር ግን ቢራኩቱም ሊያገኙት አልቻሉም ። አሰረኛው በሕይወት ሊገኝ ቀርቶ ሬሳው እንኳ ሳያገኝ ቀረ ።

በማግሥቱ የቱሎ ጋዜጣ ተጥሎ ያለውን አትም አወጣ ፤

ጥሳር 17 ቀን 1823 ዓ. ም. በአሪዮን መርከብ የአድሳት አገልግሎት ሲሰው ከነበሩት የቱሎ አሰረኞች አንደኛው ትኖንትና አደጋ ሳይ ወድቆ ሲንበረ አንድ መርከበኛ አርዳታ ሲያደርግ ቆይቶ ሲመለስ ባህር ውስጥ ሰጥሞ ቀረ ። አስከሬኑ አስካሁን ድረስ አልተገኘም ። ይህ አሰረኛ 9430 የሚል ቁጥር የተሰጠውና ስሙም ሚን ቫልጣ የተባለ ነበር ።»

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ሁለት

የተሰፋ ተፈጸሚነት

— 1 —

ሞንፈርሜይ በለ.ቫሪና በሼል መሐከል ይገኛል ። በዛሬው ጊዜ በቪላ ዎች ያጌጠ ፣ ከበርቴዎች የሚታዩበት ፣ ሰፋ ያለ ከተማ ይሁን እንጂ በ 1823 ዓ. ም. ደን ውስጥ የሚገኝ የገጠር ከተማ ነበር ። ማንኛውም ነገር ርካሽ ስለነበረ የከተማው ነዋሪዎች ብዙናንተው ይኖሩ ነበር ። ይሁን እንጂ ከተማው የተመሠረተው በኮረብታማ ሥፍራ በመሆኑ ነዋሪዎቹ የውኃ ችግር ነበረባቸው ።

በጋኜ አቅጣጫ በኩል የሚኖረው ሕዝብ ወደ ጫካ ሐዲ የኩራ ውሃ ቱድቱ ያመጣል ። በሸለ አቅጣጫ በኩል ያለው ሕዝብ ከኮረብታው አጋ ማሽ ላይ ከለው ምንጭ ውሃ ቱድቱ ያመጣል ። ምንጩ ከሞንፈመርይ ሩብ ሰዓት ያህል ያስኬዳል ።

የአኑቴናርዲዩ ሆቴል ግይኑቱ ተለት ተለቅ ያሉ በቶች ለእያንዳንዱ ባልዲ ውሃ አንድ ሳንቲም ያህል እየከፈሉ የሚያሻቸውን ውሃ ያገኛሉ ። የከተማው ውሃ ቀኟ በቀን ስምንት ሱ ያህል ይከፈልባል ። በበጋው ወራት አስከምሽቱ አንድ ሰዓት ፣ በክረምቱ ወራት አሰከ ቀኑ አሰራ አንድ ሰዓት ድረስ ብቻ ውሃ ይተዳል ። ከዚህ ሰዓት ውጭ ውሃ የሚፈልግ ሰው ቢኖር እሱ ራሱ ቀድቱ እንዲያመጣ ይገሄዳል ።

አኑቴናርዲዩ ከተመሰኑው ሰዓት ውጭ ውሃ ሲያስፈልጋቸው ክዚችን ለከው ያስመጡ ነበር ። ይህች ምስኪን ሊጅ ቀን ቀን ብቻ ሳይሆን ሌሊት በውድትት ጨለማ ወደ ጫካ ሐዲ ውሃ ለመቅዳት የምትገደድበትም ጊዜ ነበር ።

በ1823 ዓ. ም. በሷያት በዓል ዋዜማ የአኑቴናርዲዩ ሆቴል የብዙ እንግዶች አስተናጋጅ ሆነ ። በርካታ የፓሪስ ኑጋዴዎች የለደታን በዓል ምክንያት በማድረግ ወደሞንፈመርይ መጥተው ማዘጋጃ ቤተን አስፈቅደው

@OLDBOOKSPDF

በክሎግው ዋና መንገድ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር አቆመ ። ሴትዮትም ነጋ ዴዎች እንዲሁ አስፈቅደው በቢዝክርስቲያኑ አደባባይ መደብራቸውን አቆሙ ። የእኑቴናርዲዬ ሆቴል እስካለበት ፥ እስከበላንጊ ጐዳና ድረስ ያለው በታ በሙሉ መደብር በመደብር ብቻ ሆነ ። በዚህ ምክንያት የሞን ፈርመይ ሆቴሎችና መጠጥ ቤቶች በእንግዳ ተሞሉ ።

ያን ቀን ማታ በርክት ያሉ ጋሪ ነጂዎችና አግረኛ መንገደኞች በእ ኑቴናርዲዬ ሆቴል ውስጥ ተቀምጠው ሲጠጡና ትምባሆ ሲያጨሱ አመሹ። ሆቴል ቤቱ በአራት ወይም በአምስት ሻማዎች በርቷል ።

ማዳም ቴናርዲዬ ለእራት የሚሆን ምግብ ኢሳት ላይ ታበስላለች ። ሙሴ ቴናርዲዬ ከደንበኞቹ ጋር ቁጭ ብሎ ያወራል ። ኳሬት ከጠጋ ማወጫ አጠገብ ተቀምጣ ለእኑቴናርዲዬ ልጆች የእግር ሹራብ ትሠራለች ። ቡትሁ ለብሳለች ። የአንጨት ጫማ አደርጋለች ። የእኑቴናርዲዬ ልጆች ፥ ኤፖኒንና አቬሊግ ተኖሎ ባለው ክፍል ውስጥ ሆነው ሲጫወቱና ሲስቁ ይሰማል ። አልር አልርም የሕጻን ልጅ ለቅሶ ይሰማል ። ሕጻኑ የእኑቴናር ዲዬ የመጨረሻ ልጅ ነው ፥ ከሦስት ዓመታት በፊት ያተመለደ ። ማዳም ቴናርዲዬ አጥወደውም ። ሠለምን እንደተመለደ አላወቅም..... አልፈለግሁ ትም..... አንድ ቀን ሴሊት ቡበርድ ሰማን ነው የእኑሰኩ ት.... የቡርድ ው ጨት.....!ም ስትል ትሰማለች ብዙ ጊዜ ።

የሕፃኑ ለቅሶ እየባሰ ሲሔድ ፥ ሠልጅቪ ሲሎህ ኢዩሰማሽም እንዴ ? ሔደሽ እይው እንጂ!ም አላት ባሏ ።

ወአፍ! ሁል ጊዜ እንጸስትንረኝ ነው» ስትል አጉረመረመች ማዳም ቴናርዲዬ ። ሔዳ ልታስታግሰው ስላልፈቀደችም ሕጻኑ አሪታውን ቀጠለ.....

ሙሴ ቴናርዲዬ አምሳኛውን የልደት በዓሉን በቅርብ ጊዜ አክብሯል ። ማዳም ቴናርድዬም አርባኛውን የልደት በዓሏን አክብራለች ። ባልና ሚስት እግጂመሆናቸው መጠን በዕድሜ ይመጣጠናሉ ለማለት ይቻላል ።

አልታ ማጉበፍ ፥ ልብስ ማጠብ ፥ ምግብ ማብሰል ፥ የተቀረውንም ሁሉ የቤት ሥራ ማከናወን የማዳም ቴናርዲዬ ተግባር ነው ። ወንዳወንድ ነሽ ማዳም ቴናርዲዬ..... ጥርስ ተጣጣ ። ጩኸት ታበዛለች ። ብዙ ጊዜም ትራገማለች ። የቤት ልብስ የለበሰ ጠንቸኛ ኩሊ እንኳ ሴት አትመስልም ። ደሞም ጢም አላት... እንደወንድ ።

ባሏ ክሰማኖ ሰው ነው..... ደጉጉ ። ጤነኛ ቢሆንም ገመምተኛ ይመ ስላል ። ብልጣብልጥ ስለሆነ ፈገግ ማለት ደበዛል ። ጨዋ መስሎ ለመ

@OLDBOOKSPDF

ታየት ይጥራል ። መጠጥ ይወዳል ። እሱን ጋብዞ ለማስከር የቻለ ሰው አልተገኘም ። ትልቅ ጋያ ያጢሳል ። ብዙ ጊዜ ጥቁር የሆነ አሮጌ ኮት ይለብሳል ። በላዩ ላይ ካፖርት ቢጤ ይደርባል ። ከሰው ጋር በሚያወራበት ጊዜ አዋቂ ለመምሰል እነ ቮልቴርን ፣ እነ ሬናልን ፣ እነ ፖርኒን ፣ እነ ቅዱስ አውጉስጢኖስን ይጠቃቅሳል ። በዎተርሉ ጦርነት ተካፍያለሁ..... እንድ ቆስሎ የነበረ ጂኔራልን ከሞት አፋፍ አድኛለሁ እያለ ይሸልላል ። ይሁን እንጂ በሰኔ 18 ቀን 1815 ዓ. ም. በፈረንሳይና በእንግሊዝ መሐከል ፣ በና ፖሊዎንና በዌልንግተን መሪነት በተካሔደው ጦርነት ተካፋይ የሆነው በዝ ርፊያው እንጂ በወጊያው አይደለም ። ከወደቁ ወረኞች ልብስ ፣ ገንዘብ ፣ ሰዓት ፣ ቀለበት ፣ እና ሌላ ሌላም ነገር ዘረፈ እንጂ አልተዋጋም ። በሞን ፈርመይ ከተማ ሆቴል ቤት ለማቋቋም የበቃውም በዘረፈው ንብረት ምክ ንያት ነው ።

ቴናርዲዬ ስግብግብና አልጠግብ ባይ ሰው ነው ። ይሁን እንጂ ሀብ ታም ለመሆን አልቻለም ። በዚያ በልዶት ዋዜማ እንኳ አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ ያህል ዕዳ ነበረበት ።

ወደ ሆቴሉ የሚመጡ ሰዎች የሆቴሉ አስተዳዳሪ ማዳም ቴናርዲዬ የሆነች ይመስላቸዋል ። ነገር ግን እውነተኛ አስተዳዳሪው እሱ እንጂ እሷ አይደለችም ። ሳይንጫጫ ፣ ድምጹን ሳያሰማ ፣ እንደረቂቅ መንፈስ ሆኖ ሆቴሉን በበላይነት የሚያስተዳድረው እሱ ነው ። ማዳም ቴናርዲዬ ተሽቆጥቁጣ ትታዘዘዋለች ። ትፈራዋለች ። በሰው ፊት በምንም ሁኔታ ባሏን ቅር የሚያሰኝ ነገር ትንፍሽ አትልም ።

ሁለቱ ባልና ሚስት ከዜትን የቁም ስቅላት ያሳይዋታል ። ማዳም ቴናርዲዬ በጢስ ማውጫው አጠገብ የተንጠለጠለውን አሮንጋ አውርዳ ትገርፋታለች ። እንደገረድ ብታገለግላቸውም ባልየው እርባና ያለው ልብስ እንኳ አይገዛላትም ። መከረኛ ልጅ!

— 3 —

አራት አዳዲስ መንገደኞች ገቡ ፤ ያን ዕለት ምሽት ላይ ። ከዜት ስጋት ላይ ወደቀች ። ያለምክንያት አልነበረም ። ያን ቀን ማታ በውሃ ማጠራቀሚያው ጋን በቂ ውሃ አልነበረም ። እንግዶች ደሞ ውሃ ያስፈል ጋቸዋል ፤ ሰራሳቸው እንኳ ባይሆን ለፈረሶቻቸው ።

ማዳም ቴናርዲዬ ውሃ አስፈልጓት ወደማጠራቀሚያው ጋን ስት ሔድ ከዜት ይበልጡን ሥጋት አደረባት ። አምን በቂ ውሃ አልነበረም ። ማዳም ቴናርዲዬ የውሃ ማውረጃውን ከፍታ ስታንጨለጭሰው ከማማሽ ብርጭቆ ውሃ በላይ ለማግኘት አልቻለችም ። «ውሃው አልቆ የለም እንዴ አንቺነ» አለቻት ። ከዜት ከፍርሃት የተነሳ ለመተንፈስ አልደፈረችም ።

@OLDBOOKSPDF

ይባስ ብሎ ወዲያውኑ ከሦቱ እግዶች አንዱ መጣና ፈረሴ ውሃ አልጠጣም..... እስካሁን ድረስ ውሃ አልተሰጠውም!» ሲል ጮኸ ።

«ተሰጥቶታል እንጂ!» አለችው ማዳም ቴናርዲዬ ።

«አልተሰጠውም ነው የምለው!»

ከዜት ከነበረችበት ወጣ ብላ ፤ «ተሰጥቶታል ጌታዬ» አለችው ፤ «ፈረሰም ውሃ ተሰጥቶት ጠጥቷል ። በባልዲ ነው ያቀረብኩለት ። ያቀረብኩለትን ሁሉ ጥጥ አድርጎታል ።»

እውነት አልነበረም ። ከዜት ዋሸችው ።

«አንች ቀጣፊ.....! የምትናገሪው ውሸት ከቱመትሽ ይበልጣል » አለና ፤ «ፈረሴ ውሃ አልተሰጠውም ። ይህንን የሚውቀው ከህዝቃው ነው ። የፈረሴን ጠባይ መች አጣሁት» አለ ።

ከዜት በውሸትዋ ገፋችበት ። «በደምብ አድርጎ ነው ጥጥ ያደረገው ጌታዬ» አለችው ።

«ከዚህ በላይ አታናግሪኝ አንቺ ቀጣፊ! ሐጂና ውሃ ስጪው» አላት ።

ከዜት ሹልክ ብላ ጠረጴዛው ሥር ገባች ። አብዛኛውን ጊዜ የምትቀመጠው ከዚያ ነበር ።

«ፈረስም በእርግጥም ውሃ ካልተሰጠው እንዲሰጠው ይደረጋል» ብላ ማዳም ቴናርዲዬ ዞር ዞር ብላ ብትመለከት ከዜት አልታይ አለቻት ። «የት አባቷ ገባች» ብላ አጎንብሳ ጠረጴዛው ሥር ተመለከተች ። አገኘችና «አትወጪም እንዴ አንች ገልቱ» ስትል ጮኸችባት ። ከዜት ከጠረጴዛው ሥር ብቅ አለች ።

«አንች ገልቱ.... ሐጂሽ ውሃ ቅድትሽ አምጪ ።»

«ውሃኩ የለም ማዳም ።»

«እሱን መች አጣሁት! ወደምነጩ ወርደሽ ቶሎ ቅድትሽ ተመለሺ ።»

ከዜት ባልዲ ፍለጋ ስትሔድ ማዳም ቴናርዲዬ ታገሪመርም ገባች ፤ «ከምንጭ ውሃ አልጠሉም..... ይህች ከይሲ.....!» እያለች ። ቀጥላም ከመሳቢያው ውስጥ ገንዘብ ፈላልጋ አወጣችና ፤ «ስሚ አንቺ ገልቱ.....!» ስትል ተጣራች ፤ «ከምንጩ ውሃ ቅድተሽ ስትመለሺ በዚያው እግርሽ ወደ ዳቦ ቤት ገራ ብለሽ ዳቦ እንድጓገዢ..... እንቺ 15 ሱ» አለቻት ።

ከዜት ገንዘቡን ተቀብላ ፣ ባልዲዋንም ይዛ ወጥታ ሔዶች ።

@OLDBOOKSPDF

ከእንቴናርዲዩ ሆቴል ቤት ጀምሮ እስከቤተክርስቲያኑ ድረስ ባለው ሥፍራ የተሠሩት መደብሮች በሚገባ በርተው ይታዩ ነበር ። ምዕመናኑ ለመገፈቅ ሴሊት ቅዳሴ ወደቤተክርስቲያን መሔዳቸው የማይቀር መሆ ኑን ነጋዴዎቹ ያውቁ ስለነበረ የነሱን ሳይጎ ለመሳብ በማሰብ ነበር መደብራቸውን እንዲያ ያበሩት ።

ከመደብሮቹ አንዱ ከእንቴናርዲዩ ሆቴል ትይዩ ነበር ። በሚጥበረበ ረው ብርሃን አማካኝነት በውስጡ ያሉት ፣ በጣም የተጌጠና ያማሩ አሻን ጉሊቶች ይታዩበታል ። በተለይ አንድ አሻንጉሊት ጉላ ብሎ ይታያል ። ላጣም ቅልቅ ነው ። በነጭ ጨርቅ ላይ ሰፍሯል ። ሐምራዊ ቀለም ያለው ልብስ ዕብሏል ። ከላይ ወርቃማ የወፍ ቅርጽ አሰበት ። በእውነተኛ ጸጉር የተጌጠ ሴት አሻንጉሊት ነው ። ያን ቀን ከአስር ዓመት በታች ያሳቸው ሕጻናት በሙሉ አሻንጉሊቱን ሲያደንቁት ውለዋል ። ዋጋው ውድ ስለሆነ ደፍሮ የሚገዛው ወላጅ አልተገኘም ። ኤፖኒንና አዜልማ ለረጅም ጊዜ ሳያስተውሉት አልቀሩም ፤ ያን የመሰለ አሻንጉሊት አንዲኖራቸው በመ ጽጠጥ ። ከዚትም ሠረቅ አድርጋ አይታው ነበር ።

ከዚት ባልዲሞን ይዛ ከወጣች በኋላ አሻንጉሊቱን ቀረብ ብላ የማ የት ፍላጎት ስለደረባት ወደዚያ አመራች ። ቀረብ ብላ ስታየውም ይበልጥ አምሮት አደረባት ። ሰጊዜውም ቢሆን የተሳከችበትን ሥራ ረስታ ፈዝዛ ታስተውሰው ገባች ። በሕልም እንጂ በውን የሚታይ ነገር አልሆነ አሳት ። ልትመኘው እንጂ ልታገኘው የማይቻላት ብርቅ ነገር ሆነባት ። ፈይሃንን አሻንጉሊት ለማግኘት ንግሥት መይም ልዕልት ሆኖ መወለድ ያሻል» ስትል አሰበች ።

የአሻንጉሊቱን ውብ ልብስና ውብ ጸጉር በጥሞና ተመለከተችና «ይህ አሻንጉሊት ምን ያህል ደስተኛ ይሆን ነ» ስትል አሰበች ። ዓይኗን ከዚያ ለመንቀል አልቻለችም ። ይበልጥ ባስተዋለችው መጠን ይበልጥ ይስባት ፣ ይበልጥ ያጓጓት ጀመር ። መግሥት ለማያውን በዓይኗ ያየች መስላት ። የልጅ ነገር!

እንዲሁ ፈዝዛ እያለች ማዳም ቲናርዲዩ ወደ ውጭ ስትመለከት ዓይ ኗቿ በኮዜት ላይ አረፉ ። «አንቺ ገልቱ.... እስከሁን እዚሁ አለሽ.....? በይ..... ታጣኝያታለሽ.....! እዚህ ምን ልትፈጥሪ እንደፎየሽ ትጥቢጥታለሽ.....! ወይኮ አሁን ፈጠን ብለሽ ሒጂ.....!» ስትል ተንጎደጎደችባት ።

ኮዜት ተደናግጣ ባልዲዎን ይዛ በረረች ።

@OLDBOOKSPDF

እስከቤተክርስቲያኑ ድረስ ያለው መንገድ በየመያዘቡሩ በበራው መብራት የሚታይ ቢሆንም ከዚያ ወዲያ ያለው መንገድ ጭለማ ለብሷል ። ከዜት ባልዲዋን እያንገጫገጨች በጭለማ ትጓዝ ጀመር ። ርቃ በሔደችም ቁጥር ጭለማው እየከበደ ሔደ ።

ብቻዋን በጭለማ ስትጓዝ ቆየችና ከአንድ ሥፍራ ስትደርስ አንዲት ሴትዮ አጋጠመቻት ። «ይህች ፍሬ ልጅ ማን ነች?» ስትል አሰበች ሴት የዋ ። ከዜት መሆንዋን ስትገነዘብም ፤ «እኽ.....! ዘሩኟ ወፍ ነች!» አለች በልቧ ።

ከዜት የከተማውን መጨረሻ ቤት ካለፈች በኋላ ፈርታ ቆም አለች ። ባልዲዋን እመሬት ላይ አስቀምጣም እጇን አንስታ ራሷን ታክክ ጀመር ። ሕጻናት ሲጨንቃቸው ራሳቸውን ማከክ ይቀናቸዋል ። ያለችበት ቦታ ሜዳ ነው ። ሰው የለበትም ። አውሬዎች ግን አሉበት ። ምናልባት መናፍስትም ከዚያ አይጠፉም ። አውሬዎች ሣሩ ላይ ሲራመዱ ኮቴአቸውን ሰማች ። መናፍስትም በእርግጥ ያየች መሰላት ። ከዚያም በኋላ ባልዲዋን አንስታ ወደመጣችበት ዞራ እየተራመደች ፤ «ሰውዬው ምን ያደርገኛል! በምንጩ ውሃ የለም አለዋለሁ» ስትል አሰበች ።

አንድ መቶ እርምጃ ያህል ከተጓዘች በኋላ ግን እንደገና ቆማ ራሷን ታክክ ገባች ። ስለእነቴናርዲዬም ታስብ ጀመር ። «ምን ባደርግ ይሻለኛል?» አለች ዞር ዞር ብላ እየተመለከተች ፤ «ምን ይውጠኛል? ወዴት አባቴ እገባለሁ?»

ውሃ ሳትይዝ የመመለስ ሃሳብ ሰላስፈራት ፈቷን እንደገና ወደምንጩ አቅጣጫ አዙራ ትሮጥ ጀመር ። ሔዳ ሔዳ ጭለማ ከዋጠው ጫካ ውስጥ ገባች ።

እንባ እንባ አላት ። ጭለማው ከበባት ። ከጫካው ዳርቻ እስከምንጩ ድረስ ያለው መንገድ ሰባት ወይም ስምንት ደቂቃ የሚያስኬድ ነበር ። ቀን ቀን ብዙ ጊዜ የተጓዘችበት ስለሆነ መንገዱ አልጠፋትም ። ዓይኗን ወደ ቀኝም ሆነ ወደግራ ሳታዞር ፊት ለፊቷ ያለውን ብቻ እያየች ፣ በደመነፍስ እየተጓዘች ከምንጩ ደረሰች ።

ከዜት ግራ እጇን ዘርግታ ከምንጩ ዳርቻ የነበረውን የዛፍ ቅርን ጫፍ ያዝ አደረገችው ። ከዚያም በኋላ ጐንበስ ብላ ባልዲውን ውሃው ውስጥ ደፈቀችው ። ጐንበስ ስትል ሳለች በሽርጧ ኪስ ውስጥ የነበረው የ15 ሴ ሳንቲም ወጥቶ ምንጩ ውስጥ ወደቀ ። እሷ ግን ተሸብራ ስለነበረች ልብ አላለችውም ። ከዚያም በኋላ ውሃ የተሞላውን ባልዲ ስባ አውጥታ ጫር ላይ አኖረችው ።

@OLDBOOKSPDF

ድክምክም አላት ። ወዲያውኑ ለመመለስ ብታስብም አልቻለችም ። ትንሽ ማረፍ ስላስፈለጋት ሣሩ ላይ ቁጭ አለች ።

ዓይኖቿን ከደነቻቸው ። መልሳም ከፈተቻቸው ። ስማዩ ጢስ የመሰለ ጸሐና አለበት ። ጁፒተር የተሰኘውም ትልቅ ኮከብ ታያት ። ከዚያ በፊት አስተውላው አታውቅ ኖሮ አስፈራት ፤ የሚያበራ ቁስል መስሎ ።

ቀዝቃዛ ነፋስ ይነፍስ ጀመር ። ሣር ቅጠሉም በነፋሱ ኃይል ይርገበገብ ጀመር ። ከዚት ብቻዋን ጫካ ውስጥ መሆኗን ስትገነዘብ የባሰውን ፍርሃት ወረራት ። ሕጻን ልጅ ይቅርና አዋቂም ቢሆን በጭለማ ሌሊት ጫካ ውስጥ መገኘት ያስፈራዋል ። ከፍርሃቷ ብዛት የተነሳ ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ። አራሷን ረጋ ለማድረግ ያህል አንድ... ሁለት..... ሦስት..... እያለች ትቆጥር ጀመር ። እስከ አስር ድረስ ቆጠረች ። መልሳም አንድ..... ሁለት ሦስት..... እያለች እስከ አስር ድረስ ቆጠረች ። ውሃ ስትቀዳ እጇን ምንጩ ውስጥ አስገብታው ስለነበረ ቅዝቃዜው ጠዘጠዛት ። ከዚት ተነስታ ቆመች ። ከዚያ ቦታ ለመሸሽና ብርሃን ካለበት ለመድረስ ተቻኮለች ። ባልዲውን ውሃ እዚያው ትታው ሮጣ ብትሔድ ደስ ባላት! ነገር ግን የማይታሰብ ሆነባት ። ማን አባቷ ያስገባታል! የባልዲውን መያዣ በሁለት እጇ ይዛ አነሳችው ። በጣም ከበዳት ።

አስራ ሁለት ርምጃ ያህል እንደተጓዘች ከብደቱ ስላየለባት ባልዲ ውሃ መልሳ መሬት ላይ አወረደችው ። ለትንሽ ጊዜ አርፋ እንደገና አነሳችው ። ጥቂት ርምጃ ሔደችና እንደገና ቆመች ። አሁንም ለአጭር ጊዜ አረፈችና መንገዷን ቀጠለች ። እንደአርጊት ወደፊት ዘንበል ብላ ነበር የምትጓዘው ። የባልዲው ከብደት ክንዷን አዛለባት ። መያዣውም ብረት ስለሆነ ቅዝቃዜው እጇን ቆጠቆጣት ። ቆም—ራመድ ፣ ቆም—ራመድ ስትል የባልዲው ውሃ እየተንቦራጨቀ ወጥቶ እግሯ ላይ ይቸለስ ነበር ። የዚህችን ልጅ ስታይ እግዚአብሔር እንኺ ሌላ ያየ ሰው አልነበረም ። እናቷ ይህንን ብታይ ኖሮ.....!

ቁና ቁና እየተነፈሰች መንገዷን ቀጠለች ። እንባዋ ተናነቃት ። ለማልቀስ ግን አልደፈረችም ፤ እንቲኖርዲዬ በሩቅ ሆነው የሚያዩዋት እየመሰላት ።

መንገዱ አልገባደድ አላት ። በዚህ ቀሰስተኛ ርምጃ ከቀጠለች እቤት ለመድረስ አንድ ሰዓት ያህል እንደሚወስድባት ተረዳች ። ይህን ያህል ጊዜ ከወሰደባትም ዳሊ እንደሚጠብቃት ተገነዘበች ። በዚህም ምክንያት ሞንቅ አላት ። የሆነ ሆኖ ፈጥና ለመራመድ አልቻለችም ። እንዲያውም የባሰውን ድክም ፣ ድክምክም ስላላት እንደገና ቆም ብላ አረፈች ። ከዚያም በኋላ የተረፋትን ኃይል በሙሉ ሰብስባ ባልዲዋን አንስታ መንገዷን ቀጠለች ። «ምነው አምላኬ! ምነው ፈጣሪዬ!» ስትል አማረረች ።

@OLDBOOKSPDF

ለክ በዚህ ጊዜ የባልዲው ክብደት ቀሰል ሲልላት ተሰማት ። አንድ ሰውዬ ጠጋ ብሎ ባልዲዋን ያዘ አደረገው ። ቶና ብላ ተመለከተችው ። መልኩን ለይታ ባታየውም ሰውዬው ግዙፍ ነው ። ኮቴውን ሳትሰማ ቀረች አንጂ ከቧስቲላዋ ነበር የመጣው ። ባልዲዋን ከአጂ ወስዶ በእጁ አን ጠልየሎ በገና ይጓዝ ጀመር ። ከዜት ከፍርሃቷ ተላቀቀች ።

— 6 —

ያን ቀን በስምንት ሰዓት ገደማ አንድ ሰውዬ በፓሪስ ከተማ ውስጥ ሰው አጅግም በማይታይበት በሆስፒታል ጉዳና ከወዲያ ወዲህ ሲል ነበር ። ማደርያ ቦታ የሚፈልግም ይመስል ነበር ።

ጐስቋላ ቢመስልም የሚያከብሩት ሃይነት ሰው ነበር ። አሮጌ ቆብ ደፍቷል ። ሽካራና በትዙ ኮት ሰብሷል ፤ ቢጫ ቀሰም ያለው ። ስደርያም ያርሷል ። ጥቁር ቁምጣ ሱሪ ታጥቋል ። ጥቁር የጣር ሽራብ አደርጓል ። ባለዘለበት ትልቅ ጫማም ለክቷል ። ከስደሳ ዓመት ዕድሜ የዘለለ ይመስ ላል ። ጸጉሩ ሽብቷል ። ፊቱ ተጨማዷል ። ከአመለካከቱ ርጋታ ይታይ በታል ። በግራ እጁ የተጠረ ነገር ይዟል ። በቀኝ እጁ ዘንግ ጨብጧል ።

በዚያን ዘመን በየቀኑ በስምንት ሰዓት ገደማ ንጉሥ ሉዊ 18ኛ በሠ ረገላ ሆኖ ፥ በክብር ዘበኞቹ ታጅቦ በሆስፒታል ጉዳና ሲያልፍ ማየት የተ ለመደ ነበር ። በአካባቢው የሚኖሩ ድሆች ሴቶች ስምንት ሰዓት መድረሱን የሚያወቁት ንጉሡ በዚያ ሲያልፍ በሚያዩበት ወቅት ነበር ።

ቢጫ ኮት የለበሰው መንገደኛ ግን የአካባቢው ነዋሪ ባለመሆኑ ንጉሡ በዚያ አካባቢ እንደሚያልፍ አያውቅም ነበር ። በዚህ ምክንያት ንጉሡ በክብር ዘበኞቹ ታጅቦ ልክ በስምንት ሰዓት ከቸቹ ሲል በማየቱ በጣም ተገረመ ። ያልጠበቀውና ያሳሰበው ስለሆነበት ከአንድ ግድግዳ ጥግ እንደ መደበቅ አል ።

በንጉሡ መረገላ ከንጉሡ ፊት ለፊት ተቀምጠ የነበረው የክብር ዘበ ኞቹ አለቃ አየውና «ያ ሰውዬ መገዘኛ ይመስላል ጃንሆይ» አለ ንጉሡን እያየ ።

ከንጉሡ ቀድመው ሌዬው መንገዱን ሲያስሱ የነበሩ ፖሊሶችም ስውዬውን ሳያስተውሉት አልቀሩም ። ከመፈክላቸው አንዱ ተከታትሎ እንዲይዘው ትዕዛዝ ተሰጠው ። ሰውዬው ግን ፈረጠጠ ። ፖሊሱ ደርሶ ሊያዘው አልቻለም ።

ስውዬው ከፖሊሱ አምልጠ ከሔደ በኋላ እርምጃውን በእጥፍ አፋ ጠነው ። የሚከተለው ሰው መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥም ያህል አዞ ንም አሁንም ኀልመጥ ኀልመጥ ይል ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

መንግዱን ተጠለና ወደ ላኚ ስመሔድ የትራንስፖርት ጽ/ቤት ወደ ሚገኝበት ቦታ አመራ ። የሕዝብ ማመላለሻው ከዚያ የሚነሳው በአስር ሰዓት ተኩል ነበር ። ጋሪውና ፈረሶቹ ዝግጁ ሆነው ቆመው ኮዳጮቹም ሲሰፈሩ ነበሩ ።

«ቦታ ይገኝ ይሆን?» ሲል ጠየቀ ቢጫ ኮት የለበሰው መንገደኛ ።
«አንድ ቦታ አለ..... ከኔ ጎን» አለው ጋሪ ነጂው ።
«እግዲያውስ አሳፍረኝ ።»
«ግባ ።»

ጋሪ ነጂው የሰውዬውን ሙርንቱሳምነት ተመልክቶ እምነት ሰላጣ በትሂሰቡን በቅድሚያ አስከፈለውና ፣ «አሰስ ላኚ ድረስ ነው የምትሄዘው?» ሲል ጠየቀው ።

«አዎን» ሲል መለሰለት ሰውዬው ።

ጋሪው ከጣቢያው ተንቀሳቀሰ ። ኬላውን ከለፉ በኋላ ጋሪ ነጂው ሰውዬውን ሲያነጋግረው ሞከረ ። እሱ ግን በንግግሩ በጣም ቁጥብ ሆነ ። ብዙ ሰማውራት አልፈተደም ።

ጉርኔንና ነዱ—ሱር ማርንን አልፈው ሔዱ ። አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ከሼል ደረሱ ። ጋሪ ነጂው ፈረሶቹን ለማሳረፍ ፈልጎ ከመንገዱኛ ማረፊያ ሆቴል ቆም አለ ።

ቢጫ ኮት የለበሰው ሰውዬ ወደ ላኚ አገሀለሁ ቢልም በትሩንና የተቋጠረ ዕቃውን ይዞ ከጋሪው ወርዶ ዝልክ ብሎ ቀሰወረ ። ጋሪ ነጂውም ሆነ ሌሎቹ ተሳፋሪዎችም የት እንደገባ አላዩትም ።

ጋሪው ወደ ላኚ ግሀውን ሰመቀጠል ከተነሳ በኋላ ጋሪ ነጂው ወደ ኮዳገቹ ዞር ብሎ ፣ ለየቅደመ ሰውዩ የዚህ አገር ሰው አይደለም ። ከዚህ ቀደም አይቼው አላውቅም ። ቁርጪ ድግ ቢመስልም ለግንዙብ ደንታ ያለው ዓይነት አይደለም ። ለላኚ ከፍለ ከሼል መውረዱ አያስገርምም! ጊዜው መሸት ሸት ብሏል ። የሚታዩ ቤቶች ሁሉ ገማ ናቸው ። ሰውዬው ከሆቴል ቤቱ አልገባም ። በመንገድም የለም ። እንዲያው በቅጽበት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ አይደለምነ አሳቸው ።

ሰውዬው የውሃ ሽታ ሆኖ አልቀረም ። በሼል ዋና ጉዳና ፈጠን ፈጠን ብሎ ተራመደና ከቤተክርስቲያኑ ሕንጻ ከመድረሱ በፊት ወደቀኝ ታጥፎ ወደሞንሬመይ የሚወስደውን ጉዳና ተያያዘው ። አገሩንና መን ገዱን የሚያውቅ ሰው እንጂ እንግዳ አይመስልም ነበር ።

እርምጃውን አፋጥኖ በዚው መንገድ ነጐደ ። ከአንድ ሥፍራ ሲደርስ የሰው ድምጽ ሰማና ጉድባ ውስጥ ገብቶ ተደበቀ ። ሰዎቹ አልፈውት እስ

@OLDBOOKSPDF

ዝሐዱ ድረስ እዚያው ቆየ ። ጊዜው ጨለምለም ብሎ ስለነበረ ጉድባ ውስጥ ገብቶ ባይደበቅም ሰዎቹ ሊያዩት ባልቻሉም ነበር ።

መንገዱ ከጥ ከጥ እያለ ፥ ዳገት እየሆነ ሔደ ። ሰውዬው በቀጥታ ወደ ሞገሬርመይ በማዘገም ፊንታ አሳቻ አሳቻውን መንገድ ይዞ ወደ ጫካው ገባ ። ጫካ ውስጥ ከገባ በኋላ ርምጃውን ገታ አድርጎ ፥ ቀስ ብሎ ይጓዝ ጀመር ። ከአንድ ቦታ ሲደርስ መንገዱ የጠፋው መሰሎ ቆም አለ ። ከዚያም በኋላ እያላበረ ሔደና ነጫጭ ድንጋዮች ካለበት ገላጣ ሥፍራ ደረሰ ። ጠጋ ብሎ ድንጋዮቹን አስተዋላቸው ። እልፍ ብሎ አንድ ትልቅ ዛፍ ነበር ። ወደዚያ ሔዶ ዛፉን በእጁ ደባበሰው ። ከዚህ ዛፍ ፊት ለፊት ሌላ ዛፍ ነበር ፤ ቅርፊቱ ተልጦ ቅርቅሮ በምስማር የተመታበት ። ሰውዬው ወደዚያም ሔዶ ፥ በጣቱ ቆሞ ቅርቅሮውን በእጁ ዳሰሰው ። ከዚያም በኋላ በዚህ ዛፍና በድንጋዩ ቁልል መሐከል ይረማመድ ጀመር ፤ የሚረማመድበት መሬት መቆፈር አለመቆፈሩን ለማረጋገጥ እንደፈለገ ሁሉ ።

ይሁንን ካደረገ በኋላ የድን ውስጥ ጉዞውን ቀጠለ ። ይኸው ሰውዬ ነበር ከዚችን ጫካው ውስጥ አግኙኑ ፥ ባለዲሞን ብሎ የተሸከመላት ።

— 7 —

"ጮርንን ባለ ድምጽ ፤ ፈለጇ..... ባልዲሽ ከባድ ነው» አላትና ፈለመሆኑ ዕድሜሽ ስንት ነው?» ሲል ጠየቃት ።

«ስምንት ዓመት ።»
«እና ከሩቅ ቦታ ነው ውሃውን ያመጣሽው?»
«ጠጫካው ውስጥ ካለው ምንጭ ነው የቀዳሁት ።»
«ሩቅ ነው የምትሔጂበት ቦታ?»
«ከዚህ ሩብ ሰዓት ያህል ያስኬዳል ።»

ሰውዬው ዝም ብሎ ቆየና ፤ «እና..... እናት የለሽም?» ሲል ጠየቃት ።
«እኔ አላውቅም ። እናት ያለችኝ አይመስለኝም ።»

ሰውዬው ቆም ብሎ ባልዲውን መሬት ላይ አኖረው ። ጐንበስ ብሎም ሁለት እጆቹን በልጅቷ ትከሻ ላይ አሳረፋቸውና ጭስማ ቢሆንም ፊቷን ለማየት ሞከረ ። ፊቷ ደበዘዘ ብሎ ታየው ።

«ስምሽ ማነው?» አላት ።
«ኒነዜት» አለችው ።

ይህንን ሲሰማ አንዳች ነገር ጠቅ እንዳደረገው ሁሉ ሰውነቱን ነዘረው ። እንደገና ተመለከታትና እጆቹን ከትከሻዋ አንሰቶ ባልዲውን አንስቶ ይዞ መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

@OLDBOOKSPDF

«ለመሆኑ የት ነው የምትኖሪው?» አሳት ።
«የምኖርበት ቦታ ሞንፈርመይ ይባላል..... የሚያውቁት ከሆነ ።»
«ወደዚያ ነው አሁን የምናመራው?»
«አዎን ።»

አውንም ቆም አለና መልሶ መራመድ ጀመረ ።
«በዚህ ጭለማ ውሃ እንድትቀጪ የላከሽ ማነው?»
«ማዳም ቱናርዲዬ»
«ማዳም ቱናርዲዬ?» ድምጹ ተንቀጠቀጠ ፤ «ሥራዋ ምንድነው?»
«ኖኔ እመቤት ናቸው ። ሞቱል ቤት አላቸው ።»
«ሞቱል ቤት.....? እንደሱ ከሆነ እኔም ከዚያ አድራለሁ..... መንገዱን አሳዪኝ ።»

«ወደዚያውኳ ነው የምናመራው ።»

ሰውዬው ፈጠን ፈጠን ብሎ ይራመድ ጀመር ። ከዚት ያለችግር ተከተለችው ። ድካሟ ወጥቶላት ነበር ። በልቧም አዲስ ደስታና ተስፋ ተሠርጾ ነበር ።

«በማዳም ቱናርዲዬ ቤት ሠራተኛ የለም ለመሆኑ ?» አሳት ።
«የለም»
«አንቺ ብቻ ነሽ?»
«አዎን ።»

ለአጭር ጊዜ ዝምታ ሆነና ፤ «ብቻ..... ሁለት ትናንሽ ልጆች አሉ» ስትል አከለችበት ።
«ማን ናቸው ልጆቹ?»
«ፖኒንና ዜልማ» አለችው ። ኤፖኒንንና አዜልማን «ፖኒንና ዜልማ ብላ ትጠራቸው ነበር ።
«ማን ናቸው እነሱ?»
«የማዳም ቱናርዲዬ ልጆች ናቸው..... ሴት ልጆቿ ።»
«እና እነሱ ምን ይሠራሉ?»
«እነሱማ አሻንጉሊት አሳቸው ። በአሻንጉሊታቸው ሲጫወቱ ይውላሉ ።»
«ቀኑን ሙሉ?»
«አዎና !»
«አንቺስ?»
«እኔማ ሥራ አለብኝ ።»
«ቀኑን ሙሉ?»

ኒይናቿ እንባ ቋጠሩ ። ሰውዬው ግን ይህንን አላስተዋለም ፣ ጭለማ ስለነበረ ።
«አዎን» አለችው ።

@OLDBOOKSPDF

ለትንሽ ጊዜ ዝም ብላ ቆየችና ፤ «አንዳንድ ጊዜ ግን ሥራዬን ከጨረስኩ በኋላ ሲፈቀድልኝ እኔም እጨወታለሁ» ስትል አከለችበት ።

«መጫወቻ አለሽ?»

«መጫወቻ የለኝም ። ፖኒንና ዜልማ አሻንጉሊታቸውን አይሰጡኝም ። ብቻ..... ይህችን የምታህል ከቆርቆሮ የተሠራች ስለት አለችኝ» አለችው የሕጻን ጣቷን እያሳየችው ።

«ስለቱ አይቆርጥም?»

«ይቆርጣል እንጂ! ሰላጣ ወይም የዝንብ አንገት መቁረጥ ሲያቅተው ።»

ከመንደሩ ደርሰው በዳቦ ቤቱ በኩል አለፉ ። ኮዜት ግን ዳቦ ግዢ መባሉዋን ረሳችው ። ሰውዬው ሌላ ጥያቄ ሳይጠይቃት በዝምታ ተከተላት ።

ቤተክርስቲያኑን አልፈው ከሐዲዱ በኋላ ሰውዬው በዚያ አካባቢ የተመሩትን መደብሮች አስተውሎ ፤ «ምንድናቸው?» አላት ።

«ሰገና በዓል የተሠሩ መደብሮች ናቸው» አለችው ።

ከሠቴል ቤቱ ሲቃረቡ እጇን ነካ አደረገችውና «አሁን ባልዲውን ቢሰጡኝ.....» አለችው ።

«ለምን?» አላት ።

«ማዳም ባልዲውን ሌላ ሰው ተሸክሞልኝ ቢያዩ ደስ አይላቸውም..... ይቆጡኛል..... ይደበድቡኛል» አለችው ።

ሰውዬው ባልዲውን ሰጣት ።

— 8 —

ኮዜት ቀደም ብላ ያደነቀችውን አሻንጉሊት በሲያፍ አየት አደረገች ውና ሐዲድ ብላ የሠቴል ቤቱን በር አንኳኳችው ። በሩ ተከፈተ ። እመቤቷ ሻማ ይዛ ብቅ አለች ።

«አ'ቭ! አንቺ ነሽ! አንች ገልቱ! እስካሁን ወዴት አባሽ ቆየሽ ለመሆኑ?»

«መኝታ የሚፈልግ ሰው አለ ማዳም» አለቻት ኮዜት እየተንቀጠቀጠች ።

«ማነው እስኪ?»

«እኔ ነኝ» አላት ሰውዬው ቆቡን ከራሱ አውርዶ ።

የልብሱ መናኛነት ደስ አላሰኛትም ። የያዘውም ዕቃ ትንሽነት እንዳታከበረው አገዳት ። «በል እሺ ግባ» አለችው ።

ጉበቱ ስታየው የባሰውን ናቀችው ። ወደባሷ ሐዳ አማከረችውና ተመልሳ መጥታ ፤ «ይቅርታ አድርግልኝ ሰውዬ..... ያልተያዘ ክፍል የለኝም» አለችው ።

@OLDBOOKSPDF

«ጥሩ ክፍል ካልተሰጠኝ ብዬ አላስቸግርም» አላት ሰውዬው ፤ «ከፈረሶች ጋላ ውስጥ ቢሆን እንኳ ማደሪያ ካገኘሁ ሲደምበኛ ክፍል ፤ ሚከፈለውን ሂሳብ ስመክፈል ፈቃደኛ ነኝ ።»

«እንግዲያውስ አርባ ሱ ትከፍላለህ» አሰኙው ።
«እሺ ይሁን» አላት ፈጠን ብሎ ።

ከጋሪ ነጂዎቹ አንዱ ይህንን ሲሰማ በጣም ተገርሞ ፤ «አርባ ሱ፣ የአንድ ክፍል ዋጋ ሀያ ሱ አይደለም እንዴ?» አለ ።
«እሱ አርባ መክፈል አለበት» አለኝ ማዳም ቱናርዲዬ ፤ «የሱ ዓይ ኑቶቹን መንጊኖች የማስከፍላቸው ይኸው ነው ።»
«ለመሆኑ ነው..... የሱ ዓይኑቶቹ መንጊኖች ክፍል ያበላሻሉ» አለ ባለዬው ።

እነሱ ቃል ሲለዋወጡ ሳሉ መንሄናቸው ዕቃውንና ሀንጉን አግዳሚ መንበር ላይ አሰተኙለት አሰቃ ፈሱ ከአንድ ጠረጴዛ አጠገብ ሔዶ ቁጭ አለ ። ከዚት ፈጠን ብላ አንድ ብርጭቆና አጉድ ጠርሙስ ወይን ጠጅ አምጥታ ጠረጴዛው ላይ አኖረችለት ። ፈረሴ ውሃ አልተሰጠውም ብሎ አጉረምርሞ የነበረውም ነጋዴ ባልዬውን ይዞ ወጣ ።

ከዚት ወደ ተሰመደው ሥፍራዋ ፣ ወደጠረጴዛው ሥር ጉብታ ፣ የእግር ሹራብ ትጠልፍ ገባች ። ስውዬው ወይን ጠጁን እያጣጠመ ከዚትን ልብ ብሎ ተመልከታት ። ዘድስት ብትኖር ናር ውብ ልጅ ሳትሆን ባል ቀረች ነበር ። አሁን ግን ቆንጅ የምትባል አይደለችም ። ከሳሳ ነች ። ስም ንት ዓመት ዕድሜ ዚኖራትም ቁርክሳለች ። በወጌር የሚያነበ ዓይኖቿ ጉድጉደዋል ። የአፏ ጥግ ተግ ኩርባ ሠርተዋል ። የስውነቷ አጥንቶች አግጠዋል ። ቅልጥሞቿ በጣም ቀጫጭንና ቁያይ ናቸው ። የአንገቷ ሥር ሠርጉዱ ስለሚታይ ታሳዝናለች ። የለበሰቻቸው ልብሶች ደብያለዎች ናቸው ። ክረምትም ሆነ በጋ የምትለብሳቸው እነዚህኑ ነው ።

በርዷት ብትገባም ወደ እሳቱ ስመጠጋት አልዬረረችም ። በፍርሃት ተሸማችታ ወደ ጠረጴዛው ሥር ጉብታ ሥራዋን ቀጠለች ። ሰውዬው ዓይኑን ከእሷ ስመንቀል አልቻለም ።

«ሀንገራችን ላይ..... ዳቦው የት አለ ?» አሰኝት ማዳም ቱናርዲዬ በደንገት ።

ከዚት እግረ መንገዷን ዳቦ ገዝታ እንድታመጣ መታዘዝዋን አሁን ገና አስታወሰች ። በፍርሃትም ተብረከረከች ። በፍርሃቱ የሚናገ ሕጻናት መዋሸት ልማዳቸው ስለሆነ እሷም ፤ «ዳቦ ቤቱ ዝግ ነው ማዳም» አሰኝት ።

«ዝግ ነ——ው ? ዝግ ሆኖ ካገኘሽው አትቆረቁሪውም ኖሯል ታዳያ!»
«ቆርቁሬዋለሁ ማዳም ።»

@OLDBOOKSPDF

ዝና.....»

«አልከፍት አሉኝ ።»

«እውነት ይሁን ውሸት ነገ ጠዋት እናያለን ። ውሸት ከሆነም ታግ ሂያታለሽ!» ስትል ዛተችባትና ፈለማንኛውም አስራ አምስቱን ሱ ወዲህ በይው» አሰቻት ።

ከዜት እጇን ከሽርጧ ኪስ ውስጥ ከትታ ብትደባብስ ሳንቲሙ ከዚያ የለም ። የባሰውን ተበረክረክች ።

«በይኩ ፈጠን በይ..... አልሰማሽኝም እንዴ!»

የሽርጧን ኪስ ገልብጣ አወጣችው ። በውስጡ ምንም የለም ። የት አባቴ ገባ!? ከዜት የምትለውን አጥታ ሐውልት ሆና ቀረች ።

«አስራ አምስቱን ሱ ጣልሽው እንዴ አንቺ?» ስትል ተጎነዳዳችው ባት ማዳም ቴናርዲዬ ። እጇን ዘርግታም ከጤስ ማውጫው አጠገብ ግርግዳው ላይ ተሰቅሎ የነበረውን አለኑጋ አወረደችው ።

«ይማሩኝ እመቤቴ..... ይማሩኝ..... ከአሁን ወዲያ አይለምደኝም» ስትል ተማጸነቻት ከዜት ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ቢጫ ኮት የለበሰው መንገደኛ የሰደርያውን ኪስ ሲደባብስ ነበር ። የተቀሩት መንገደኞች ጥን ሃሳባቸውን በመጠጣቸው ላይ አለዚያም በሚጫወቱበት ካርታ ላይ ጥለው ነበር ።

ከዜት ግርፋቱን ፈርታ ተሸማቅቃ ቆመች ። ማዳም ቴናርዲዬም አለን ጋውን ወደላይ ሰታነሳው ፤ «ይቅርታ..... ይቅርታ.....» አለ መንገደኛው ፤ «ከልጅቷ ሽርጥ ኪስ አንዳች ነገር ሲወድቅ የሰማሁ መስሎኛል ። ምናል ባት የጠፋው ገንዘብ ይሆናል» ብሎ ወለሉ ላይ ይደባብስ ገባ ። ጐንበስ ካለበት ቀና ብሎም ፤ «ይኸው.....!» አለ ።

ሰውዬው አገኘሁት ያለው ገንዘብ ሀያ ሱ እንጂ አስራ አምስት ሱ አልነበረም ። ሆኖም ማዳም ቴናርዲዬ አልተከራከረችውም ። ገንዘቡን ተቀብላ ኪሷ ውስጥ ጨመረችው ። በሚያስፈራ ዓይኖቿም ከዜትን እያ የች «በይ እሺ ሁለተኛ እንዳይሰምድሽ!» ስትል አስጠነቀቀቻት ።

ቀጠል አርጋም ዓይኗን ወደሰውዬው መልሳ ፤ «ራት ይዘጋጅልህ?» ስትል ጠየቀችው ። ሰውዬው በሃሳብ ተውጦ ስለነበረ መልስ አልሰጣትም ።

«ምን ዓይነቱ ነውጥ» ስትል አሰበች ማዳም ቴናርዲዬ ፤ «መናጢ ድሃ መሆን አለበት ። እራት የሚበላበት ገንዘብ እንኳ የለውም ። ለመ ሆኑ የመኝታውን ሂሳብ ችሎ ይከፍለኝ ይሆን?»

@OLDBOOKSPDF

ይሀንኑ ስታስብ ሳለች በሩ ተከፈተና ኤፖኒንና አዜልማ ገቡ ። ሁለቱም ወላፀ ናቸው ። ሁለቱም ሕይወት ያንጸባርቃሉ ። ሁለቱም የሚያምር ልብስ ለብሰዋል ። ሺክ ብለዋል ።

ማዳም ቱናርዲዬ «አቦ! እናንተ ናችሁ!» ብሳ በየተራ ወደራሷ አስጠግታ ጸጉራቸውን ታስተካክልላቸው ፣ የጸጉር ማሠርያ ጥብጣባቸውን ታስርላቸው ገባች ። ከዚያም በጓላ ልጆቹ ወደ አሳት ማንደጃው ጠጋ ብለው ቁሙ አሉ ። በየተራም አሻንጉሊታቸውን ታሳያለው ይጫወቱ ጀመር ። ኮዜት በቅናት ዓይን ታያቸዋለች ። እነሱ ግን ከቁም ነገር ስለማይቆጥሯት ዓይናቸውን ወደሷ አላዞሩም ።

ከዜት በልጆቹ ጨዋታ ተዘናግታ ሥራዋን ገታ አድርጋ ወደእነሱ መመልከቷን ከወዲያ ወዲህ ስትል የነበረችው ማዳም ቱናርዲዬ ልብ ሳትል አልቀረችም ። «ያላየሁሽ መስሎሻል!» አለቻት ፤ «ሥራ የሚሠራው እንዲህ ነወይ ሥራሽን ትተሽ ሌላ ነገር የምትመለከቺ ከሆነ....! » ስትል አሰፈራራቻት ።

ቢጫ ኮት የሰቢስው መጎንደኛ በዚህ ጊዜ ራቱን ወደ ማዳም ቱናርዲዬ አዙሮ ፤ «ምናለበት ብትጫወት....? እሷም እኮ ልጅ ነች» አሳት ሲፈራ ሲቸር ።

ማዳም ቱናርዲዬ ያልጠበቀችው ሆነባት ። ሰውዬው አለባበሱ ያማረና ከበርቴ ቢሆን ኖሮ አስከዚህም ባሳስጨረሻት ነበር ። አሁን ግን ቅር ሳትሰኝ አልቀረችም ። «መሥራት አለባት» አሰኛው ፤ «ካልሠራች እሷን የምትለብቢት ምክንያት የለኝም ።»

«ለመሆኑ ምንድነው የምትጠልፈው?» ሲል ጠየቃት ።

«የምትጠልፈውማ የእግር ሹራብ ነው..... ለልጆቹ የሚሆን የእግር ሹራብ ።»

«እና..... ሹራቦቹን ጠልፋ ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅባታል?»

«ጸጉኛ ሆና አስቸገረች እንጂ ቢያንስ በሦስት ወይም በአራት ቀናት ሠርታ መጨረስ ትተግባት!»

ሰውዬው ጥያቄውን በመቀጠል ፤ «ሠርታ ስትጨርስላቸው ሹራቦቹ ምን ያህል ያወጣሉ?» ሲል ጠየቃት ።

ማዳም ቱናርዲዬ በንቀት ዓይን አየቸውና «ቢያንስ ሠላሳ ሱ» ስትል መለሰችለት ።

«አምስት ፍራንክ ብሰጥሽ ሹራቦቹን ትሸጪልኛለሽ?»

ሲያዳምጣቸው የነበረ አንድ ጋሪ ነጂ ይሀንን ሲሰማ በጣም ተግርሞ ፤ «አምስት ፍራንክ! ጉድ ነው!» አለ ።

የማዳም ቱናርዲዬም ባል ከጠፋው በላይ ስለሆነበት ቱሲ ብሎ ፤ «እምነ ጌታዬ..... ሹራቦቹን ከፈለጓቸው አምስት ፍራንክ ከፍለው ይው

@OLDBOOKSPDF

ሰዲቸው ። እንግዶቻችን የጠየቁንን ከሚሚላት ወደኋላ አንልም» አለው ።

«ዱቤ ከሆነ ግን አይቻልም ። እጅ በእጅ መከፈል አለበት» አለች ማዲም ቱናርዲዬ ።

«አሁኑኑ ልክፈልሽ» ብሎ ሰውዬው አምስት ፍራንክ አውጥቶ ጠረ ጴዛው ላይ አኖረላትና ሳይኑን ወደ ከዚያ አዙሮ ፤ «በይ ልጂ.... ሒደሽ ተጫወቺ ። ሹራቦቹን ጠልፈሽ ባትጨርሺአቸውም ገዝቻቸዋለሁ» አላት ።

ማዳም ቱናርዲዬ በሆዲ አርር አሰኙ ። ከዚት በበኩልዋ ለማመን አል ቻሉችም ። ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ ። «እውነት እንድጫወት ፈቅደውልኛል እመቤቴን» ስትል ጠየቀቻት ማዳም ቱናርዲዬን ።

«ሒጂና ተጫወቺ» አሰቻት ማዳም ቱናርዲዬ ፤ ሆዲ አርር ቢልም ።

ከዚት እመቤቷን አመሰገነቻት ። በእሱ አሲን ታመሰግን እንጂ በሆዲ ግን ያመሰገኑት ሰውዬውን ነበር ።

የማዳም ቱናርዲዬ ባል ሃሳቡን ወደ መጠዉ አዞረ ። አሲም ወደሱ ጠጋ ብሳ በጆሮው «ይህ ሰው ግን ሊሆን ይችላል?» ስትል ጠየቀችው ።

«ደባደቦ ሉበሰው የሚሔዱ ሚሲዮኦሮች እንዳሉ አታውቂም!» አሳትና ሃሳቡን አሁንም ወደመጠዉ አዙረው ።

አፖኒንና አዜልማ አሻንጉሊታቸውን ወለሉ ላይ ትተውት የቤቱን ድመት ይዘው ይጫወቱ ጀመር ። ከዚት በበኩሏዋ የቆርቆሮ ሰሰታን ክሳጥን አውጥታ አሻንጉሊት ይመስል ምናምን እያለባበሰች ትጫወት ነባች ። ሕጻናት አሻንጉሊት የሚወዱት ያለምክንያት አይደለም ። አዋቂ ምጭን ለመምሰል ነው ። አዋቂም ሕጻናትን እንደሚንከባከቡ ሁሉ ሕጻ ናትም አሻንጉሊታቸውን መንከባከብ ይወዳሉ.... ማለበስ ፣ ማስጌጥ ማስተማር ፣ መጣሠጽ ፣ እሽሩሩ ማለት.....

አሻንጉሊት የሌላቸው ሕጻናት ልጅ እንደሌላቸው ወላጆች ናቸው ። ሁለቱም ሠዎችም አይደሉቱም ።

የቱናርዲዬ ልጆችና ከዚት በየፈናቸው ሲጫወቱ ሳሉ ማዳም ቱና ርዲዬ ወደ ሰውዬው ጠጋ ብላ ፤ «ሰሙ ወይ.....» አለችው ። እስካሁን ድረስ በአንተታ ስታናግረው ቆይታ አሁን ግን በአንቺታ ስታናግረው ኮና ብሎ ኢየት ። «ሰሙ ወይ..... ልጅቷ እንድትጫወት ፈቅጂላታለሁ ። እርስዎም ለልጅቷ ቸር መሆንም ደግ ነው ። ሆኖም ልጅቷ ምንም የሌላት ቁርጩ ደሃ ስለሆነች መሥራት አለባት» አለችው ።

«ያንቺ ልጅ አይደለችማ»

«ኧረ በማትኩት.....! የኔ ል———ጅ! እሷ ለራሷ ሰማኝ.....! እኛኮ ለችሮታ ብሰን ነው ያስጠጋናት ። ደሞም ገለጂጅ ነች ። የራስ ቅሷ ትልቅ ቢሆንም በውስጡ ወሣ ካለበት በስተቀር ባዶ ነው ። የተቻለንን እናደርግ

@OLDBOOKSPDF

ሳታሰን ። ብቻ..... እኛም ብንሆን ሀብታሞች አይደለንም ። ሰወላጅ እናቷ ይበጸቤ ጽፈንላት ነበር ። ነገር ግን ይኸው በስድስት ወር ውስጥ መልስ አንኳ አላገኘንም ። እናቷ በሕይወት ባትኖር ነው» አሰኙው ።

«እሠ» አሰና ሰውዬው ከሃሳብ ውስጥ ገባ ።
«እናቷ የማትረባ ሴት ነበረች ። ለጅቷን እዚህ ጥላት ሔደች ።»

ሰውዬውና ሚዳም ቱናርዲዬ ስለእናቷ ሲያወሩ ከዜት ጆሮዋን አቅንታ ሰማቻቸው ። «እናቱ ሞታለች..... እናቱ ሞታለች..... እናቴ ሞታለች» እያለችም ድምጿን አጥፍታ ታንጎራጉር ጀመር ።

በሦቱት ወስጥ ያሉት ጠጪዎች ወደመስክር ተቃረቡ ። በስካር አፍ የሚነገር ዓይነትም የብልግና ዘፈን ይዘራገቱ ጀመር ። ማዳም ቱናርዲዬ በዘፈኑና በሳቁ ሰመሳተፍ ወደነሱ ሔዳ ትጎሽ ቆየችና ተመልሳ ወደሰውዬው መጣች ። «ሰእራት ምን እንዲዘጋጅልዎት ይፈልጋሉ ጨሲ» ስትል ጠየቀችው ።

«ዳቦና አይብ» አላት ።

ማዳም ቱናርዲዬም ግራ ተጋብታ ፤ ጌይሀ ሰውዬ በእርግጥም መናጢ ድሃ መሆን አለበት» ስትል አሰበች ።

ጠጪዎቹ በብልግና ዘፈናቸው ገፉበት ። ከዜትም እጉርጉሮዋን ፋጠሰችና በድንገት ቆም አለች ። የቱናርዲዬ ሊጆች ወሰዱ ሳይ የወረወሩት አሻንጉሊት ከዓይኖቿ ሥር ድቅን አለባት ። አንገቷን አዙራ ብትታዝ ሚዳም ቱናርዲዬ ከባሏ ጋር በሹክሹክታ እያወራች ግንዙብ ትጭጥራለች ። ኤፖኒንና አዜልማ መሳ መንፈሳቸውን ድመቲቱ ላይ ጥለዋል ። ጠጪዎቹ እየበሱና እየጠጡ ይዘፍናሉ ። ከዜትን የሚመለከት ማንም አልነበረም ። ዝማ ብላ ወደ አሻንጉሊቱ ሔዳ አነሳችው ። ተመልሳም ወደጠረጴዛው ሥር ንብታ ጸጥ ብላ ተቀመጠች ። አሻንጉሊቱን ጥላዋ ሥር አደረገችው ። በእውነተኛ አሻንጉሊት የመጫወት ፅድል ስላጋጣማትም እጅግ በጣም ደስ አላት ። ብልዲዋን ተሸክሞላት ከመጣው ሰውዬ በስተቀር ማንም ልብ አላሳትም ። እሱ ግን ምግቡን እየቀማመስ ሲያስተውላት ነበር ።

ከዜት ለሩብ ሰዓት ያህል በአሻንጉሊቱ ስትጫወት ቆየች ። የአሻንጉሊቱ እማር ከጥላዋ ውጭ ሆኖ በሚነደው እሳት ብርሃን ይታይ እንደነበረና የአዜልማም ዓይን በአሻንጉሊቱ ላይ ማረፉን ልብ አላለችም ። አዜልማም ወደ እህቷ ዞር ብላ ፤ ወአንቺዬ..... አይ.....ነ» አለቻት ።

ከዜት ደፍራ የአነሱን አሻንጉሊት አንስታ በመጫወቷ በጣም ተጣ ረመ ። ዓይናቸውን ለማመን አቅታቸው ።

ኤፖኒን ድመቲቷን እንደታቀፈች ወደ እናቷ ሔዳ የእናቷን ቀሚስ ትስበው ገባች ።

@OLDBOOKSPDF

«እኮ ተይኛ! ምንድነው የፈለግሺውን» አለቻት አናቷ ።
«እማዬ..... ተመልከቺ.....!» አለቻት ወደከዚት እያመለከተች ።

ከዚት ከደስታዋ የተነሳ አንዳችም ነገር ሳታስተውል ቀረች ። መላ መንፈሰዋ በአሻንጉሊቱ ላይ ነበር ።

ማዳም ቱናርዲዬ ተደፈርክ በማለት የቁጣ ሲቃ ያዛት ። «ከዚት!» ስትል በኃይል ጮኸችባት ።

ከዚት ምድር የተንቀጠቀጠ መሰላት ።
«ከዚት!» ስትል እንደገና ተንገዳገዳችባት ማዳም ቱናርዲዬ ።

ከዚት አሻንጉሊቱን ቀስ ብላ መሰለ ላይ አስቀምጣው ቃለቅስ ጀመር ፣ ሆድ ብሷት ።
«ምን ሆናለች?» ሲል ጠየቀ መንገደኛው ፣ ሳይኑን ወደ ማዳም ቱናርዲዬ አዞር ።
«እያዩም እንዴ?» አለችው ማዳም ቱናርዲዬ መያአሻንጉሊቱ ነያ መለከተች ።
«ታዲያ ምን አለበት?» አሳት ።
«ምን አለበ——ት! የልጆቼን አሻንጉሊት.....!»
«ይህ ሁሉ ጩኸት ለዚህ ጥሯል! ብትጫወትበት ምን አለበት?»
«የልጆቼን አሻንጉሊት ደፍራ በእድፍ ነጂ ትንካውን»

ከዚት የባለውን ታነባ ጀመር ።
«እኮ ዝም በይ....! ይበቃሻል.....!» አለቻት ማዳም ቱናርዲዬ ።

መንገደኛው ተነስቶ ወደ በሩ አመራ ። በሩንም ከፍቶ ወጣ ።
ስውዬው ሲወጣ ማዳም ቱናርዲዬ ወደ ከዚት ሐዲያ አንድ ሁለት አርግጫ አቀመሰቻት ። ከዜት ጩኸቷን ለቀቀችው ።

ወጥቶ ሐዲዱ የነበረው መንገደኛ ተነስ ሙሉ የሠራሩ ልጆች ዓይናቸውን የጣሉበት ፣ ትልቁንና አስደናቂውን አሻንጉሊት ተሸክሞ ገባ ።
«ይሽውልሽ..... ሳንቺ ነው የገዛሁልሽ ከዜት» አሳት ።

ከዜት ተደናግራ ስውዬውን ወደላይ አንጋጣ ተመለከተችው ። ከዚያም በኋላ ሽምትት ብላ ጠረጴዛው ሥር ገብታ ተደበቀች ።

ማዳም ቱናርዲዬ ፣ ኤፖሂንና አዜልማ ሐውልት ሆነው ቀሩ ። ጠጪ ዎቹም በጣም ተገረሙ ። ክፍሉ ውስጥ ፍጹም ጸጥታ ሆነ ።

«ይህ ሰው ማን ነው? መናጢ ድሃ ወይንስ ሚሊየነር? ወይንስ ቀጣፊ ሌባ?» ስትል አሰበች ማዳም ቱናርዲዬ ።

@OLDBOOKSPDF

ሙሴ ቱናርዲዬም አሻንጉሊቱንና ስውዬውን አፈራርቆ አየቸው ። ወደ ሚስቱም ሔድ ብሎ በጆሮዋ ፤ «ያህ አሻንጉሊት ቢያንስ ቢያንስ ሠላሳ ፍራንክ ያወጣል ። ሰውዬውን በአክብሮት መያዝ አለብን» አላት ።

ማዳም ቱናርዲዬም በሰውዬው ላይ የነበራትን አስተያየት ቸይራ ፥ ድምጽዋን አስለልሳ ፥ ፊቷን ወደ ከዚት አዙራ ፤ «አሻንጉሊቱን አትቀበዩም እንዴ?» አለቻት ።

ከዚት ስትፈራ ስትቸር ከጠረጴዛው ሥር ወጣች ።

«አቅህ እንግዳችን አሻንጉሊት ገዝተውልሻል..... ሐዲሽ ተቀበያ ቸው» አለቻት ድምጹዋን ይበልጥ አሰልሳና አሳምራ ።

ከዚት ፍራሟቷን ለማሽነፍ ባትጥልም ያጉነ ውበና ትልት አሻንጉሊት እንደገና አየት አደረገችው ። የአንባዋ በይ አሁንም አፌቷ ላይ ይታ ያል ። ነገር ግን ፊቷ በደስታ ይጥቢረበራል ። የፈረንሳይ ንግሥት ሆነሻል ተብላ ቢነገራትም ኖሮ ፊቷ ከዚያ ይበልጥ በደስታ ባልተጥበረበረ ነበር!

«አሻንጉሊቱን እንድተበል እውነት ፈትደውልኛል አመቤቱ?»
«ፈቅጂልሻለሁ እንሺ! ሐዲሽ ተቀበዪ ።»
«እውነት..... እውነት ፈትደውልኛል?»

መንገደኛው ይሆንን ሲስማ አንባ ተናነቀው ። እንዲያለቅስም በመ ፍራት መናገሩን ትቶ ከዚት አሻንጉሊቱን እንድትቀበለው በምልክት ነገራት ።

በመጨረሻም አሻንጉሊቱን ተቀበለችውና «ካትሪን» ብዬ እጠራ ታለሁ አለቸው ። ለአሻንጉሊቷ «ካትሪን» የሚል የሴት ስም የሰጠቸት ሴት አሻንጉሊት በመሆኗ ነው ።

አሻንጉሊቷ ስስ ወረቅ ለብሳለች ። መቀነት ተደርጎላታል ። ከሷ ቡትቶ ልብሶች ጋር ሊያስተያዩዋት የአሻንጉሊቷ ልብስ በጣም ያማረና የጸዳ ነበር ።

«ካትሪንን ወንበር ላይ ላስቀምጣት እችላለሁ አመቤቱ?» ስትል ማዳም ቱናርዲዬን ጠየቀቻት ።

«አምን..... ትቸያለሽ ።»

ኤፖኒንና አዜልማ ከዚትን ሲያስቀኗት እንዳልኖሩ ሁሉ አሁን በተራቸው ቀኑባት ። ከዚት አሻንጉሊቷን በወንበሩ ላይ አስቀምጣት እሷ ራሷ ወለሉ ላይ ቁጭ አለች ። ዝም ብላም አሻንጉሊቷን በአድናቆት ታስተውላት ገባች ።

@OLDBOOKSPDF

«ተጫወቺባት» አላት ሰውዬው ።

«እየተጫወትኩባት ነኝ!» አለችው ።

ማዳም ቴናርዲዬ ሰውዬውን እጅግ አድርጋ ጠላችው ። ጥሏቻዋን ለማሳየት ግን አልደፈረችም ። ልጅቷን ወደመኝታዋው ላክቻቸውና ፊቷን ወደ ሰውዬው አዙራ ፤ «ከዚትም ብዙ ሥራ ስትሠራ ስለዋለች ብትተኛ ይበጃታል» አለችው ። ከዚት ካትሪንን ተሸክማ ወደመኝታዋ አመራች ።

ማዳም ቴናርዲዬ የሆነው ሁሉ አልዋጥ ስላላት ወደ ባሏ ሐሳ ንዴ ቷን ትገልጽለት ገባች ። «ይህ የሸጀ ሰውዬ ከቢታችን መጥቶ ለምን ያስቀጣናል? ልጅቷ ብትጫወት ምን አለበት ማለቱ.....! ደርሶም ይህንን ያህል ገንዘብ አውጥቶ አሻንጉሊት መግዛቱ.....! አሷ ራሷ ብትሸጥ የዚህ ግማሽ ፥ ከዚያም ያነሰ ዋጋ አታወጣም.....! አሷ ብሎ ደም ... ገልቱ!» አለችው ።

«አንቺን ምን አስጨነቀሽ!» አላት ባሏ ፤ «የፈለገውን ያድርግ ።»

መንገደኛው ከርኑን ጠረጴዛው ላይ ተክሎ ከሃሳብ ባሕር ውስጥ ገብቶ ቀረ ። የተቀሩት እንግዶች ዘፈናቸውን ጋብ አደረጉት ። በሩቅ ሆነው ሰውዬውንም ሲያስተውሱት ነበሩ ።

ሴሊቱ እየተግባደደ ሔደ ። የመኝታ ሴሊት ቅዳሴ በሚፈጸምበት ሰዓት የቤተክርስቲያን ደውሎች መደወላቸውን አቆሙ ። ጠጪዎቹ ተነ ስተው ወጡ ። መጠጥ ቤቱም ተዘጋ ። አሳቱ ነደዱ ነድዱ ኮሰመ ። መንገደኛው ግን በቀድሞ ቦታውና በቀድሞው ሁኔታ ቆየ ። ከዚት ከሔ ደች ጀምሮ አንድም ቃል አልተነፈሰም ።

ማዳም ቴናርዲዬ ሰውዬው ብቻውን እንዳይሆን በማሰት እዚያው ቆየች ። «እዚሁ ቁጭ ብሎ ሊያድር ነው እንዴ?» ስትል አሰበች ። እስከ ሴሊቱ ስምንት ሰዓት ከጠበቀችው በኋላ አንቅልፍ ስላሸነፋት ወደ ባሏ ጠጋ ብላ ፤ «ወደመኝታዬ መሔዴ ነው ። አንተ እንደፈለግህ አድርግ» ብላ ተሰናበተችው ። ሙሴ ቴናርዲዬ በአንድ ጥግ ተቀምጠ ፈኩርዬ ፍራ ንሴ» የተባለውን ጋዜጣ ያነብብ ነበር ።

በዚህ ሁኔታ አንድ ሰዓት አለፈ ። ሙሴ ቴናርዲዬ ጋዜጣውን ከመ ጀመሪያው ገጽ እስከመጨረሻው ገጽ ድረስ ሦስት ጊዜ ወጣው ። መንገ ደኛው ግን ከቦታው ንቅንቅ አላለም ።

ሙሴ ቴናርዲዬ ይቁነጠነጥ ጀመር ። ይሳሰላል ። ምራቁን እንትፍ ይላል ። ይናፈጣል ። ወንበሩን ያንጫጫል ። መንገደኛው ግን ንቅንቅ..... ፍንክች አልል አለ ።«ይህ ሰውዬ ምን ሆኗል? እንቅልፍ ወስዶት ይሆን እንዴ?» ሲል አሰበ ሙሴ ቴናርዲዬ ። በመጨረሻም ቆቡን አውልቆ ፥

@OLDBOOKSPDF

ወደመንገደኛው ሔደ ብሎ ፣ በአክብሮት ፣ «ለማረፍ አይፈልጉም እንዴ ጌታዬ? » ሲል ጠየቀው ።

«አዎ..... ባርፍ አልጠላም» አለውና መንገደኛው ፣ «በረቱ ወዴት ነው ያለው?» ሲል ጠየቀው ።

ሙሴ ቱናርዲዬ ፈገግ አለና «ይከተሉኝ ጌታዬ.....» አለው አሁንም በአክብሮት ።

ተከታትሰው ወጡ ። ሙሴ ቱናርዲዬ ሻማ ይዟል ። መንገደኛው ጥቅል ዕቃውንና በትሩን ይዟል ። ሙሴ ቱናርዲዬ መንገዱን እየመራ ወደ አንደኛው ሮቅ ወጡ ። በጣም ከተጌጠና ምቹ ከሆነ ክፍል ውስጥ ገቡ ።

«ምንድነው ይሄ?» አለው መንገደኛው ።

«በእውነቱ ከሆነ የቀድሞ ጓደላ ቤታችን ነው..... የኔና የባለቤቱ ። አሁን ግን ባለቤቱና ጓሬ በሴላ ክፍል ውስጥ አንኖራለን ። በዚህኛው ክፍል ውስጥ በዓመት ምስት ወይም አራት ሴሊት ብናድርበት ነው» አለው ፣ ክፍሉን ለማዋደድ ያህል ።

«እኔክ በረት ውስጥ ባድር ይበቃኝ ነበር ።»

ቱናርዲዬ ያልሰማው መስሎ ሁለት ሻማ አበራለት ። በእሳት ማን ደጃው ቦታም እሳት ሲንቀለቀል ነበር ።

መንገደኛው ከእሳት ማንደጃው ሳይ ፡ነበረ መደርደርያ ሻሽ የመሰሰ ነገር ታየውና «ይህ ምንድነው?» ሲል ጠየቀው ሙሴ ቱናርዲዬን ።

«የመ·ሸራ ቹዋል ነው..... በሠርጋችን ዕለት ባለቤቴ አድርጋው የነበረ ቹዋል ።»

«እውነት ይህች ጭራቅ ሴት ልጃገረድ የነበረችበት ዘመን ነበር ማለት ነው?» ሲል አሰበ መንገደኛው ።

ሙሴ ቱናርዲዬ ዋሸው ። በክብ መስታወት ውስጥ የነበረው ቹዋል ሞቴል ቤቱን በኮንቴራት ሲከራየው እዚያው ያገኘው እንጂ የሚስቱ የሠርግ ቹዋል አልነበረም ።

ሙሴ ቱናርዲዬ ይሁንን ውሸ ፣ ከተናገረ በኋላ መንደገኛውን ደህና እደር እንኳ ሳይለው እዚያው ትዶት ወደ ራሱ መኛታ ቤት ኑመራ ።

«ነገ ከዚችን እንደማባርራት አውቀሃል?» ስትል ጠየቀችው ባለ ቤቱ ፣ ከመኛታ ቤታቸው እንደገባ ።

@OLDBOOKSPDF

«ምን ማለትሽ ነውን» አላትና ሻማውን አጠፋው ። መልስ አልሰጠችውም ። እሱም መልስ ስጪኝ ብሎ አልወተወታትም ። ዝም ብለው ተኙ ።

መንገደኛው በበኩሉ ዱላውንና ጥቅል ዕቃውን በአንድ ጥግ አኖራቸውና ሰፋ ላይ ቁጭ ብሎ ያስብ ጀመር ። ተጥሎም ጫማውን አውልቆ ፣ ከሁለቱ ሻማዎች አንዱን አጥፍቶ ፣ አንዱን ይዞ በሩን ከፍቶ ወጣ ፣ አንዳች ነገር እንደሚፈልግ ሰው ። መተላለፊያ በረንዳውን አልፎ ከመ ውጫና መውረጃ ደረጃ ደረሰ ። የልጅ ትንፋሽ የሚመስል ድምጽ ተሰ ማው ። ድምጹ ወደመጣበት ሐድ ቢል ከዜት ነች ። ወለሉ ላይ በግር ገዝገዝ ላይ ተኝታለች ። ነፍሷን አታውቅም ። የተቦጫጨቀ ብርድ ልብስ በላይዋ ላይ አለ ። የቀን ልብሷን አላወለቀችም ፣ እንዳይበርዳት ። ትልቁን አሻንጉሊት ታቅፋዋለች ። የአሻንጉሊቱ ዓይን በጭለማው ውስጥ ያበ ራል ። በጉዝጓዙ አጠገብ የእንጨት ጫማዋ ይታያል ፣ አንደኛው እግር ብቻ ።

መንገደኛው ከዜትን ጠጋ ብሎ ካስተዋላት በኋላ እሷ ከተኛችበ ት ቦታ አልፍ ብሎ የተከፈተ በር መኖሩን ተገነዘበ ። በሩ ሰፋ ካለ ክፍል ውስጥ ያስገባል ። መንገደኛው ሐድ ብሎ ከዚያ ገባ ። ሁለት ነጫጭ አል ጋዎች አሉበት..... የኤፖኒንና የአዜልማ አልጋዎች ። ከእነሱ አልጋ ቀጥሎ የሕጻን ልጅ አልጋ አለበት..... ምሽቱን ሙሉ ሲያለቅስ የነበረው ሕጻን ልጅ አልጋ ። ሦስቱም አልጋቸው ላይ እንቅልፍ ወስዷቸዋል ።

«የእነቴናርዲዬ መኝታ ቤት ከሕጻናቱ ክፍል ተጥሎ ያለው መሆን አለበት ።» ሲል አሰበ መንገደኛው ። ከዚያም በኋላ ወደኋላው መሰስ ለማለት ሲያስብ ዓይኖቹ አንድ ነገር ላይ አረፉ ። እኩል ያልሆኑ ሁለት ጫማዎች በእሳት ማንደጃው ቦታ ታዩት ። በልዶት ቦዓል ዋዜማ ሕጻናት ልጆች ጫማቸውን በእሳት ማንደጁው ቦታ ማስቀመጥ የአውሮጳ ባህል ነው ። ይኸውም የገና ስጦታ ለመቀበል ነው ። ኤፖኒንና አዜልማ ጫማ ቸውን ከዚያ ያኖሩት ይህንን ባህል በማስታወስ ነበር ።

መንገደኛው ጐንበስ ብሎ በጫማዎቹ ውስጥ ያለውን ስጦታ ተመ ለከተ ። በእያንዳንዳቸው ውስጥ የነ ስር ሱ ሽርፍራፊ ነበረበት ። ልጆቹ በሚነቁበት ወቅት ስጦታው ከሰማይ የወረደላቸው እንደሚመስላቸው የታወቀ ቢሆንም ሳንቲሞቹን ከዚያ ያስቀመጠቻቸው እናታቸው ነች ።

ከሁለቱ ጫማዎች ለጥቆ ጨለምለም ካለው ሥፍራ ሌላ ጫማ ታየው..... በአመድና በጭቃ የተለወሰ የእንጨት ጫማ..... የከዜት ጫማ..... ሁለተኛው እግር ። ከዜትም ብትሆን የገና ስጦታ ከሰማይ ይወርድልኛል ብላ እንደነሱው ጫማዋን ከዚያ አኑራዋለች ። በሷ ጫማ ውስጥ ግን አን ዳችም ሳንቲም አልነበረበትም ። መንገደኛው የሰደርያውን ኪስ ደባብሶ የሚያብረቀርቅ የወርቅ ፍራንክ ጨመረበት ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ በኋላ ፊቱን አዙሮ ፥ ቀስ ብሎ እየተራመደ ወጥቶ ወደ ክፍሉ አመራ ።

— 9 —

በማግሥቱ ጠዋት ገና ጎሕ ሳይቀድ ሙሴ ቲናርዲዬ ከመኝታው ተነስቶ ፥ ወደ መጠጥ ቤቱ ሒዶ ፥ በጠራ ሻማ አጠገብ ተቀምጦ ፥ ብዕር በእጁ ይዞ የመንገደኛውን ሂሳብ ያሰላ ጀመር ። ባለቤቱ በአጠገቡ ጎንበስ ብላ በዓይኗ ትከተለዋለች ። ከውጭ የሚንኳኳ ድምጽ ይሰማል ። ክዚት መውጫ መውረጃውን ደረጃ ስትጠርግ ነበረች ።

ሙሴ ቲናርዲዬ ሰፋ ብ ሰዓት ያህል ሲጽፍ ሲደልዝ ሲያሰላ የነ በረው ሂሳብ እነሆ ፥

በክፍል ቁጥር አንድ ከተኛው መንገደኛ የሚፈለግ ሂሳብ ፥

እራት	፡—	3 ፍራንክ
መኝታ	፡—	10 ፍራንክ
ሻማ	፡—	5 ፍራንክ
እሳት	፡—	4 ፍራንክ
አገልግሎት	፡—	1 ፍራንክ

ጠቅላላ ድምር 23 ፍራንክ

«ሀያ ሦስት ፍራንክ!» ሰቶስ ጮኸች ሚስቱ ቲናርዲዬ ። እንዲያ የጮኸችው መንገደኛው በመክፈሉ አይስማማ ይሆናል በማሰት እንጂ ደስ ሳይላት ቀርቶ አይደለም ።

«ምነው ተግረምሽ?» አላት ባሏ ።

«አይ እንዲያው..... ሂሳቡ እንኳ ትክክል ነው» አለችው ፥ መን ገደኛው ለክፍሉ የገዛላትን አሻንጉሊት እያስታወሰች ፥ «ብቻ..... ምናልባት ሂሳቡ በዝድል..... አልከፍልም እንዳይል ፈርቼ ነው ።»

«ይከጥላል እንጂ!..... ወዶ ነው!»

ሙሴ ቲናርዲዬ ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ ያስብ ጀመር ። ሚስ ቱም ጠረጴዛውን ታዘገጃጅ ጀመር ። «በነገራችን ላይ..... ልጅቷን ዛሬ እንደማባርራት ነግሬህ የለም?» አለችው ።

ሙሴ ቲናርዲዬ መልስ አልሰጣትም ። አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ ዕዳ ስለነበረበት ስለዚህ ሲያሰላስል ነበር ። የትምባሆ ፣ማጤሻውን በአፉ

@OLDBOOKSPDF

ይህ አሳት አያያዘና ፤ «ሂሳቡን ለሰውዬው አንቺ ተሰጠዋለሽ» ብሏት ከቤቱ ወጣ አለ ።

ልክ በዚህ ጊዜ መንገደኛው ከአደረበት ክፍል ወደ መጠጥ ቤቱ መጣ ። የሰውዬውን መምጣት ሲያይ ሙሴ ቴናርዲዬ ተመልሶ ገብቶ ከመ ንገዱ በስተጀርባ ቆመ ።

«በጠዋት ተነስም አይደል?» አለችው ማዳም ቴናርድዬ ። ሰውዬው ጥቅሉንና ዱላውን ይዞ ስለነበረ ፤ «አሁን ሊሔዱ አሰቡ እንዴ?» ስትል ጠየቀችው ።

«አምን ማዳም..... ለመሔድ ተነስቻለሁ» አላት ።
«በሞንፈርመይ የሚያቆይዎት ጉዳይ የለም ማለት ነዋ!»
«ምንም ጉዳይ የለኝም ። በዚህ ለማለፍ እንጂ እዚህ ለመቆየት አይ ደለም አመጣጤ» አላትና ፤ «ለመሆኑ ሂሳቡ ስንት ነው?» ሲል ጠየቃት ።

ማዳም ቴናርዲዬ አጣጥሩ የያዘችውን ወረቀት ሰጠችው ። መንገደ ኛው በአእምሮው ሃሳብ ይዞ ስለነበረ ወረቀቱን ዘርግቶ ቢያየውም የሂሳቡን ከፍተኛነት ልብ ሳይለው ቀረ ።
«ለመሆኑ ሥራ እንዴት ነው ማዳም?» ሲል ጠየቃት ።

«እስከዚህም አይደል! በአካባቢያችን ከበርቴዎች የሉም ። ሁሉም ድሃ ስለሆነ ገበያ የለንም ። አልፎ አልፎ የእርስዎ ዓይነት ቸር እንግዶች ባያጋጥሙን ኖሮ ኑሮውን ባልቻልነውም ነበር ። ወጪአችን ብዙ ነው ። ያቺ ልጅ እንኳ ስንት የምታስወጣን መሰልዎት!»

«የቷ ነች እሷ?»
«ያች የሚያውቋት ልጅ ነቻ! ኮዜት ።»
«አሃ! እሷን ማለትሽ ነው?»

«አዩ ጌታዬ.....! እኛ ምጽዋት ለመቀበል እንሻም ። ምጽዋት ለመ ስጠትም አንችልም ። ገቢአችን በጣም ትንሽ ነው ። ወጪአችን ግን ሰፍር ቁጥር የለውም ። የጉግድ ፈታድ ግብር..... የግምሩክ ቀረጥ..... የበርና የመስኮት ታክስ..... ምኑም ምኑም እያራቆተን ነው ። በዚያ ላይ የወሰድና ቸው ልጆች እያሉን የሰው ልጅ ለማሳደግ ፍላጎት የለንም ።»

«ልጅቷን የሚወስድልሽ ሰው ብታገኚ ትለቂያታለሽ?»
«ማንን? ኮዜትን?»
«አዎን ።»
«በማን ዕድሉ! ከፈለጉ ይውሰዷት ። አሁኑኑ!»
«ጥሩ.....! በጣም ጥሩ.....! »
«እውነት ከሷ ይገላግሉኛል?»
«እመስዳታለሁ ብዬሻለሁ ።»

@OLDBOOKSPDF

«አዘዙት ?»
«አዘዙት! ልጅቷን ጥሪያት ።»
«ከዚችስ» ሰትል ተጣራች ማዳም ቱናርዲዩ ።

«እስከዚያው ጊዜ ድረስ ሂሳቡን ልክፈልሽ..... ስንት ነው ዕመሦኑ?» ብሎ ወረቀቱን በጥሞና ተመለከተው ። «ሀያ ምስት ፍራንክ!» አለ በመገረም ።

«ነው ጌታዬ..... ሀያ ምስት ፍራንክ ።»

በዚህ ጊዜ መሲ ቱናርዲዩ ጠጋ አለና «ሂሳቡ ሀያ ሦስት ፍራንክ እይደለም ። ሀያ ስድስት ሱ ነው» አለ ።

«ም————ን ? ሀያ ስድስት ሱን» ሰትል ጠየቀችው ማዳም ቱናር ዲዩ ፣ ቱደናግጣ ።

«አዎን ሀያ ሱ ዕመኚ ። እና ስድስት ሱ ለእራት ። ስለልጅቷ መሐዲ አለመሐዲ ግን ከመንገድኛው ጋር በቆይታ ዕመነጋገር ስለም ፈልግ እንደ ጊዜ ገለል ብትይልኝ.....» አላት ።

ባሏ አንዳች ብልጣብልጥ ሃሳብ ይዞ መቅረቡን በመገመት ሴት ታል ሳትተነፍስ ገለል አለችላቸው ።

ሁሉቱ ሰዎች ብቻቸውን ሲቀሩ መሲ ቱናርዲዩ ፈረቃ እንዲል መሃ ንደኛውን ጋበዘው ። እሱ ግን አልተቀመጠም ። «ልጅቷን በጣም አመጸ ታለሁ ጌታዬ ። ለነግሮት የፈለግሁት ደኅነኑ ነው» አለው ።

«የትኛዋን ልጅ?»

«ከዚችን ነዋ! ለረጅም ጊዜ ከኛ ጋር ስለኖረች አፈቅራታለሁ ። ከዚህ ብትሔድ በጣም ትጥቀሳኛለች ። ጥና ሕጻን ልጅ ሆናኮ ነው ከኦኛ ጋር መኖር የጀመረችው ። በእርግጥ ገንዘብ ታስወጣናለች ። ለምሳሌ አንድ ስሞን ታምማ አራት መዳ ፍራንክ አስወጥታናለች ። ብቻ ወጪ ወጣ ቻልነው ። አዩ..... ልጅቷ አባትም ሆነ እናት የላትም ። የሙት ልጅ ነች ። እኛ ነን ያሳደግናት ። በዚህ ምክንያት እመጻታለሁ ። ባለቤቴም ብት ሆን ትቆጣታለች እንጂ በልባ ታፈቅራታለች ። ሁለታችንም እንደልጃ ችን ነው የምንቆጥራት ። ስለዚህ ከኛ ተለይታ እንድትሔድ ፈቃዴ አይ ደለም ።»

መንገደኛው ዝም ብሎ ተመለከተው ። መሲ ቱናርዲዩም ንግግሩን ቀጠለ ፤ «አዩ..... ሌላም ነገር አለ ። ኮዜት ከአርስዎ ጋር እንድትሔድ ብፈ ቅድ እንኳ አርስዎ ማን እንደሆኑ አላወቅም ። የት እንደሚኖሩም አላው ቅም ። ልጅቷ እንድትሔድ ብፈቅድ እንኳ ወዴት እንደምትሔድ ማወቅ ይገባኛል ። ሔዳ የውሃ ሽታ ሆና እንድትቀር ፈቃዴ አይደለም ። አስፈላጊ

@OLDBOOKSPDF

በሆነ ጊዜ ሐጂ እንድጠይቃት ይገባኛል ። አሷም እንደማሰብላት ማወቅ ይገባታል ። ስለዚህ ሊወስዷት ከፈለጉ መጀመሪያ የመታወቂያ ወረቀትዎን እንዲያሳዩኝ ያሻል ።»

«ከፓሪስ እሰከዚህ ድረስ ያለውን ሀያ አራት ኪሎሜትር መንገድ ለመጓዝ የመታወቅያ ወረቀት አያሻውም ሙሴ ቱናርዲዬ ። ከዚትን የምወስዳት ከሆነ እንዲሁ እወስዳታለሁ እንጂ ሴሳ ግዳጅ ውስጥ አልገባም ። ስሜንም ሆነ አድራሻዬን ልሰዋህ ፈቃዴ አይደለም ። ከወሰድኳት በኋላ የት እንዳለች እንድታውቅም አልፈልግም ። ሁለተኛ እናንተን እን ድታይ አልሻም ። እና እንድወስዳት ትፈልጋለህ ወይንስ አትፈልግም? ቁርጡን ንገረኝ ።»

መንገደኛው ቆራጥ ሰው መሆኑን ሙሴ ቱናርዲዬ ተረዳ ። ትናንትና ማታም ቢሆን ሌሎቹ እንግዶች ሲጠጡና የባለጌ ዘፈን ሲዘፍኑ ይህንን መንገደኛ በጥሞና ሲያስተውለው ነበር ። «ይህ ሰው ለከዚት ምኗ ይሆን ? ለምንድነው የተጨነቀላት? እሱስ ራሱ ገንዘብ የተረፈው ሆኖ ሳለ ለምን አልባሌ ልብስ ለበሰ?» እያለ ሲያስብ ነው ያደረው ።

አሁንም ፤ «ይህ ሰውዬ የከዚት አባት ይሆን ወይ ወይንስ አያቷ? ከሆነ ለምን ነኝ ብሎ አይናገርም? ብቻ..... የደበቀው ነገር ያለ ይመስላል ። ማንነቱን ለማሳወቅ ያልፈለገው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም» ሲል አሰበ ።

በመጨረሻም ምን እንደሚፈልግ ሳያወላውል ቁርጥ አድርጎ ሊነ ግረው ወሰነ ።

«አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ ዕዳ ያሰብኝ ሰው ነኝ ጌታዬ» አለው ።

መንገደኛው ኪሱን ደባብሶ ፣ ቦርሳውን አውጥቶ ገንዘቡን ከፊቱ አኖረለትና ፤ « ሒድና ከዚትን አምጣት» አለው ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከዜት የተለምዶ የጠዋት ሥራዋን ስታከናውን ነበረች ። ልቧም በአዲስ ተስፋ ተመልቶ ነቦር ። ያን ቀን ማልዳ ስትነሳ በእንጨት ጫማዋ ውስጥ የሀያ ፍራንክ ዋጋ ያለው የገና ስጦታ በማግኘቷ በጣም ተደስታ ነበር ። የወርቁን ፍራንክ ጫማዋ ውስጥ ማን እንዳስቀመ ጠላት ሳትጠራጠር አልቀረችም ። የጽዳት ሥራ በምታከናውንበት ጊዜም ፍራንኩን አሁንም አሁንም እያወጣች ትመለከተው ነበር ።

በዚሁ ሁኔታ እያለች ተጠርታ ወዴ መጠጥ ቤቱ ወረደች ። መንገደኛው ይዘት የመጣውን ጥቅል ፈትቶ ከሱፍ የተሠራ ልብስ ፣ ሽርጥ ፣ ጥብቆ ፣ መሐረብ ፣ የውስጥ ልብስ ፣ የግር ሹራብ ፣ እና ጫማ አውጥቶ ሰጣት ። እነዚህ ሁሉ ጥቁር ነበሩ..... የሐዘን ልብሶች ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚት ለባበሳ ስትጨርስ «በይ እንሒድ ልጂ» አላትና መንገድ ጀመሩ ። ጊዜው ሙሉ በሙሉ ነጭቷል ። የሞንፈርመይ ነዋሪዎች የቤታቸውን ቦር ሲከፍቱ ይታያሉ ። ሰውዬውን የሚያውቀው ሰው የለም ። ከዚትም በትዮዎችዋን ወዲያ ወርውራ አዲስ ልብስ ለብሳ ፣ አሻንጉሊት ታቅፋ ትራመድ ስለነበረ ማንም ለይቶ አላወቃትም ።

ከዚት የት እንደምትሔድ አታውቅም ። የሰውዬውንም ማንነት አታውቅም ። በዚያን ሰዓት ያወቀችው ነገር ቢኖር ከአኑቲናርዲዬ መላላንሷን ብቻ ነበር ።

ሚዳም ቲናርዲዬ በባሷ ላይ ከጥቂት የሆነ ግምት ስላላት መንገድ ኛውን በቆይታ ላነጋግረው እወዳለሁ ባላት ጊዜ ደህና አድርጎ ያልበዋል ብላ ተስፋ አድርጋ ነበር ። መንገደኛውና ከዚት ከሐዱ ከአራብ ሰዓት በኋላ የተቀበለውን አንድ ቪ አምስት መቶ ፍራንክ ሲያሳያት ግን እጅግም አልተደሰተችም ። «ለዚሁ ብቻ ኖሯል አንዴ!» ስትል አንጎጠጠችው ። ባሏን ስታንገላጥጥ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር ።

መሉ ቲናርዲዬም ቁጭት አደረበት ። «ይበልጥ መጠየቅ ነበረብኝ» ሲል አሰበና መንገደኛውን ሲከታተለው ወሰነ ። «ባርኔጣዬን ስጪኝ» አላትና ግንዘቡን በኪሱ አድርጎ ወዲያውኑ ተነስቶ ወጣ ።

ወደቀኙ ታጥፎ ባልሆነ መንገድ ይጓዝ ጀመር ። ትንሽ ከተጓዘ በኋላ ግን መንገደኛውና ከዚት በወዴት አቅጣጫ እንደሔዱ ጠይቆ ተረዳና ከትክክለኛው መንገድ ገባ ። ሰዎች እንደነገሩት መንገደኛውና ከዚት በሊቭሪ አቅጣጫ ይጓዙ ነበር ።

ፈጠን ፈጠን ብሎ እየተራመደ ራሱ ሰራሱ ይናገር ጀመር ፣ «የማል ረባ ሰው ነኝ!» አለ ፣ «ሰውዬው ቢጫና መኖኛ ልብስ ቢሰጠኝም ሀብታም መሆኑ አያጠራጥርም ። በመጀመሪያ ከወሰል ላይ ያነሳው መስሎ ሀያ ሱ ሰጠ ። ቀጥሎም አምስት ፍራንክ ። ከዚያም በኋላ ከፍተኛ ወጪ አድርጎ አሻንጉሊቱን ገዛ ። በመጨረሻም አንድ ቪ አምስት መቶ ፍራንክ ሰጠኝ ። ይህንን ሁሉ ሲሰጥ ለአንድ አፍታ አንኳ አላመነታም ። የተረፈው ከበርቴ መሆን አለበት ። እኔም አሰራ አምስት ቪ ፍራንክ ብጠይቀው ኖሮ ላያመነታ በከፈልኝ ነበር» አለና ፤ «ያመጣችው ልብስ በቅድሚያ የተዘጋጁ ናቸው ። ይገርማልኮ ነገሩ አ ሥዳች ምስጢር ያዘለ መሆን አለበት» ሲል አሰበ ።

ከሞንፈርመይ አልፎ ወደ ሊቭሪ የሚጠመዘዘው መንገድ ወጣ ያለ ስለሆ ነ አስከሩት ቦታ ድረስ አሻግሮ ለማየት ይቻላል ፣ ዓይንን የሚያማ

@OLDBOOKSPDF

ደው ነገር የሰምና ። ሙሲ ቱናርዲዬ ከዚያ ሲደርስ መንገደኛውና ከዜት በሩቅም ቢሆን ይታዩኛል ብሎ ቦሳመነ ዓይኑ እስከቻለለት ድረስ አሻ ግሮ ተመለከተ ። ነገር ግን አልታዩትም ። በአካባቢው ሰው አግኝየ ወሬ ቢጠይቅ መንገደኛውና ልጅቷ በጋኜ አቅጣጫ በኩራ ወጻለው ጫካ መግ ባታቸውን ሰማ ። ያንን አቅጣጫ ይዞ መንገዱን ቀጠሶ ፤ እየኮቸከስ ።

እንዲህ ሲጣደፍ ነለ አንድ ነገር ትዝ አለውና ግንባሩን በእጁ መትቶ «ጠበንጀዩን ይገር መምጣት ነበረብኝ!» አለ ፥ በጸጸት ።

የጥድፊያ ክትትሉን ቀጠለ ። ከአንድ ሥፍራ ሲደርስ የወንድ ባር ኔጣ የአሻንጉሊት ራስ ታዩት ። መንገደኛው ከዜትን ለማሳረፍ ሰሰፈለግ ፀለቱም ቁጭ ብለው ነበር ።

ቱናርዲዬ ከመንገደኛው አጠገብ ሲደርስ «ይቅርታ ያድርጉልኝ ጌታዬ..... አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክም እሰሠ..... ይቀበሉኝ» አለው ።

መንገደኛው እንግቱን አቅንዩ ተመለከተው ። «ምን ማለትህ ነው» ሲል ጠየቀው ።

«ማለቴማ..... ከዜትን መልሼ ለመስዳት ነኝ ።»

ከዜት ይህንን ሰትሰማ ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ ወደ መንገደኛው ጠጋ አለች ።

«ከዜትን መልሼ ለመሰዳት ነኜ.....?»

«አዎን ጌታዬ ። በጉዳዩ ብዙ አብቢበታለው ። እንዲያውም እሷን ለአርስዎ ሰመስጠት ሙበት የለኝም ። ይህች ልጅ የኔ ልጅ አይደለችም ። አናቷ በአደራ መልክ ነው ሰኔ የሰጠችኝ ። ስለዚህ ሰእናቷ መልሼ ማሰረ ክብ ይኖርብኛሊ ። እሷ ብትሞት እንኳ ሰእግሴ ይሰጥልኝ ብላ በፊርማዋ ሳረጋገጠችለት ሰው ብቻ ነው የምሰጣት ። ሰሌላ ሰው ለሰጣት አይቻለ ዥም ። ጉዳዩ ግልጽ ይመስለኛል» አለው ።

መንገደኛው የኪስ ደብተሩን ሰዞ አመጣ ። የኪስ ደብተሩ ፣ገንዘብ ታጭቋል ። ቱናርዲዬ ይህንን ሲያይ ክፉኛ ጮመጠ ። ከአሁን አሁን አፍሶ ሊሰጠኝ ነው ብሎ አሰፈሰፈ ።

መንገደኛው በአካባቢው ሰው መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ዙር ያውን ታኝ ። ቦታው አርጭ ብሏል ። በሽለቆውም ሆነ በደኑ ውስጥ አን ድም ሰው አይታይም ። ይህንኑ ካረጋገጠ በኋላ መንገደኛው የኪስ ደብተሩን ከፈተው ። ገንዘብ ለማውጣት ሳይሆን አንድ ቁራጭ ወረቀት ስቦ ለማውጣት ነበር ። ወረቀቱን ዘርግቶ ለቱናርዲዬ አሳየውና ፤ ፊንካ አንብበው አለው ።

@OLDBOOKSPDF

ቴናርዲዩ ወረቀቱን ተቀብሎ ያነብበው ጀመር ፤

ኤም ሱር ኤም ፣ መጋቢት 25 ቀን 1823 ዓ. ም.

ሙሴ ቴናርዲዩ ፤—

ከዚትን ለዚህ ሰውዬ አስረክባት ።
ያወጣሃቸው ጥቃትን መጪዎች ይከፈሉሃል ።
ከማክበር ሰላምታ ጋር

ፋንቲን ።

«ፌርማውን እውቀኸው የለም?» ሲል ጠየቀው መግቢያው ።

«ይህ ፊርማ የሷን ፊርማ አስመስሎ ለሳ ሰው የፈረመው ሊሆን ይችላል ። ብቻ ግድ የለም ። ለማንቸውም ከዚትን ስመረከብ የመጡት እርስዎ ከሆኑ በቅድሚያ ያወጣኋቸውን ወጪዎች እንዲከፍሉኝ እሻለሁ ። ያወጣኋቸውም ወጪዎች ጥቃቅን አይደሉም ።

መንገደኛው ተነስቶ ቁም ሽላቱ እጅጉ ላይ የነበረውን አፀፉ አራ ነፈና «ሙሴ ቴናርዲዩ....» አለው ፤ ወለፈው ጥር ወር የከዚት እናት ስእጉ መክፈል ያለባት ዕዳ አንድ መቶ ሀያ ፍራንክ ብቻ ነው ብላ አሰበ ነበር ። አጉሉ ግን ባለፈው የካቲት ወር እምስት መቶ ፍራንክ አስቢሽ ስትል መልእክት ላክሀባት ። በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ሦስት መቶ ፍራንክ ተከፈለሀ ። በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ደግሞ ምስት መቶ ፍራንክ ተላክሎሀ ። ይህ ከሆነ ዘጠኝ ወራት አልፈዋል ፡ በተስማማችሁበት መሠረት ለእያንዳንዱ ወር አሰራ አምስት ፍራንክ ፤ ዘጠኝላለው ለዘ ጠኝ ወራት አንድ መቶ ሠላሳ አምስት ፍራንክ የሚከፈልህ ሂሳብ አለ ። ነገር ግን ቀደም ብለህ አንድ መቶ ፍራንክ ስርጅ ስለወሰድህ የሚቀርህ ሂሳብ ሠላሳ አምስት ፍራንክ ብቻ ነበር ። እኔ ከዚትህ ስመጣ የከፈልኩህ ግንዘብ አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ ነው ተግባባንስ» ሲል ጠየቀው ።

ቴናርዲዩ በዘረታ ወጥመድ የተያዘ ቀነሳ ሆነ ። «ይህ ጄያብሎስ ማነው» ሲልም አሰበና «ይስመኝ....» አለው ፣ «ምስት ሺ ፍራንክ ባል ከፈልኝ በስተቀር ከዚትን መለሺ መመለሷ ነው ።»

መንገደኛው ቴናርዲዩን ጭለ ብሎት የከዚትን እጅ በግራ እጁ ሲ ቀም አደርጎ ፣ በኮኛ እጁም ዴላውን ይዘ «ነይ ልጄ..... እንሒድ» አለትና መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

ቴናርዲዩ የዓለሙን ትልትነትና የኢትባቢውን ረጭ ማሰት ፡ የመ ንገደኛውን ትክሻ ስፈንትና የእጁንም ግዙፍነት ሳያስተውል አልቀረም ። የራሱ ክንዶችና እጆቹም የመነ ጠሉ መሆናቸውንም ሳይገነዘብ አልቀረም ። «ጠበንጃዬን ሳልይዝ ልምን መጣሁ....! ክብት ነኝ!» ሲል ተቆጨ ።

@OLDBOOKSPDF

መንገደኛውና ከዚች ጫካው ውስጥ ገብተው ጠፉበት ። እሱም ፀየት እንደሚሔዱ ማወቅ አለብኝ» በማለት አውንም ክትትሉን ቀጠለ ። ከሱ ርቀው ቢሔዱም ዱካቸውን አልሳተም ። መንገደኛው አውንም አውንም ዞር ብሎ ያይ ስለነበረ ከአንድ ሥፍራ ሲደርስ ዞር ብሎ ቢመለከት ቴና ርዲዬ አውንም ተከትሎታል ። በቱጣ ዓይን አየው ። አመለካከቱም ቴና ርዲዬን በጣም ስላስፈራው ከዚያ በላይ ላይከታተለው ወስኖ ፊቱን ወደ መጣበት አቅጣጫ አዞረ ።

— 11 —

መንገደኛው ግን ቫልጣ እንጂ ሴላ ሰው አልነበረም ። ነገር ግን ግን ቫልጣ ባህር ውስጥ ከጣባ በኋላ እንዴት አድርጎ ለመውጣት ቻለ?

ከባህሩ ውስጥ በገባበት ወቅት አግሩ ከሠንሠለቱ ነጻ ስለነበረ ውስጥ ለውስጥ እየዋኘ ሔዶ ከአንድ ከቆሙ መርከብ አጠገብ ደረሰ ። ከመርከቡ ጋር የተያያዘም አንድ ጀልባ ነበር ። እስኪመሽ ድረስ በዚህ ጀልባ ውስጥ ተደብቆ ዋሰና ሴሊት ቂሶማ ሲወርድ እንደገና አየዋኘ ወደ ጠረፍ ተመለሰ ። ከዚያም በኋላ በቂ ግንዘብ ስለነበረው ልብስ ገዛ ። ከወህኒ ቤት ያመለጠ አስረኞች ግንዘብ ከጭለው ልብስ የሚቀይሩበት ቤት በአካባቢው ስለነበረ ከዚያ ሔዶ ልብሱን ከተየረ በኋላ እንዳይያዝ አሳቻ አሳቻውን መንገድ እየመረጠ ይዝዝ ጀመር ። በፕራዶ ፡ በግራ - ቪላር ፡ በኤን ፡ በፒሬኔ በፔርጎ አድርጎ ፓሪስ ከተማ ደረሰ ።

ፓሪስ እንደደረሰ የመጀመሪያ ተግባሩ ከሰባት አስከስምንት ዓመት ዕድሜ ላሳት ልጅ የሠዘን ልብስ መግዛትና ሲራሱም ማረፊያ ቤት ፈልጎ ማግኘት ሆነ ። ይህንን ካደረገ በኋላ ወደሞንፈርመይ አቀና ።

በሌሎች ሰዎች ዓይን ግን ግን ቫልጣ እንደሞተ ተቆጥሮ ነበር ። ሞቷል የሚል ወሬ በጋዜጣ ላይ ሰፍሮ በማየቱም በጣም ደስ ብሎት ፣ እፎይታም ተሰምቶት ነበር ።

ከዚችን ከእነቴናርዲዬ እጅ ፈልቅቆ ያወጣት ዕለት ተግዝ ተግዝ እንደገና ፓሪስ ገባ ። በሴሊት ነው ፓሪስ የገባው ። ከዚያም በኋላ ጋሪ ተከራይቶ ተጓዘና ከኡበሴርቫቷር ሲደርስ ከጋሪው ወርዶ ፣ ሂሳቡን ከፍሎ ከዚችን ይዞ ወደ ቡልቫር ዶ ሎጊታል አመራ ።

ያን ቀን ለከዚት ልዩ የሆነ ቀን ነበር ። ነገር ግን አንዳንዴ በአግር አን ዳንዴም በሕዝብ ማመላለሻ ሲጓዙ ስለዋሉ በጣም ደክማት ። መራመድ እንዳቃታት ሲገነዘብ ግን ቫልጣ እንስቶ በጀርባው አዘላት ። እሷም አሻንጉሊቷን ሳትለቅ ራሷን ከጣን ቫልጣ ትከሻ ላይ አሳርፋ ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰዳት ።

— 252 —

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ሦስት

የጎርቦ ማረፊያ ቤት

— 1 —

በፓሪስ ከተማ ከልል ውስጥ በጣም ጥቂት ሰዎች የሚኖሩበት ፣ ገጠር ነው አንዳይባል የከተማ ቤቶችና መንገዶች ያሉበት ፣ ከተማም ነው አንዳይባል ቦርቧራና ማርማ መንገድ የቤዘበት ፣ ምንነቱ በውል ያልተረጋገጠ ነባር ግን የፓሪስ ከተማ አካል የሆነ ፣ ማርሼ— ኦ—ቭ ተብሎ የሚጠራ አሮጌ ሥፍራ አለ ። ይህ ሥፍራ በማምሻ አጥር የተከለለ ሆኖ ከአጥሩ ውጭ ውሃንትነቱ የወጣ አንድ አሮጌ ሕንጻ አለበት.....ባለአንድ ፎቅ ሕንጻ ። በፋሳይ ከውጭ ቁጥር 50 ፣ ከውስጥ ቁጥር 52 የሚል ጽሑፍ ሠፍሮበታል ።

ወደ ውስጥ ገብ ሲሉ የሚታየው ደረጃ ወዲ ሮቁ ያመራል ። ሮቁ ረጅም የሆነ መተላለፊያ በረንዳ ያለው ሆኖ በግራና በቀኙ በርካታ ክፍ ሰሞች አሉት..... ጨለምለም ያሉና ደቦ የሚይሉ ክፍሎች ። ግድግዳውቹ ላይ ቀለሷች ቸረፈሯች ይታዩበቸዋል ። ቤቱ በግምት የመቶ ዓመት ዕድሜ ሳይኖረው አይቀርም ። የጎርቦ ቤት ፣ ወይም የጎርቦ መጠለያ ተብሎ ይጠራል ። ይኸውም ቀደም ባሉ ጊዜ የቁጥር 50—52 ቤት ባለቤት ጎርቦ የተባለ አቃቤ ሕግ ስለነበረ ነው ።

ከዚህ ቤት ፊት ለፊት ሦስት አራተኛው የደረቀና «ኤልም» ተብሎ የሚጠራ ዛፍ ፣ ከዛፉም ኋልፍ ብሎ አንድ ሩባሪክ አለበት ።

በአጠቃላይ ሙልቱ ይህ አካባቢ ደስ የማይልና ቀዶም ብሎም የነ ጥስ ግድያና ሌላ ሌላም ወንጅል ሲፈጸምበት የኖረ ሥፍራ ነበር ። ቀን ቀን ቦታው ያስጠላል ። ሌሊት ሌሊት ደሞ በጣም ያስፈራል ። በመንገዱም ለማኞች ይበዙበታል ።

ዣን ቫልጊ ወደ ሞንፈርመይ ከመሔዱ አስቀድሞ ለማረፊያነት መረጠው ቦታ ይህ ስዕነበረ ከሥፍራው ሲደርስ ቆም አለ ። ከዚያም በኋላ

@OLDBOOKSPDF

ከጥብቆው ኪሲ ቁልፍ አመጣ ፣ በሩን ከፍቶ ገብቶ በሩን መልሶ ዘጋቸ ፣ ደረጃውን ሸቅብ ተያይዘው ፣ ክዚጉን አንዳዘሳት ። ያረሽሙን ጨርስ ከወጣ በኋላ ሌላ ቁልፍ ከኪሱ አመጣዮ ሌላ በር ከፍቶ ገባ ። የነባበት ከፍል በመጠኑም ቢሆን ሰፋ ያለ ነው ። መሰሉ ላይ ፍራሽ ተዋለበታል ። አንድ ጠረጴዛ ፣ በርከት ያሉ ወንበሮችና የእሳት ማንደጃም ቦታ አልው። ከነፍሱ መዲያኖው ሳጣ ታጣራ አለጋ ተዘርግቶበታል ። ግን ቫልገ ወደ ዚያ ሐኖ ክዚጉን አለጋው ላይ አስተኛት ፣ ከእንቅልፍ ሳይተሰቅሰቅ ። ገንበስ ብሎም ተመለከተታት ፣ በርህራሄ ሚይን ። ተጥሎም እጂን ሳማት ። ክዚጉ ያለችበትን ሲታወቅ አንዴው አደረች ።

በማግሥቱ ንጉት ላይ የጠዋት ጨረር ዘልቆ በነበበት መቅት እንኳ ክዚጉ ከእንቅልፍ አልነቃችም ። በኋላ ግን ከዛድ ዕታ የተሜን ጋራ በመጣድ ሲያልፍ መራቡን ሲያስታንተው የክዚጉም አለጋ ስለተነታ ኑሎ ሲጅት በእንቅልፍ ለባ ፣ « አምን ማዘም ..... መጣው ..... ! ውጣው ..... ! » ስትል ጮኸች ።

ያሠንንም ብላ ከመኝታዋ ተንሳች ። ሚሄዋጂ መሉ ፡ሙ ሉ አለተከ ፈተም ። እጂን ወደ ግድግዳው በጭም ፣ ሠሙዮሪጊያው የሻ አለ ! ወይ አምላኬ ! » አለች ።

ሚሄዋጅን መቱ በመሉ ኪስነድታችው ግን ከለማ በእፍሱ መስጥ አዕ ። ራቱ በፈጣታ ተመለጅል ።

ክዚጉ ልሸገላሪጅን ከአለጋዋ ሥር ሆኖ አየቻት ። ሲሆም አደ ርጋ አንሰጅተና ግን ቫልገን በጥያቱ ታማክራው ገባች ፣

« የት ነው ያለው ..... ?
« ታሪክ ሰፊ ክተማ ነው ..... ?
« ማዘም ቱናርዲዬ ሩቅ ነው ያለት ..... ?

« እሰቸው ሠንድ ተመልሼ እሔዳለው ..... ? »
ወዘተረፈ ።

ከፍሉ ደስ ተሰኝል ቢሆንም ክዚጉ በዚያ ክፍል ውስጥ የነጸነት ሽሚት ተሰማት ።

« ክፍሉን ልዋረጠጥ » ስትል ጠየቀችው ግን ቫልገን ።

« ተጫወቺ ..... ! » አላት ፈገግ ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

ግን ሻልጎ ሰሀያ አምስት ዓመታት በብቸኝነት የኖረ ሰው እንደ መሆኑ የሚያፈቅረው አልነበረውም ። አባት ሆኖ አያውቅም ። ባል ሆኖ አያውቅም ። ፍቅረኛ ሆኖ አያውቅም ። ልቡ ድንግል ነበር ለማለት ይቻላል ። አሀዜንና ልጅቱን ለማግኘት ያላደረገው ጥረት ባይኖርም ሊያገኛቸው ሳይችል ቀረ ። ደብዛቸው ጠፋብን ። ከዘመድና ከወዳጅ ተነጥሎ ፍጹም ብቸኛ ሆኖ ነበር የኖረው ።

አሁን ግን ኮዜትን አግኝቶ ፣ ከአኑቲናርዲዬ እጅ መንጥቆ ለመውሰድ ድና ከራሱ ጋር ለማኖር በመሻት ልቡ እየምትለት ሌዶ ። ሰብአዊ ስሜት ፣ ሰብአዊ ፍቅር ይሰማው ጀመር..... የሕይወት ሁሬድሶ!

ከዜትም በበኩሏ የመላጅ ፍቅር ምን እንደሆነ ሳታውቅ የኖረች ልጅ ነች ። አናቷን አታስታውሳትም ። ለማጥቀር ብትሻም የምታፈቅረው አልነበራትም ። አሁን ግን የምታፈቅረው አገኘች ። ግን ሻልጎ ርኅራሄና ፍቅር ስላሳየት እሷም አፈቀረችው ። የሕይወ ኮ ጎሕ ቀደደለት ። የሌጅነት ብሩህ ተስፋ ታያት ።

በሁለቱ መሐከል ያለው የሰጅሜ መራራት አንዳችም እንክን አልፈጠረባቸውም ። ሁለቱም ከመጻበኛ ሕይወት የተፈናቀሉ ፣ በየበኩላቸው የተሰቃዩ በመሆናቸው ደህ ሁኔታቸው አቀራረባቸው ፣ አንድ አደረጋቸው ፣ አዋሐዳቸው ። እሳ በደመ ነፍስ አባት ሉሻ ነበር ። እሱም በደመ ነፍስ ልጅ ይሻ ነበር ። ሁለቱም የሚሹትን አገኙ ። መልካም አጋጣሚ! መልካም ዕድል!

በሳርቦ ቤት ያረፉበት ክፍል ተስማሚያቸው ። ካለአንድ መስኮት ሰላልነበረው ሌሎቻቸውን የሚበክል አንዳችም ነገር አልነበረም ። ፎቱ በርካታ ክፍሎች ቢኖሩትም ለሻገ ሻልጎ ምቾፀ የምታዘጋጅለቱ ፣ ከፍሉን የምታጸዳለት አሮጊት ሴትዮ ከምትኖርበት ክፍል በስተቀር ሌሎቹ ክፍሎች በተከራይ ያልተያዙ ባዶ ክፍሎች ነበሩ ።

በልደት በዓል ዋዜማ ክፍሉን ያከራየችው ይህችው አሮጊት ነበረች ። እሱም በቂ ግንዘብ ያለው ሰው መሆኑንና ከሴት ልጁ ጋር ክፍል ተከራይቶ ለመኖር እንደሚሻ ገልጸሊት ነበር ። የስድስት ወር ሂሳብም በቅድሚያ ከፍሏታል ።

ግን ሻልጎና ኮዜት በሳርቦ ቤት ደስ ብሏቸው ይኖሩ ጀመር ። አንዳንድ ጊዜም ግን ሻልጎ እጁን ሰቀም አድርጎ ያስመጥል ። ከዜት ሶድ ብድብ እንጂ ለእንዲህ ዓይነቱ ደግነትና ሰብአዊ ፍቅር ያልተላመጀች በመ ሆኗ ድንግርግር ይላታል ።

@OLDBOOKSPDF

ግን ሻልጣ ጊዜ ሳያጠፋ ወዲያውኑ ፌዶል ያስቆጥራትም ጀመር ። እሱ ራሱ ፈዶል የቆጠረው በእስር ቤት ውስጥ በመሆኑ አውን ለዚህ በትፍ እሷን በማስተማሩ ደስታ ይሰማዋል ። ስለእናቷም ያወራላታል ። እንድትጸል ይላትም ይመክራታል ።

— 3 —

ከዚት አባባ ብላ ትጠራው ጀመር ። ይህም ተጨማሪ ደስታ ሰጠው ።

ግን ሻልጣ ማታ ማታ እንጂ ቀን ቀን ወደ ጦጭ አይወጣም ። መሸቶ ለሳይን ሲያዝ ግን ከዚትን አስከትሎ ፣ አለዚያም ብቻውን ሰው እርግም ከማይታይበት አካባቢ ሐዲ ይንሸራሸራል ። አማረ መንገዱን ከቢተክር ሁቲያ ጥበቅ ይጸልያል ።

የተመጠነ ኑሮ ነው የሚኖረው ሦን ሻልጣ ። አሮጊቷ ከጠዋያ ሽምታ ፣ ከዚት አብስላ የምታቀርብለትን ይበላል ። አለባበሱ ፈጽሞ አልተለወጠም ። አውንም ቢጫ ኮቱን ይለብሳል ፣ ጥቁር ቁምጣውን ይታጠቃል ፣ አሮጌ ባርኔጣውን ይደፋል ። በመንገድ የሚያዩት ሰምት እንደለማኝ ይቆጥሩታል ። አዝነውለት ምጽዋት የሚሰጡት አንኳ አሉ ። ምጽዋት ሲሰጡት ዝም ብሎ እጅ ነስቶ ይቀበላቸዋል ። አሱም በበኩሉ አሳዛኝ ለማ ኛት ሲያጋጥሙት ምጽዋት ይሰጣቸዋል ። ይሁን እንጂ ምጽዋት በሚለ ጥበት ጊዜ ሰው እንዲያየው ስለማይፈልግ ሦር ሦር ብሎ ተመልክቶ ሰው አለመኖሩን ሲያረጋግጥ ብቻ ምጽዋቱን ሰጥቶ ቶሎ ብሎ ያልፋል ።

ግን ሻልጣ ሠወር ብሎ መኖሩን ያስተዋለችው ቤት አከራይዋ አሮ ጊት ስለግን ሻልጣ ማንነት የማወቅ ፍላጎት ስላደረባት እሱ ሳያውቅ ችከታተለው ጀመር ። ስለማንነቱ ከዚትን የጠየቀቻት ጊዜም ነበር ። ነገር ግን ከዚት ራሷ ምንም የምታውቀው ስለሌላት ነሷ እንዳችም ፍንጭ ለማግኘት ሳትችል ቀረች ።

አንድ ቀን ጠዋት ግን ሻልጣ ከአልተያዙት ክፍሎች ወደ አንዱ ጐራ ሲል አሮጊቷ ልብ አሰኙው ። አንደደመት ቀስ ብሳም ተከተለችው ። በሩን መለስ ሲያደርገው አሷ ከመጭ ሆና በበሩ ስንጣቂ ወደ ውስጥ ትያ ኖች ትሰልለው ገባች ።

ግን ሻልጣ ራቱን ወዴ በሩ መልሶ ቆሟል ። ኪሱን ይበብሶ የዕቃ መያዣ አንስተኛ ሳጥን ፣ መቀስ ፣ እና ክር ስቦ አወጣ ። ከዚያም በኋላ የኮቱን ገበር ቀድዶ የአንድ ሺ ፍራንክ ዋጋ ያለው የወረቀት ገንዘብ መገመ አወጣ ። አሮጊቷ በመላ ሕይወቷ ከዓሰት ወይም ከሦስት ጊዜ በላይ ይኸን ያህል ዋጋ ያለው የወረቀት ገንዘብ አይታ አታውቅ ስለነበረ ደንግጣ ቸበኛ ።

@OLDBOOKSPDF

ከሦንሽ ጊዜ በኋላ ጐን ቫልገር ከንበረበት ክፍል ወጥቶ ወደ አሮጊቷ ቋያና የወረቀት ገንዘቡን እንድትመነዝርለት ጠየቃት ።« የሩብ ዓመት ገቢዬ ነው..... ከትናንት ወዲያ ነው የተቀበልኩት» አላት ።

ተጠራጠረችው ። ቁከየት አመጣውና ግታ ግታ ከአሰራ ሁለት ሰዓት በፊት አይወጣም ። ከአሰራ ሁለት ሰዓት በኋላ የመንግሥት ባንኮች ዝግ ናቸው ። እና ከወደዬት አመጣውን» ስትል አሰበች ።

ገንዘቡን ግን ዘረዘረችለት ። ወሬውንም ስለነካችው የአካባቢው ነዋሪዎች ስለዚህ ገንዘብ አጋንነው ያወሩ ጀመር ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ጐን ቫልገር በመሪላለፊያው በረንዳ ላይ ሆኖ በመጋዝ እንጨት ሲቆርጥ ነበር ። ሸሚዝ ብቻ ለብሷል ። ኮዜት ከእሱ ጋር ነች ። አሮጊቷ በክፍሉ ውስጥ ብቻዋን ቀርታ ዕቃ ስትደረድር ሳሰች የጐን ቫልገርን ኮት ግድግዳው ላይ በምስማር ሰንጠልጥሎ አየች ። ከፊት አድርጋ ገበሩን ብታየው ተቀድዶ የነበረው ክፍል ተሰፍቷል ። ይበልጥ ዳበስ አድርጋ ብታየው በርካታ መረቀቶች በመሰለው እንዳለበት ተረዳች ። ቁየመቶ የሙዩ ፍራንክ ዋጋ ያላቸው የገንዘብ መረቀቶች መሆን አለባቸው» ስትል አሰበች ።

ከዚህም በሰተቀር የኮቱ ኪሶች በተለያዩ ዕቃዎች ዳታሩ መሆኗ ቸውን አስተዋለች ። ጠርሬ..... ክር..... መቀስ..... ትልቅ የማስታወሻ ደብ ቀር..... መቁረጫ ስለት..... እና በርካታ ሰው ሠራሽ ጎጉሮች ። ላልታሰበ ጊዜ የሚያገለግሉ ዕቃዎች»

አሰከ ከረምቱ መጨረሻ ድረስ የጐን ቫልገ ሕይወት ሳይለወጥ በዚሁ ሁኔታ ቆየ ።

— 4 —

ከቅዱስ ሚጸር ቤተክርስቲያን አቅራቢያ የማይጠፉና ጐን ቫልገም ሁልጊዜ ምጽዋት የሚሰጠው አንድ ለማኝ አለ ። ጐን ቫልገ ቤሳ ቢስነቱ ሳይወረውርለት ምን ጊዜም አያልፍም ። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ቆም ብሎ ያነጋግረዋል ። ይህ ለማኝ በቀድሞ ጊዜ የቤተክህነት ባልደረባ ነበር ይሳሉ ። የሰባ አንድ ዓመት አዛውንት ነው ። ዘወትር አንገቱን ደፍቶ ሰጸልይ ይታያል ። ይህም ሆኖ ሳለ የሚመቀኙት ሰዎች የፖሊስ ባልደረ ባና ሰላይ ነው ኢያሉ ያሙታል ።

አንድ ቀን ምሽት ላይ ጐን ቫልገ ኮዜትን ሳያስከትል ብቻውን ሲንሸራሸር ሳለ አዛውንቱን ለማኝ በተለመደው ቦታ ፣ በበራ ፋኖስ ሥር

@OLDBOOKSPDF

ተቀምጦ አየው ። እንደወትሮው አቀርቅሮ ሲጸልይ ነበር ። ግን ቫልጣ ያስለመደውን ምጽዋት ሊሰጠው ጠጋ አለው ። ሰማኙ አንገቱን አቅንቶ አየውና ወዲያውኑ መልሶ አቀረቀረ ። ግን ቫልጣም የሚያንቀጠቅጥ ስሜት ተሰማው ። የለማኙን ፊት ሳይሆን እሱ የሚፈራውን የሌላ ሰው ፊት ያየ መሰለው ። በጭለማ ውስጥ ሳያስበው በድንገት ከነበር ጋር ቢፋጠጥ ኖሮ ከዚያ ይበልጥ ባልደነገጠ ነበር ። ከድንጋጤውም የተነሳ ወደኋላው ዘሸሸ አለ ።

ለማኙ እንደወትሮው ቡትቶ ሰብሷል ። አመለካከቱም እንደወትሮው ነው ። «ኧረዲያ.....!» አለ ግን ቫልጣ ራሱ ለራሱ ፤ «አበድኩ መሰለኝ.....! ወይንስ በቀን ሕልም ውስጥ ነው ያለሁት.....! የማይሆን ነገር!»

እንዲሁ እያሰበ ወደማረፊያ ክፍሉ ተመለሰ ፤ ወንፈሱ ተረብሿ ። ለራሱ እንኳ ደፍሮ ለመናገር አቃተው እንጂ ያየው ሰውዬ ግቩር መስሎት ነበር ።

በማግሥቱ ምሽት ላይ ግን ቫልጣ ተመልሶ ለማኙ ከሚተመጥበት ሥፍራ ሔደ ። በቦታው አገኘው ። «እንደምን ዋልክ» አለው በሳ በአክብ እየመጸወተው ።

«ደህና ነኝ..... እግዚአብሔር ይመስገን» ሲል መለሰለት ። ያው የሚያወቀው ለማኝ እንጂ ግቩር አልነበረም ።

ግን ቫልጣ ልቡ መለስ ብሎለት ይስቅ ጀመር ። «ጣቸርን አየሁ ያለሰንኝ ምን ኖሯል? ዓይኔ እየደከመ ሔዷል ልበ——ልነ» ሲል አሰበ ። ከዚያ በኋላ ነጭን እርግፍ አድርጎ ተወው ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በማምሻ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ኮዚትን ሲያ ለጠናት ሳለ የጎርቦ ቤት በር ተከፍቶ ሲዘጋ ሰማ ። በተለምዶ በዚህ ሰዓት የሚገባና የሚወጣ ሰው የለም ። አሮጊቷ ሻማ ለመቅጠብ ብላ በጊዜ ትተ ኛለች ። በቤቱ ውስጥ ሌላ ነዋሪም የለም ። የበሩ መከፈትና መዘጋት አዲስ ነገር ስለሆነበት ኮዚት ዝም እንድትል በእጁ ምልክት አስጠነቀቃትና ጆሮውን አቁሞ ያዳምጥ ጀመር ። የሰው ኩቴ ሰማና «ምናልባት አሮጊቷ አሚት መድኃኒት ለመግዛት ወጥታ መመለሷ ይሆን?» ሲል አሰበ ።

ኩቴው ግን የወንድ እንጂ የሴት አልነበረም ። ግን ቫልጣ ጥርጣሬ አድሮበት ሻማውን አጠፋው ። ኮዚትንም ሳማትና «ቀስ ብለሽ ሔደሽ ተኚ » አላት ።

ደረጃውን ሲወጣ የነበረው ኩቴ ቆም አለ ። ግን ቫልጣም ጀርባውን ለበሩ ሰጥቶ ዝም ብሎ ቆየ ።

@OLDBOOKSPDF

ለዘም ያለ ጊዜ ካለፈ በኋላ ጎን ቫልጋ ፊቱን ወደ በሩ አዙሮ በቁልፉ ቀዳዳ ወደ ውጭ ቢመለከት ብርሃን መኖሩን ተገነዘበ ። ሻማ ይዘ ቆሞ የሚያዳምጠው ሰው ኖሯል!

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የሻማው ብርሃን አየራት ሔደ ። የከቱ ድምጽ ግን አልነበረም ። ሰውዬው ጫማውን አውልቆ በባዶ እግሩ ሲራመድ ነበር ማለት ነው ።

ጎን ቫልጋ ልብሱን ሳያወልቅ አልጋው ላይ ጋደም አለ ። እንቅልፍ ግን አልወሰደህ አሰው ። ንጋት ላይ ገና ዐሥብ ሲያደርገው የበር ሲጥሲጥታ ሰማና ነቃ ። ቀጥሎም የሰው ኩቱ ሰማ ። ዘልሎ ተነስቶ ወደ በሩ ሔደና አሁንም በቁልፉ ቀዳዳ ይመለከት ጀመር ። ሰውዬው ዮጎን ቫልጋን ክፍል አልፎ ሔደ ። መተላለፊያው በረንዳ ጨለምለም ከማለቱ የተነሳ ጎን ቫልጋ የሰውዬውን ፊት ስማየት ሳይችል ቀረ ። ሰውዬው ወደመው ረጃጀ ደረጃ ሲደርስ ግን ከመጭው የጣባ ጨረር ጅርባው ላይ ስላረፈ ግሼር መሆኑ ያስታወቅ ነበር ። ረጅም ካፖርት ለብሷል ። ቡብቡቱ ሥር ቆመጥ ዘንጥሏል ።

ጎን ቫልጋ መስኮቱን ከፍቶ በዓይኑ ሊከተለው ይችል ነበር ። ነገር ግን አልደፈረም ። ወንጀሌ አድርጎ ገባ.....? ቁልፍ ቢኖረው ኖሮ..... ነገር ግን ቁልፉን ማን ሰጠው.....? ደሞስ ጠቅላላው ሁኔታ ምን ትርጉም ሊሰጠው ይችላል?» ሲል አሰበ ።

ከንጋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን አሮጊቷ የተሊምዶ ሥራዋን ሰመሥራት ከጎን ቫልጋ ክፍል ውስጥ ገባች ። ጎን ቫልጋ አተኩሮ ተመለከታት ። አዲስ ነገር ግን አላየባትም ።

«ትናንትና ማታ እንድ ሰውዬ ሲገቡ አልሰሙም?» ስትል ጠየቀ ችው ፤ ክፍሉን እየጠራረገች ።

«ጨረ ካልሽሰ ሰምቻለሁ.....! ማን ኖሯል?»

«አስማቸውን አልያዝኩትም ። ግን ነበር ያሉኝ.....? ዲሞ ነው ወይንሰ ዶሞን»

«እና ሙሴ ዲሞ ማን ነው?»

አተኩራ አየችውና «እንደ እርስዎው በዓመት ገቢያቸው የሚተ ዳደሩ ሰው ናቸው» አለችው ።

አሮጊቷ ክፍሉን ጠራርጋ ስትጨርስ ወጥታ ሔደች ። ጎን ቫልገርም ከቱም ሳጥኑ ውስጥ የወዳጁ ፍራንክ ሳንቲሞች አውጥቶ በጥንቃቄ ይጠቀል ላቸው ገባ ። ምንም ያህል ቢጠቀቅም ግን አንድ ሳንቲም ከእጁ አምልጦ ወርዶ ወለሉ ላይ ተንጨለጨለበት ።

@OLDBOOKSPDF

ማታ ጭለማው ለዓይን ሲይዝ ጐን ሻልጎ ከክፍሉ ወጥቶ ፥ ደረጃውን ወርዶ ፥ ወደመንገዱ ወጣና ግራ ቀኙን ቃኘ ፤ ሰው መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ። ምናልባት ከዛፍ ግንድ በስተጀርባ የተደበቀ ሰው ካልኖረ በስተቀር በአካባቢው ማንም አልነበረም ። መንገዱም እርጭ ብሎ ነበር ።

ጐን ሻልጎ ተመልሶ ገብቶ ፥ ደረጃውን ወጥቶ ከክፍሉ ደረሰና ክዚትን አስከትሎ ወጥቶ ሔደ ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አራት

አዲን ያበረረው

— 1 —

ጨረቃ ወጥታለች ። ጨረቃዋ ከአድማስ አካባቢ ስለሆነች በመንደሩ ያለ ቋሚ ነገር ሁሉ ጥላ ሠርቶ ይታያል ። ግን ቫልገ ከዜትን አስከትሎ ብርሃን ብርሃኑን ሥራ አየተመ ፣ ጥላ ጥላውን እየመረጠ ፣ የተከተለው ሰው መኖር አለመኖሩን እያረጋገጥ ዝልመጥ ዝልመጥ ብሎ እየተመለከተ ነጐደ ። የት እንደሚሔድ አያውቅም ። ከዜት አሱን አምና እንደተከተለ ለኾው ሁሉ አሱም እምነቱን በአዝዚአብሔር ላይ ጥሎ እግሩ ወደመራው አመራ ።

ለመሆኑ በጎርቦ ቤት ያየው ሰውዬ ዐአርግጥ ግቬር ነበር ወይስ ግቬር ከሠኝ ግን ቫልገን አውቆት ኖሯል ወይስ እንዴትስ ሊያወቀው ወይም ሊጠራጠረው ቻለ? ግን ቫልገን ባህር በላው ተብሎ በገሃድ ተነግሮ የለም ወይ!?

መልሱ ምንም ይሁን ምንም ግን ቫልገ ከዚያን ወቅት ጀምሮ ከጐሬው የተባረረ አውሬ ሆኖ ፣ ጎርቦ ቤት ላለመመለስም ቆርጦ ሴላ መደ ዘቂያ ሥራ ለመሻት ይሯሯጥ ጀመር ። ድግት የጮከተለው ሰው ቢኖር ደብዛውን ለማጥፋት በማሰብ በዘወርዋራ መንገድ እየተጓዘ ፣ ከአንድ ሠፈር ወጥቶ ከሴላ ሠፈር እየነባ ፣ ከዚያም ወጥቶ ከሦስተኛ ሠፈር እየ ገባ ፣ እንዲሁ እንዲሁ ኢያለ የሽሽት ጉዞውን ቀጠለ ።

ከሴሊቱ አምስት ሰዓት ሲሆን የፖንቷዝ ጐዳናን አቋርጦ ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ሬት ለፊት አለፈ ። ጥርጣሬ ገብቶት ዞር ብሎ ቢመለከት ሦስት ሰዎች ተከትለውታል ። እንደኛው የበራ ፋኖስ ይዘዋል ።

ግን ቫልገ ተደናግጦ ፣ ከዜትን «ሄይ ልጄ» አሉትና ርምጃውን አፋጠነ ። የተለያዩ መንገዶችን አቋርጦ ሐዲ ከፖስት ጐዳና ሲደርስ ለምቹ አውንም ተከትለውት እንደሆነ ለማረጋገጥ ጨለም ያለ ጥግ ይዞ ቆመ ።

@OLDBOOKSPDF

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሦስት የነበሩት ሰዎች አራት ሆነው አየ ቸው ። አራቱም ረጂድም ናቸው ። ረጅምና ቡናማ ካፖርት ለብሰዋል ። ከብ ባርኔጣ ደፍተዋል ። ጥላልት ቆመጥ ይዘዋል ። ያስፈራሉ ።

ግን ቫልገር ስለጠፉባቸው ፡ ለመመካከር እንደፈለጉ ዓይነት ሰብ ሰብ ብለው ቆሙ ። ሃሳባቸውን ለመቁረጥ የተቸገሩ ይመስላሉ ። አንዱ ኛው በእጁ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲያመለክት ሌላው ወደ ሌላ አቅጣጫ ያመለክታል ። ከሰዎቹ አንደኛው ዞር ሲል የጨረቃ ብርሃን በፊቱ ላይ አረፈበት ። ግን ቫልገር ጨለም ካለው ጭማ ሆኖ አየውና ማን እንደሆነ አወቀ ። ጥቬር ነበር ።

— 2 —

ግን ቫልገር አራቱ ሰዎች በማመንታት ላይ መሆናቸውን ተገንዝቦ ከተደበቀበት ሹልክ ብሎ ወጥቶ በፖስት ጐዳና ወደ ጥርጁ ዴ ፕላንት አቅጣጫ ነጐደ ። ከቤት ደከምከም ስላለችበት አንስቶ ተሸከማት ። በመ ንገዱ ሰው የለም ። ጨረቃም ስላለ የመንገድ መብራት አልበራም ።

አርምጃውን በአጥፍ አፋጠነው ግን ቫልገ ። ከቶንሽ ጊዜም በኋላ በሲን ወንዝ ካለው ከመርከብ መጫኛና ማራገፊያ ሥፍራ ደረሰ ። ዞር ብሎ ቢመለከት የተከተለው ሰው የለም ። ለጊዜውም ቢሆን እፎይታ ተሰማው ።

ገፍቶ ሔዶ ከኦስተርሊዝ ድልድይ ደረሰ ። በዚያን ዘመን ድልድዮን ለመሻገር ቀረጥ ይከፈል ነበር ። ከቀረጥ መክፈያው ቢሮ ሔዶ አንድ ሱ ከፈለ ። ቀረጥ ተቀባዩም «የተሸከምከት ልጅ በእግሯ ለመሔድ የም ትችል ስለሆነ ለአሷም መክፈል አለብህ» አለው ። ግን ቫልገ አንድ ሱ ጨመረለት ። ይሁን እንጂ ሰውዬው ስላኑጋገረው ደስ አላለውም ፤ ማንም ልብ ሳይለው፡ እንደጥላ ለማለፍ ወዶ ነበርና ።

ድልድዩን በሚሻገርበት ወቅት አንድ ከባድ ጋሪ ስላገኘ ቢጋሪው ጥላ ሥር ሆኖ ይረማመድ ጀመር ። ከድልድዩ መሐከል ሲደርስ ከቤት በእግሯ ለመሔድ ፈለገች ። አወረዳትና እጇን ይዞ ይጓዝ ጀመር ።

ድልድዩን ከተሻገረ በኋላ ከበስተቀኙ በኩል ሁለት የእንጨት መከ መሪያ ቦታዎች ታዩትና ወደዚያ አቀና ። ቦታው የበራና ሊያጋልጠውም የሚችል ቢሆንም ላያመነታ መንገዱን ቀጠለ ፤ ሲከታተሉት የነበሩት ሰዎች ዱካው የጠፋባቸው መስሎት ነበርና ።

በሁለቱ የእንጨት መከመሪያ ቦታዎች መሐከል ጠባብ መንገድ አለ ። ጨለምለም ያለ ነው ። ከዚያ መንገድ ከመግባቱ በፊት ግን ቫልገ

@OLDBOOKSPDF

ዙር ብሎ ተመለከተ ። ተሻግሮት የመጣው የኦስተርሊዝ ድልድይ ወጣ ብሎ ታየው ። ወጣ ብሎ የታየው ድልድዩ ብቻም አልነበረም ። እኒያ ሲከታተሉት የነበሩት ሰዎች ድልድዩን ሊመሻገር ተቃርበው ነበር ። ደብ ዘው እንዳለጠፉባቸው ሲገነዘብ ግን ቫልገ ተንቀጠቀጠ ። ይሁን እንጂ አላዩኛም ይሆናል የሚል ተስፋ ከልቡ አሌተሩቀም ነበር ። ይህንኑ ተስፋ በልቡ ይዞ ከጨለምላማው ጠባብ መንገድ ገባ ።

— 3 —

ሦስት መቶ ርምጃ ከተራመደ በኋላ መንገዱ መንጵየሽ ሆኖ አንደኛው በስላት ወደ ቀኝ ፡ ሁለተኛው በስላት ወደ ግራ አቅጣጫ የሚያመራ ሆነ ። ግን ቫልገ ጭጋን ለያዝ ወይንስ ግራውን ሲል አመነታ ። በመጨረሻም ወደቀኝ የሚወስደውን መንገድ መረጠ ፤ ሰው ብዙዛት ወደማይናርበት አከባቢ ያመራ ነበርና ።

ከዚት እንደገና ደክምከም ሰላሳት ግን ቫልገ በጥጥት ለመራመድ አልቻለም ። ስለሆነም እንደገና አነሰቱ ተሸከማት ። ከዚያም በኋላ እንደተለ መደው ግልመጥ ብሎ አየተመለከተ መንገዱን ቀጠለ ። ሁለት ጊዜ ዙር ሲመለከት አንዳትም ነገር አሌታየውም ። ጥቂት ከተራመደ በኋላ እንደ ገና ዙር ሲመለከት ግን ወርወር የሚል ነገር ያየ መሰለው ። ተደናግጦ ርም ጃውን ይበልጥ አፋጠነው ። እየዳ,ሁ በጥድፊያ ሲራመድ ሳለ ከአንድ ግምብ ደረሰ ። ይዝገበት የነበረው መንገድ ከዚህ ግምብ ሲደርስ የሚያልቅ ቢሆ ንም ግራና ቀኝ የሚያከዳ ሁለት መንገዶች ነበሩበት ። አሁንም የት ኛውን አቅጣጫ ለምረጥ ቢል አመነታ ግን ቫልገ ። ወደ ቀኝ አሻግሮ ቢመለከት ይህ መንገድ ሩቅ የሚዘልቅ ሳይሆን ከአጉድ ከሌላ ግምብ ደርሶ የሚያበቃ ሆኖ አገኘው ። በግራ በኩል ያለው መንገድ ግን ገፍቶ ሔዶ ከትልቅ ጐዳና የሚዘልቅ ነበር ። የሚያዋጣው መንገድ ይኸኛው መሆኑን ግን ቫልገ ተገነዘበ ። ይሁን እንጂ ወዲዚሁ አቅጣጫ ሲታጠፍ በሩቅ ጥቁር ሐውልት የመሰለ ቅርጽ ታየው ። ሰው እንጂ ሐውልት አልነበረም ። መንገዱን ለመጠበቅ ታዝዘ የቆመ ሰው መሆን አስበት ሲል አሰበና መለስ አለ ግን ቫልገ ።

ወደየት አቅጣጫ እንደሚሔድ ጨነቀው ። በመጣበት መንገድ እንዳ ይመለስ ግቪርና ሰምቶ እየተከታተሉት ኖሮው ። በስተቀኙ ያለው መን ገድ ገማ ነው ። በስተግራው ያለው መንገድ ጠባቂ ዘበኛ የመሰለ ሰው ቆሞበታል ። መላ ቅጡ ጠፍቶት ዓይኑን እግዚአብሔር ወዳለበት ወደሰማይ ሰቀለው ።

@OLDBOOKSPDF

ግን ቫልግ መሸሻ ሲያጣ ከፊት ለፊቱ ያለውን አሮጌ ሕንጻ በዓይኑ ይፈታትሸው ገባ ። ሕንጻው ሰው የሚኖርበት አይመስልም ። በግድግዳው ላይ እንደዛፍ ቅርንጫፍ እዚህም እዚያም የተጋደሙ ቧንቧዎች አሉበት ። ከሕንጻው ማዶ ጫፉ የሚታይ ረጅም ዛፍ አለ ። ግን ቫልግ ይህንን ተመ ልክቶ ወዛፉ የበቀለው በአትክልት ቦታ ላይ ሳይሆን አይቀርም..... ከዚያ ለመድረስ ብችል ኖሮ እድን ነበር..... ነገር ግን እንዴት አድርጌ ከአትክ ልቱ ቦታ ለመዝለል አችላለሁ.....? በግድግዳው ላይ ባሉት ቧንቧዎች አቀባብዬ ልውጣ ይሆን.....? ብቻ ከዚችን ምን አደርጋታለሁ.....? ይዣለት ግድግዳው ላይ ለመውጣት የማይሞክር ነው..... እሷን እዚህ ትቼአት እንዳ ልሸሽም የማይታሰብ ነው.....!» ሲል አሰበ ። ጭንት..... ጭንትቅንት አለው ። በፍጥነት አንድ ዓይነት ርምጃ ካልወሰደ ከመያዝ እንደማያመልጥ በድን ተሰማው ። የሕንፃውን የተዘጉ በሮች እየት አዩረገና ሰብሮ ለመግባት ታጣው ። ነገር ግን ይህም የማያዋጣ ሆነበት ።

ከሩቅ ቦታ የሰው ኩቴ ሰማና ዓይኑን ድምጹ ወደመጣበት አቅጣጫ አዞረ ። ሰባት ወይም ስምንት የሚሆኑ ወታደሮች በሩቱ ታዩት ። ሳንሸ ወድረው እሱ ወዳለበት አቅጣጫ ያመራሉ ። ቆም ብለው ግራና ቀኝ ይመ ለከታሉ ። መልሰውም ይንቀሳቀሳሉ ። ዙርያ ገቡን በማሰስ ላይ ስለሆኑ ዝግ ብለው ነው የሚራመዱት ።

ግን ቫልግ ይበልጥ ተሸበረ ። ግቫርና ሰዎቹ ደርሰው ከያዙት እንደገና ዕድሜ ልክ እስራት እንደሚጠብቀው ደህና አድርጎ ያውቃል ። ዕድሜ ልክ ከታሠረም ከእዚች መነጠሉ የማይቀር ነው ። ስለዚህ ባለው ዘዴ ማምለጥ አለበት ።

ግን ቫልግ በቱሉ እስር ቤት በኖረበት ዘመን ያለመሰላል ፣ ቢሰው ነቱ ጡንቻ ብቻ እየተመካ ግድግዳ ቧጥጦ እስከ ፎቅ ቤት ጣራ ድረስ ይወጣ እንደነበረ ትዝ አለው ። ይህ ችሎታው አሁንም አለ ። «ለምን አልጠቀምበትም?» ለማለት እንደፈለገ ሁሉ የሕንጻውን ግድግዳ መልሶ በዓይኑ ፈታተሸው ። ግድግዳው አስራ ስምንት ሜማ ያህል ከፍታ አለው ። አልፎ አልፎ ለመያዝ የሚያመቹ ጉጦች አሉበት ። ግድግዳው በጣም ወፍራም ስለሆነ ጫፉ ዝርግ ነው ።

ለግን ቫልግ ከሁሉም ይልቅ ችግር የሆነበት የከዜት ጉዳይ ነበር ። እሱ ግድግዳውን ቧጥጦ ለመውጣት ቢችልም እሷ በምንም ሁኔታ ልትሞ ክረው አይቻላትም ። ትቷት እንዳይሸሽ ደሞ የማይሆን ነገር ነው ። ዉጣመድ

@OLDBOOKSPDF

ቢኖረኝ.....!» ሲል ተመኘ ። ገመድ ግን አልያዘም ። ወበመንፈቀ ሌሊት ገመድ ከወዴት አባቱ ላመጣ ነኝ!» አለና በድንገት አንድ ሃሳብ መጣለት ። ዓይኑንም በመንገድ መብራት ላይ ጣለ ።

በዚያን ዘመን የመንገድ ፋኖሶች ራት ራት ካለ ሥፍራ ይንጠለጠሉ ነበር ። መስቀያና ማውረጃ ገመድ ነበራቸው ። ግን ቫልጥ ራመድ ብሎ ሔዶ ፥ ስለቱን መዝዞ አወጣቱ የአንዱን ፋኖስ መስቀያና ማውረጃ ገመድ ቆርጦ ያዘና ከዚት ወዳለችበት ተመለሰ ።

እሱ ከወዲያ ወዲህ ሲንቀራጠጥ ሳለ ከዚት ደንገጥገጥ ብላ ሰታ-ስተ-ጉ-ለው ነበረች ። የወታደሮቹም ኮቴ እየተቃረበ በመምጣት ላይ ነበር ።

«አባዬ..... ፈርቻለሁ..... ማን ነው ወደኛ የሚመጣውባ» ስትል ጠየቀችው ።

«እስኪ..... ዝም በይ..... ማዳም ቴናርዲዬ ነች» አሳት ።

ከዚት በፍርሃት ተንቀጠቀጠች ።

«አንድ ቃል እንዳትተነፍሺ.....» ሲል አስጠነቀቃት ፤ «ምን እንደማ ደርግም እንዳትጠይቂኝ ። ብትጮኺ ወይም ብታለቅሺ ማዳም ቴናርዲዮ ሰምታሽ መጥታ ነው የምትወስደሽ»

ግን ቫልጥ ይህንን ከነገራት በኋላ ከራሳቱን ከአንገቱ ፈትቶ በከዚት ወገብ ላይ አሰረው ። እንዳያሳምማት በመፍራት ያለልክ አላጠበቀውም ። የገመዱን አንድ ጫፍ ከራሳቱ ላይ ቋጠረው ። ከዚያም በኋላ ጫማውንና የግር ሹራቡን አውልቶ በግድግዳው ላይ አሻግሮ ወረወራቸው ። የገመዱ ንም ሁለተኛው ጫፍ በጥርሱ ይዞ ግድግዳውን እየዘለጠ ፥ የሚያዝ ነገር ሲያገኝ ያንን እየያዘ በማያውቀው ዘዴ እየተጠቀመ ከግድግዳው ዝርግ ጫፍ ደረሰ ።

ከዚት አንዳችም ቃል ሳትተነፍስ በመደነቅ ሰታ-ስተውለው ቆየች ። የማዳም ቴናርዲዬን ስም ስላነሳባት ለመተንፈስ አልደፈረችም ።

ግን ቫልጥ ግድግዳው ጫፍ ላይ ሆኖ ትንሳሹ መለስ ካለለት በኋላ «ጀርባሽን ለግድግዳው ሰጥተሽ ቁሚ ከዚት..... አይዞሽ አትፍሪ» አላት ዝቅ ባለ ድምጽ ። ቀጥሎም በገመዱ እየሳበ ወደላይ ያወጣት ጀመር ። ሳታ-ጤነው እሱ ካለበት ደረሰች ። ግን ቫልጥም ጀርባው ላይ አዝሏት በሆዱ እየተሳበ ወደግድግዳው ጥግ አመራ ። ከጥቱ ሲደርስ የገቨር ድምጽ ጆሮ ውን መታው ። «ወንጀለኛን ፈትሹ..... ከዚህ አካባቢ ነው የተደበቀው» ሲል ነበር ገቨር ።

ግን ቫልገ ከዚትን ይዞ ከግድግዳው ጥግ በነበረው የሕንጻው ጣራ አቀባብሎ ቀስ ብሎ ተጓዘና ወደምድር በሚያወርድ መውረጃ ከመሬት ዘልሎ ዱብ አለ ። ከዚት አውንም ቃል አልተነፈሰችም ።

@OLDBOOKSPDF

ገርን ቫልገርና ከዜት ያሉበትን ቦታ አያውቁትም ። ቦታው በጣም ሰፊና ሞላላ ሆኖ የአግር መንገዶች ፣ ሣሮች ፣ የፍራፍሬ ተክሎች ፣ ቅጠላቅ ጠሎች ፣ የውሃ ጉድጓድ ፣ የድንጋይ መቀመጫዎች ፣ ሣር ቅጠሎች ፣ እነ ዚህ ሁሉ አሉበት ። የአትክልት ቦታ ነው ። ጣራውን ተንሸራትቶ ከወረ ደበት ሕንጻም ሴላ የሚገቡ አንጨት ክምርና አንድ የድንጋይ ሐውልት በአካባቢው ይታያሉ ።

ይህ ሰፈ የአትክልት ቦታ ነጠላ ያለና ምድረ በዳ የመሰለ ነው ። ሴሊት ስለሆነ አንዳችም ሰው አይታይበትም ። ቀንም ቢሆን ሰው የሚያ ዘወትረው ቦታ አይደለም ።

ሕንጻው ተዶረማምሷል ። ክፍሎቹ ወጥንቅጣቸው ወጥቷል ። ከከ ፍሎቹ አንደኛው ግን አንደመጠለያ የሚያገለግል ነበር ።

ገን ቫልገር ጫማዎቹን ከወረወረበት ሥፍራ ሔዶ አነሳቸውና ሰካቸው ። ቀጥሎም ከዜትን አስከትሎ ወደመጠለያው ገሥቶ ሔዶ ሁለቱም እዚያ ውስጥ ተደበቁ ።

ከዜት በጣም ስለፈራች ገን ቫልገር ላይ ተጣበቀችበት ። እሱን ሲከታተሉ የነበሩት ወታደሮች ሲንጫጩ ፣ የጠበንጃቸው ስደፍ ከድን ንጋይ ጋር ሲፋጭ ፣ ገሸር ከወታደሮች ጋር ቃል ሲለዋወጥ ፣ ይህ ሁሉ ይሰማል ።

ከሩብ ሰዓት በኋላ ግን የወታደሮቹ ጫጫታ እየራቀ ሔደ ። ገን ቫልገር ድምጹን አጥፍቶ ቆየ ። ከዜትም እንዳትናገር አፍን ያዛት ። በዚህ ምክንያት አካባቢው ጸጥ ፣ እርጭ አለ ።

አካባቢው እንዲሁ ጸጥ ፣ እርጭ ብሎ ከቆየ በኋላ በድንገት ከሰማይ የወረደ የሚመስል መንፈሳዊ ድምጽ ጆሮአቸውን ዳስሰው ። መንፈሳዊ ዜማ ነበር ..... ከልብ ውስጥ ጠልቆ የሚገባ ዓይነት ። የልጆገሪዶች ዜማ ..... የሕጻናት ዜማ ..... የደናግሎች ዜማ .....

ዜማው ከሴላ ከሩቅ ዓለም ዘልቆ የመጣ እንጂ ከዚህ ካለንበት ዓለም የመነጨ አይመስልም ። ይሁን እንጂ ምንጩ ከአትክልቱ ቦታ አጠ ገብ የነበረው ግዙፍ ሕንጻ እንጂ ሴላ አልነበረም ።

ገን ቫልገርና ከዜት ዜማው ምን እንደሆነ ፣ ያሉበትም ቦታ የት እንደሆነ ባያውቁም አንዳች ውስጣዊ ኃይል አስገድዷቸው መሬቱ ላይ ወርደው ተንበረከኩ ፤ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደሚጸልዩ ምዕመናን ።

@OLDBOOKSPDF

ግን ቫልገር ዜማውን በጥሞና ከማድመጥ በስተቀር ስለሌላ ነገር ማሰቡን አቆመ ። ጭለማው በዚያ የሌለም መሰለው ። ሰማዩ ጥቁር በመሆን ፈንታ ሰማያዊ ሆኖ ታየው ።

ዜማው በድንገት ጆሮአቸውን እንደዳሰሰው ሁሉ በድንገት አበቃ ። ምናልባት ለረጅም ጊዜ ቆይቶ ይሆናል ። ለግን ቫልገር ግን ቅጽበት መስሎ ተሰማው ፤ ደስ የሚያሰኝ ነገር ሁልጊዜም በፍጥነት ያልፋልና ።

አካባቢው እንደገና ጸጥ ፥ አርጭ አለ ። ነፋስ ዝግ ብሎ ይነፍሳል ። በግምቡ ላይ ያሉ ዶሪቅ በቀልቶች ይንሿሿሉ.....

— 7 —

ሴሊቱ እየገፋ ሔደ ከሰባት አስክ ስምንት ሰዓት ገደማ ሆነ ። ከዚት ቃል አልተነፈሰችም ። ራሷን ግን ቫልገር ለውጎት ላይ አስደግፉ ዝም ብላ ቁጭ አለች ። ስጋት ያለባት ትመስላለች ። ግን ቫልገር ጐንበስ ብሎ «እንቅልፍሽ መጣ እንዴ?» አላት ።

«በርዶኛል» አለችው ።

ኮቱን አውልቆ አለበሳት ።

«አሁንም አሉ.....? አልሔዱምን» ስትል ጠየቀችው ።

«ማን?»

«ማዳም ቱናርዲዬ ።»

ግን ቫልገር ከዚችን ለማሰፈራራት ያህል ማዳም ቱናርዲዬ በዚያ አካባቢ አለች ማለቱን ረስቶት ነበር ።

«ሔዳለችኮ.....! ከአሁን ወዲያ የሚያስፈራሽ ነገር የለም» አላት ።

ሸክም እንደወረደላት ሁሉ በኃይል ተንፈሰች ከዚት ።

መፈቱ ይቀዘቅዛል ። መጠለያው በሁሉም ገፉ ክፍት ነው ። ነፋሱም እየቀዘቀዘ ሔደ ። ግን ቫልገር ኮቱን አውልቆ ካለበሳት በኋላ «አሁን ትንሽ ተሻለሽ ብርዱን» አላት ።

«አዎን አባዬ ።»

«እንግዲያውስ እዚሁ ቁዪኝ ። እኔ አሁን እመለሳለሁ» አላትና ከመጠለያው ወጥቶ በግዙፉ ሕንጻ አካባቢ ወዲያ ወዲህ ይል ጀመር ። የተሻለ መጠለያ መፈለጉ ነበር ። የሕንጻው በሮችና መስኮቶቹ ተዘግተው አገኛቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ከአንድ ጥግ ሲደርስ ግን መብራት ያለባቸው መስኩቶች መኖራቸውን ተገነዘበ ። በጣቱ ቆሞ በአንደኛው መስኮት መስታወት ወደ ውስጥ ቢመለከት ውስጡ አዳራሽ መሆኑን ተገነዘበ ። ወለሉ ንጣፍ ድንጋይ ሆኖ ቋሚ አምዶች አሉበት ። የጨፍ ብርሃን ስላለ ጥላዎች ይታያሉ ። ግን ቫልገር ትክ ብሎ ቢመለከት አዳራሹ ውስጥ የተገነዘ አስከሬን የሚመስል ቅርጽ ታየው ። አስከሬን የመሰለው ቅርጽ በፊቱ ተደፍቷል ። ግራና ቀኝ እጆቹ የተዘረጉ በመሆናቸው የመስቀል ቅርጽ ይሠሏል ። አስከሬን የመሰለው ቅርጽ አይንቀሳቀስም ። እንደአወነተኛ አስከሬን ለጥ ብሏል ። በአንቱ ዙርያ ገመድ የተጠመጠመበት ይመስላል ።

ግን ቫልገር ይህንን ሲያይ በጣም ቀፈፈው ። «በእርግጥም የሰው አስከሬን ነወ። ወይንስ ወለሉ ላይ የተኛ ሕያው ሰወ?» ሲል አሰበ ። ረዘም ላለ ጊዜ እንዲሁ ሲያስተውለው ቆይቶ እንዳችም እንቅስቃሴ ባለማየቱ ፍርሃት ወርሮት ከዚያ ሸሽቶ ሔዶ ። አስከሬኑ ተኝቶ የሚከተለው ይመስል ፊርቶ ወደ ኋላው ዞር ብሎ ለማየት እንኳ አልደፈረም ። በሩጫ ወደመጠለያው ቦታ አመራ ። ከዚያ ሲደርስ ጉልበቱ ተብረከረከ ። ላብ ኑጥለቀለቀው ። በኃይል ስለሮጠም ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለበት ።

«የት ነው ያለሁት....» ሲል ያሰብ ጀመር ፤ «ፓሪስ ከተማ ውስጥ እንዲህ ያለም ቦታ አለ! ይህ አስገራሚ ሕንጻ ምንድነወ? በእንድ በኩል ከመንግሥት ስማያት የወረዱ የሚመስል ዜማ የሚሰማበት ፥ በሌላ በኩል የማይንቀሳቀስ አስከሬን የመሰለ ነገር የሚታይበት ሕንጻ....»

ብርዱ ፥ ጭንቀቱ ፥ ሰጋቱ ፥ እነዚህ ሁሉ ተጸምረው ትኩሳት ሰቀቁበት ። የተምታቱት ሃሳቦችም በአእምሮው ውስጥ ይመላለሱበት ጀመር ። እንጉቱን ደፉ አድርጎ ከዜትን ቢመለከታት እንቅልፍ ወስዷታል ።

— 8 —

ግን ቫልገር በሃሳብ ሲባዝን ከቆየ በኋላ ከወዴ አትክልቱ ቦታ አቅጣጫ የሚቅጨሰጨል ድምጽ ሰማ ። ድምጹ ወደመጣበት ዞር ብሎ ቢመለከት ሰው መኖሩን ተገነዘበ ። ሰውዬው በመሬት ላይ አንዳች ነገር እየገመተና እየዘረጋ አንዴ ገንበስ ፥ አንዴ ቀና ፥ አንዴ ቆም ፥ አንዴ ሔድ ሲል ነበር ። ደሞም ያንክሳል ።

ግን ቫልገር ተንቀጠቀጠ ። ሰውዬውን በጣም ተጠራጠረው ። ቀደም ብሎ የአትክልቱን ቦታ እና ሆኖ ሲያገኘው እንዳልፈራ ሁሉ አሁን ደሞ ሰው መኖሩን ሲገነዘብ ከበፊቱ ይልቅ ፈራ ። ይኸውም በፖሊስ የሚታደኑ ሰዎች ባህርይ ነው ። ሁሉም ነገር ያስፈራቸዋል ። ያስደነብራቸዋል ።

«ጎርቬር የሚከታተለኝ ሰው አድርጎብኛል..... ይህ ሰውዬ ካየኝ ጮኾ እንደሚያስይዘኝ ጥርጥር የለውም» ሲል አሰበና ከዜትን አንስቶ ታቅፏት

@OLDBOOKSPDF

መጠሊያውን ለቅቆ አሮጌ የቤት ዕቃ ከተከማቸበት ጣ ሔደ ። ከዚት ከአንቅልፏ አልነቃችም ።

ጎን ቫልገ ካለበት ጣ ሆኖ ሰውዬውን በዓይኑ ይከተለው ገባ ። ሰውዬው በተንቀሳቀሰ ቁጥር ታጭሱ ይቅጨለጨላል ። እየራቀ ሲሄድ የታጭሱ ድምጽ ዝቅ ይላል ። ርምጃውን ሲያፋጥን ድምጹም ቀስ ቀስ ይቅጨለጨላል ። ቆም ሲል የታጭሱ ድምጽ ጥፍት ይላል ። ታጭሱ ከሰውዬው አካል ጋር የተያያዘ መሆኑ የሚያጠራጥር አልነበረም ። « ምን ማለት ነው ፣ አንደሙክት ወይም እንደበሬ ታጭስ የታሠረለት ሰውዬ ማን ነው ?» ሲል አሰበና መንፈሱን ወደ ከዚት በመመለስ ነክ አድርጎ ቢያያት ቅዝቅዝ ብላለች ።

« ጉዴ ፊላ ! ምን ሆናለች ይቺ ልጅ ?» አለና «ከዚት ! » ሲል ጠራት ፣ ዝቅ ባለ ድምጽ ። መልስ አልሰጠችውም ። ጎን ቫልገ ነቅነቅ አደረ ረጋት ። እሷ ግን ዩጥ ብላ ቀረች ።

« ሞታለች እንዴ ይቺ ልጅ ? » ብሎ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ቀኑ ሲዩ ቆመ ። መጥፎ መጥፎ ሃሳቦች በአእምሮው ጠለቀ ይመላለሱበት ጀመር ። በሚያፈቅሩት ላይ አንዳች ነገር ሲደርስ በሽታ ግልብ መጨመድ የተለመደ ነው ።

አግሩ ሥር በድን ሆኖ ስለቀረች ዝቅ ብሎ ትንፋሿን ያዳምጥ ጀመር። ከዚት አልሞተችም ። ነገር ግን በጣም ተጨንግፋለች ። የአዲቱ ቁር ነው ከዚህ ያደረሰት ።

« እንዴት አድርጌ ላሙቃት ? እንዴትስ አድርጌ ባኔታት ፣ እሳት ከወደዩት ለማግኘት እሮጫለሁ ? በራብ ሰንሰት ወስጥ እሳት ካለበት ካልወሰድኳት በስተቀር ሕይወቷ ማለፉ ነው » ሲል አሰበ ጎን ቫልገ።

— 9 —

ጎን ቫልገ ቀደም ብሎ በአትክልቱ ቦታ ያየውን ሰውዬ የጉቨር ሰው ይሆናል ብሎ ቢጠረጠረውም የከዚትን ሕይወት ለማዳን ሲባ ምርጫ ስላልነበረው ጥርሃቱን አቨንር በቁጥታ ወደሰውዬው አመራ ። ከዚያም ሲደርስ ከሰደርያው ኪስ ገንዘብ አወጥቶ «ሙት ጥራንክ» አለው

ሰውዬው ከጉንበሰበት ቀና ብሎ በመገረም ዓይን አየው ።

«ለባሬ ሌሊት መጠለያ ከስጠሽኝ ሞቶ ጥራንክ አከፍልሃለሁ» አለው ።

ጫንደሬ አርስዎ ነምት እንዴ ሙሴ ማድሌንዘ አለው ሰውዬው ።

@OLDBOOKSPDF

ግን ቫልጣ ይህን ሲሰማ ደንገጥ ብሎ ሸሸት አለ ። በፍጹም ያልጠበቀው ፥ በፍጹም ያላሰበው ሆነበት ። ሰውዬው አዛውንትና አንካሳ ነበር ። አስባበሱ ገጠሬ አስመስሎታል ። ግራ ጉልበቱ ላይ የታሠረ ቃጭል ይታያል ። ፊቱ ግን በጉለሀ አይታይም ፥ ጥላ ሥር ስለሆነ ።

በእኩለሮት ቆቡን አውልቆ «ወይ አግዚአብሔር! ወደዚህ እንዴት መጡ? እንዴትስ አድርገው ከዚህ ምድረ ግቢ ገቡ? ወይ የአግዚአብሔር ሥራ! ከሰማይ ወረዱ ልበ——ል! ከሰማይ ቢወርዱም አይገርመኝም! ደሞም ምን መሰለዋል ሙሴ ማድሌን! ክራቫት ሳያሥሩ..... ባርኔጣ ሳይደፉ..... ኮት ሳይለብሱ..... ባላውቆት ኖሮ ባስፈራኝ ነበር!»

«አንተ ማነህ? ሕንዳውስ ምንድነው?»
«አወጣት አላወቁኝም? ወደዚህ የላኩኝ አርስዎ ነዎት ። ደሞም ይህን ቦታ አላውቀውም ነው የሚሉኝ?»

«አዬ አላወቅሁህም ። አንተ ግን እንዴት አወቅኸኝ?»
«በአንድ ወቅት ከሞት አድነውኛልኮ ሙሴ ማድሌን ።»

ሰውዬው ከጥላው ሥር ብቅ ሲል ፊቱ ላይ የጨረቃ ብርሃን ስላረፈበት ግን ቫልጣ የሚያወቀው ሰው መሆኑን ተረዳ ።

«እንዴ! አንተ ነህ ልክ! አሁንስ አውቄሃለሁ» አለው ።
«አንዴት ቢሉ ይሻላል ሙሴ ከንቲባ!» አሰው ፎሽለሻ ።
«እና ምን እየሠራህ ነወት?»
«የሀባብ ተክሎቹን እየሸፈንኳቸው ነኝ ።»

በእርግጥም ፎሽለሻ የሀባብ ተክሎቹን ኬሻ ሲያለብሳቸው ነበር ። ቀደም ብሎም ቅና ደፋ ሲል የነበረው በዚህ ሥራ በመሆኑ ነበር ።

«ጨረቃው ወገግ ብሎ ስለወጣ እየሩ በጣም ሳይቀዘቅዝ አይቀርም ብዬ ስለሰጋህ ተክሎቼን ልሸፍናቸው ብዬ ነው..... እረ ለመሆኑ እንዴት አድርገው መጡ መሉ ማድሌን?»

ግን ቫልጣ ምስጢሩን ለማባከን ስላልፈለገ ፎሽለሻ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ በመስጠት ፈንታ እሱ ራሱ ጥያቄ ይደረድርለት ገባ ። «ይህ በጉልበትህ ላይ የታሠረው ቃጭል ምንድነው?» አለው ።

«ሌቶች እኔ ካለሁበት ሥፍራ እንዳይቀርቡ የሚያግዳቸው መሣሪያ ነው ሙሴ ማድሌን ።»

«እንዴት.....? ምን ማለትህ ነወት?»

«እዩ ሙሴ ማድሌን..... ከዚህ ቦታ ሴት እንኺ ወንድ አይኖርበትም ።

@OLDBOOKSPDF

እኔ ወንድ ስለሆንኩ ኢደግኛ ስለምመስላቸው ታጭሶን ሲሰሙ ይሸሹ ኛል ። ለዚህ ነው ታጭሶን የማሥረው ።»

«ሐንጻውስ ምንድነው?»
«እውነት አላወቁትም?»
«በእውነት አላወቅሁትም ።»
«የአትክልተኛነት ሥራ አግኝተውልኝ ወደዚህ ሲልኩኝ ቦታውን ኢየወቁትም ነበር ማለት ነው?»
«ይልቁንስ ብትነግረኝ አይሻልም?»
«ይሽኩ የፐቲ—ፒክፐ ገዳም ነው ሙሴ ማድሴን ።»

ዣን ቫልጣ ቦታውን አሁን አስታወሰው ። «አህ! የፐቲ—ፒክፑ ገዳም!» አለ ራሱ ለራሱ እንደማናገር ሰው ።

«አምን.... ብቻ እንዴት አድርገው ከዚህ ለመጣት ያሉ ሙሴ ማድሴን ። ማንኛውም ወንድ— ቅዱስ ቢሆን እንኳ— ከዚህ ለመጣት አይ ፈቀድስትም ።»
«እንተስ ወንድ አይደለህም!»?
«እኔ በስተኮር ማለቱ ነበር ።»
«ተፈቀደም አልተፈቀደ ይሽው ከዚህ አጣኑኝሻል ።»
«ወይ የእግዚአብሔር ነገር!»
«ሕያውትህን አድኜልሃለሁ አባ ሮዝሲቫ..... ያኔ ጋሪው ጨፍል ቆሀ የነበረ ዕለት.....»
«እሱንማ ቀድሚ ነግፌዎት የለም እንዴ!»
«እሁን ደም በተራህ እንተ ሰኔ የምታሥርግልኝ አሰ ።»
«ወላታ መላሽ ብሆን ምንኛ ደስ ባለኝ» አለው በሚንቀጠቀጡ እጆቹ የገኖን ቫልጣን ከባድ እጆች ለቀም አድርጎ ይዞ ። «ለኛ ምን ባደረግ ሎት ይወዳሉ?»
«ልነግርህ ነኝ..... ለመሆኑ ከፍል አለህ?»
«ከገዳሙ በስተጀርባ ነጠላ ያለች ጎጆ አለኝኝ ። ሦስት ክፍሎች አሏት ።»

በእርግጥም ጎጇው ሰው ከሚያየው ጣዝ ሰለነበረ ዣን ቫልጣ ልብ አላለውም ነበር ።
«መልካም ነው ። እና አሁን ሁለት ነገር ልነግርህ እወዳለሁ» አለው ዣን ቫልጣ ።
«ምንና ምን?»
«አንደኛ ስለኔ የምታውቀውን ለማንም ሰው እንዳታወራ ። ሁለተኛም ስለኔ ከምታውቀው በላይ ለማወቅ አንዳችም ጥያቄ እንዳትጠይቀኝ።»

«እንዳሉት ይሁን ሙሴ ከኑቪ ። ደግ ነገር እንጂ ክፉ ነገር እንደማ ይሠሩ ስለማውቅ ታማኝዎ ነኝ ።»

@OLDBOOKSPDF

«እንግዲያውስ ተግባብተናል። እና አንዲት ፍሬ ልጅ ከኔ ጋር ስላለች እሷ ዘንድ እንሒድ።»

«ልጅም አስከትለዋል እንዴ!» አለውና እንደታማኝ አሽከር ከኋላው ተከተለው።

ግን ቫልግና ፎሽለቫ ከዜትን ይዘው ወደ ጎጆው ቤት ሒደው እሳት አጠገብ አስተኟት። ከእኩል ሰዓት በኋላ ሰውነቷ ስለሞቀ ከፎሽለቫ አልጋ ላይ አውጥተው አስተኟት። ከዚያ በኋላ ሁለቱ እምድኟው አጠገብ ተቀምጠው ዳቦና አይብ እየበሉ ወይን ጠጅም እየጠጡ ጓሳት ይሞቁ ጀመር።

«ወቸ ጉድ!» አለ ፎሽለቫ ፤ «በመጀመሪያ ሳያውቁኝ በመቅረትዎ ተግርሚአለሁ መሲ ማድሌን! ሰውን ከሞት አፋፍ ይመልሱና ሰውዬውን መርሳት.....! እኔ ግን ልረሳዎት አይቻለኝም ነበር።»

— 10 —

ግን ቫልግ ከኡም ሱር ኡም ወሀኒ ቤት አምልጦ ከወጣ በኋላ ፖሊሶች ወዴ ፓሪስ ሒዲል ብለው አምነው ነበር። ፓሪስ እንደባህር የገባበትን ሁሉ የሚውጥ ስለሆነ ለመደበቂያነት ከፓሪስ የተሻለ ቦታ ከቶም የለም። ወንጀለኞችም ሆኑ እነሱን የሚከታተሉ ፖሊሶች ይህንን ደህና አድርገው ያውቃሉ። ስለሆነም ፖሊሶቹ በገቨር እየተመሩ ግን ቫልግን ፓሪስ ውስጥ ሲፈልጉትና ሲያስፈልጉት ሰንበተው ነበር። ይሁን እንጂ በታህሳስ ወር 1823 ዓ. ም. «ግን ቫልግ ሞቷል» የሚል ዜና በጋዜጣ ወጥቶ ስለነበረና ገቨርም ዜናውን አንብበት ስለነበረ የግን ቫልግን ጉዳይ እርግፍ አድርጎ ትቶት ነበር። ጊዜው ውሎ ካደረ በኋላ ግን አንዲት ልጅ ከሞንፈርመይ ተጠልፋ ተወሰዳለች የሚል ዘገባ ከፓሪስ ፖሊስ ጽ/ቤት ደረሰ። ዘገባው ፤ «የሰባት ወይም የስምንት ዓመት ዕድሜ ያላት አንዲት ልጅ እናቷ በአደራ ካስቀመጠቻት ቦታ ፥ ማለት ከአንድ የሆቴል ቤት ባለንብረት ባልታወቀ ሰው ተጠልፋ ተወስዳለች። ልጅቷ ከዜት ትባላለች። እናቷም ሩንቲን የተሰኘች ነበረች» የሚል ነበር።

ወሬው ከገቨር ጆሮ ሲደርስ ዝም ብሎ ለመቀመጥ አልቻለም። ሩንቲንን ያውቃታል። ግን ቫልግ የሩንቲንን ልጅ ካለችበት ሒዶ ለማምጣት ሦስት ቀን እንዲሰጠው እንደተማጸነው ትዝ አለው። ግን ቫልግ ወዴ ሞንፈርመይ ለመጓዝ በጋሪ ሲሳፈር ሳለ በፓሪስ ከተማ እንደተያዘም አስታወሰ። «ያን ጊዜ ግን ቫልግ ወዴ ሞንፈርመይ ለመሔድ የፈለገው ይህችን ልጅ ለማምጣት መሆን አለበት..... እና አሁን ይህች ልጅ ተጠልፋለች..... ጠላፊዋ ማን ሊሆን ይችላል? ግን ቫልግ ራሱ ይሆ—ን....? እሱ ሊሆን ግን እንዴት ይችላል.....? እሱ ሞቷል ተብሎ በጋዜጣ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ወጥቶ የሰም ወይ?» እነዚህን ጥያቄዎች በአእምሮው ውስጥ አንስቶ ሲጥል ቆየና ለማንም ሳይናገር ወደማንፈርመይ ሐዲዱ ሁኔታውን ለማጣራት ወሰነ ።

ሁኔታውን በሚገባ ለማጣራት ግን አልሆነለትም ። እነቴናርዲዬ ለጣቪር እውነቱን አፍረጥርጠው ለመናገር አልፈለጉም ። ምክንያቱም በሕግ ፊት እነሱን የሚያስጠይቁ ጉዳዮች ነበሩና ። ለመሳሌ ቴናርዲዬ በኮዜት ምክንያት 1,500 ፍራንክ ተቀብሏል ። ይህንን ገንዘብ በምን ምክንያት ተቀበልሁ ብሎ ሊያስረዳ ይችል ኖሯል? ቴናርዲዬ ጉዳዩን ለመሸፋፈን ስለፈለገ ጣቪር መጥቶ ስለሁኔታው ሲጠይቀው ፣ «ልጅቷን አናፈቅራት ነበር ። ሁለት ወይ ሦስት ቀን እንኳ ከሸው ጋር እንድትቆይ ፈቃዳችን ነበር ። ነገር ግን የልጅቷ አያት ተቃውሞ ወሰዳት» ሲል የተድበሰበሰ ነገር ነገረው ።

«የልጅቷ አያት.....? ስሙ ማን ይባላል?»

«በይለፍ ወረቀቱ ላይ እንዳየሁት ስሙ ሙሴ ጊዮም ላምቤር ይመስ ለኛል..... ሀብታም ገበሬ ነው » አለው ።

ላምቤር የታወቀ ቤተሰብ ስም በመሆኑ ጣቪር ሌላ ነገር ሳይጠይቀው ወደ ፓሪስ ተመለሰ ። «ጣን ቫልጣ በእርግጥ ሞታለ.....እኔ በከንቱ ተሞኛቹ ነበር» ሲልም አሰበ ።

ጣቪር በመጋቢት ወር 1824 ዓ. ም. «ምጽዋት የሚሰጥ ሰማኝ በቅዱስ ሚዳር ሰበካ አካባቢ ይኖራል» የሚል ወሬ ሲሰማ እንደገና ተጠራጠረ ። «ይህ ለማኝ ሀብት ያለው ሰው ነው ። ስሙ ግን ማን እንደሆነ አይታወቅም ..... የሰምንት ዓመት ዕድሜ ካላት ልጅ ጋር ይኖራል..... ልጅቷ ከሞንፈርመይ መምጣቷን እንኚ ከዚያ በላይ ስለራሷ የምታውቀው ምንም የላትም» ተብሎ ተወርቶ ነበር ። ከሞንፈርመይ መጣች መባሉ በጣቪር ላይ ከፍተኛ የሆነ የማወቅ ጉጉት አሳደረበት ። ጣን ቫልጣ ምጽዋት ይሰጠው የነበረውም ሽማግሌው ለማኝ የፖሊስ ሰላይ እንደመሆኑ ለጣቪር እንዳንድ ወሬ አቀብሎታል ። «ሰውዬው አፋራም ቢጠ ነው ። ማታ ማታ እንኚ ቀን ቀን ከቤቱ አይወጣም ። ከሰው ጋር እምብዛም አያወራም ። ሰው እዲጠጋውም አይፈቅድም» ሲል ነግሮታል ። ይህ ዓይነቱም መረጃ የጣቪርን የማወቅ ጉጉት አባባሰው ። ለዚህም ነው ጣቪር የለማኙን ሰላይ ልብስ ለብሶ ለማኙ በሚቀመጥበት ቦታ ቁጭ ብሎ ግን ቫልጣን የጠበቀው ። ፈላጊውና ተፈላጊው ያን ቀን ምሽት በድንገት ሲፋጠጡም ሁለቱም ተደናገጡ ።

ይህም ሆኖ ሳለ ጣቪር ምናልባት ጭለማው አሳስቶኛ ይሆናል በማለት ያየው ሰውዬ እውነት ግን ቫልጣ መሆን አለመሆኑን በይበልጥ ለማረጋገጥ ወደ ሳርቦ ቤት ሐዲዱ አሮጊቷን አነጋገራት ። አሮጊቷም የምታውቀውን ፣ በተለይም ሰውዬው ብዙ ገንዘብ በአሮጌ ኮቱ ውስጥ ይዞ እንደሚሔድ ፣ አሷ ራሷ የአንድ ሺ ፍራንክ ወረቀት እንደዘረዘረችለት

@OLDBOOKSPDF

ዝክዝክ አድርጋ ነገረችው ። ያኔ ነው ጎርቬር በዚያ ቤት ውስጥ ክፍል ተከራይቶ ያደረው ። ከጎን ቫልጉ ክፍል ውጭ ቆሞም ድምጹን ሰመስማት መከራ አደረገ ። ጎን ቫልጉ ግን ነቅቶበት ስለነበረ አንዳችም ቃል አልተነፈሰም ።

በማግሥቱ ጎን ቫልጉ ቤቱን ለቅቆ ሲሔድ ወዲያውኑ አሮጊቷ ወደ ጎርቬር ሔዳ ነገረችው ። ጎርቬር ሁሉት ሰው አስከትሎ መጥቶ ጎን ቫልጉን ተከታተለው ። ተጨማሪ ሰው እንዲሰጠውም የፖሊስ ጣቢያውን ጠየቀ ። ማንን ለመከታተል እንደፈለገ ግን ለፖሊስ ጣቢያው አላስታወቀም ።

የፈለገውን ተጨማሪ ሰው ተሰጥቶት ጎን ቫልጉን በቅርብ ተከታተለው ። ነገር ግን ጎን ቫልጉ ላይ እጁን ለማሳረፍ አልደፈረም ። ምክንያቱም ፥ አውነም ቢሆን ስለእሱነቱ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ለመሆን አልቻለም ። እርግጠኛ ሳይሆን ቢይዘውና ጋዜጠኞች ይህንን ቢሰሙ የፖሊስ ሥራዊቱን ስም ያጠፉት ቲል ፈራ ። ሳያረጋግጡ ሰውን መያዝ የሰውን የነጻነት መብት መጻፈር ስለሆነ ጎብረተሰቡ ያወግዘዋል ። ያለ አግባብ ሰውን የያዘ ፖሊስ ከሥራ ሊባረርም ይችላል ። ስለዚህ ጎርቬር ስህተት እንዳይሠራ በጣም ተጠነቀቀ ። ስለሆነም ጎን ቫልጉን በመያዝ ፈንታ እርግጠኛ እስኪሆን ድረስ ሊከታተለው ወሰኖ በጎባበትና በወጣበት ሁሉ ተከታተለው ።

ርግጠኛም የሆነው በፖቶቷዝ ጉዳና ከአንድ መጠጥ ቤት የሚን ጸባረቅ ኃይለኛ ብርሃን ጎን ቫልጉ ላይ ባረፈበት ወቅት ሆነ ። እሱነቱን ሙሉ በሙሉ ካረጋገጠ በኋላ ክትትሉን በአዲስ ኃይል ቀጠለ ። ደርሼ እይዘዋለሁ ባለበት ወቅት ግን ጎን ቫልጉ የውሃ ሽታ ሆነበት ። ጎቬር ቀደም ብሎ ስላልያዘው ተቆጨ ። «ወይኦት አባቱ ግባ ?» ሲልም አሰበ ። ለጊዜው ቢያመልጠውም ግን ተስፋ አልቆረጠም ሌሊቱን ሙሉ አካባቢውን በዘበኞች ሲያስፈትሽ አደረ ። ሌሊቱ ሲነጋም ሁለት ሰላዮች የጎን ቫልጉን ዱካ እንዲፈልጉ አዝዞ እሱ ወደ ፖሊስ ጣቢያው አመራ ። ክትትሉ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ውጤት አልባ ሆኖ በመቅረቱ በሆዱ ሰያፍርበት አልቀረም ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አምስት

ፕሉ-ፒክፑ

— 1 —

በፕሉ ፒክፑ ጐዳና ያለው ቁጥር 62 የሆነው ቤታ በግምብ አጥር የታጠረ ፣ በምድረ ግቢውም መኳኩሲዶች የሚኖሩበት ሕንጻ ፣ ልጃገረዶች በአዳሪነት የሚኖሩበትና የሚማሩበት ሕንጻ ፣ እንዲሁም ዕለት ሞታቸውን የሚጠባበቁ ባሉቴቶች የሚኖሩበት ሕንጻ ፣ ቤተ ክርስቲያን ፣ ሰፊ ሚዳና የአትክልት ማልሚያ ሥፍራ ያለው ፣ የቤርናርዲኖች ገዳም በሚል ስም የሚጠራ የሴቶች ገዳም ነው ።

መኳኩሲዶቹ ሰፊ እጅጌ ያለው ጥቁር ተሚስ ይለብሳሉ ። ፊታቸውን በሻሽ ይጋርዳሉ ። ዓመቱን ሙሉ ይጾማሉ ። ሥጋ አይቀምሱም ። በግር ጉዝጓዝ ላይ ይተኛሉ ። ስውነታቸውን እንዳይታጠቡ ፣ ጥርሳቸውን እን ዳይፍቁ ፣ እስት እንድደው እንዳይሞቁ ክልክል ነው ። ከሌሊቱ ከሰባት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ጊዜ ከመኝታቸው ተነስተው የጸሎት መጽሐፋቸውን ያነበባሉ ፣ መንፈሳዊ ዜማም ያዜማሉ ። አርብ አርብ ራሳቸውን በራሳቸው ይገረፋሉ ። ቢዝም ታ ይኖራሉ ። በዕረፍት ሰዓት ካልሆነ በስተቀር እርስ በእርሳቸው ፈጽሞ አይነጋገሩም ። ታዛዥ ነት ፣ ድህነት ፣ ንጽህና ፣ እና ከውጪ ዓለም ተነጥሎ መኖር ሕጋቸውና ግዴ ታቸው ነው ።

ወንድ እንዳያዩ አይፈቀድላቸውም ። በቅዳሴ ጊዜ እንኳ ቀዳሹ ካህን በመጋረጃ ስለሚጋረድ ሊያዩት አይችሉም ። ሲሐዱ አንገታቸውን ደፍ ተው መሬት መሬቱን እያዩ እንጂ አንገታቸውን አቅንተው ለመራመድ የገዳሙ ድንጋጌ አይፈቅድላቸውም ። ከገዳማቸው ለመጣባት የሚችል ሊቀ ዳዳሱ ብቻ ነው ። ከሱ ሌላ አንድ ወንድ አትክልተኛ ብቻ በገዳሙ ለመኖር ይችላል ። ለዚህም አትክልተኛው ሽማግሌ መሆን አለበት ። መኳኩሲዶቹም እንዳይጠጉት ቃጭል በትልበቱ ላይ እንዲያስር ይገደዳል ።

@OLDBOOKSPDF

በጸም በጸሎት ከመኖራቸውም በላይ እያንዳንዳቸው በየተራ መን ፈሳዊ ተጋድሎ የሚያደርጉበት ጊዜ አለ ። ተጋድሎ በሚያደርጉበት ጊዜ ያለማቋረጥ በተከታታይ ለአስራ ሁለት ሰዓት ከቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ ፊት ለፊት ባለው ንጣፍ ድንጋይ ላይ ይንበረከካሉ ። ይኸውም ከቀኑ አስር ሰዓት እስከ ሌሊቱ አስር ሰዓት ፣ ወይም ከሌሊቱ አስር ሰዓት እስከ ቀኑ አስር ሰዓት ድረስ ነው ። ተረኛዋ መነኩሲት እንዲህ ተንበርክካ በምትቆይበት ጊዜ እጅጅን እርስ በእርሳቸው ታቆላልፋቸዋለች ። በእን ጂህም ዙርያ ገመድ ታስራለች ። መንበርከኩ ፍጹም ሲያደክማት ንጣፍ ድንጋዩ ላይ በሆድዋ ተኝታና እጅጅን መስቀልያ ተዘረጋቸዋለች ። ከድ ካሚ የምታርፈው በዚህ ሁኔታ ብቻ ነው ። ይህንን ተጋድሎ በምታደር ግበት ጊዜ በመላው ዓለም ላሉ ኃጢአተኞች ትጸልያለች ።

ከዚህም በስተቀር እያንዳንዷ መነኩሲት በየተራ ለአንድ ሰዓት ጊዜ በመቅደሱ አጠገብ ተንበርክካ ትጸልያለች ። አንድ ሰዓት ሲያልፍ ሌላ መነኩሲት ትተካታለች ። ኢሷንም ሦስተኛ መነኩሲት ትተካታለች ። እንዲሁ እንዲሁ እያሉ ስለሚፈራረቁ በማንኛውም ሰዓት አንዲት መነኩ ሲት በመቅደሱ አጠገብ ትገኛለች ማለት ነው ። ይህንን ሥርዓት «የማ ያቋርጥ ስግደት» ብለው ይጠሩታል ።

እነዚህ መነኩሲቶች የግላቸው የሆነ አንዳችም ነገር የላቸውም ። በዚህ ምክንያት ስለሚያስሩት ሻሽ ወይም ስለሚለብሱት ሸሚዝ ሲናገሩ እንኳ «ሻሻችን» «ሸሚዛችን» ይላሉ እንጂ «ሻሼ» ፣ «ሸሚዜ» አይሉም ።

በጥቃቅን ክፍሎች ውስጥ ይኖራሉ ። የክፍላቸውን በር ለመዝጋት ግን አይፈቀድላቸውም ። እርስ በእርሳቸው ሲገናኙ አንዷ መነኩሲት «በ መቅደስ ያለው ቅዱስ ቁርባን የተባረከና የተቀደሰ ይሁን» ስትል ሌላዋ መነኩሲት «ለዘለዓለም» ብላ ትመልሳለች ። የስሳምታ አሰጣጣቸው ይኸው ነው ።

በሕይወት እስካሉ ድረስ ገዳሙን ለቅቀው አይወጡም ። ሲሞቱ ግን አስክሬናቸው በገዳሙ ሲተበር ስለማይችል ወዶ ቫቲራር መካነ መቃብር ተወስዶ ይቀበራል ።

በሳምንት አንድ ቀን በእመምኔቷ ሰብሳቢነት ይሰበሰባሉ ። እመ ምኔቷን የሚመርጧት እነሱው ራሳቸው ናቸው ። እመምኔቷ ሦስት ዓመት በእልቅና ታገለግላለች ። እንደገና ልትመረጥ ትችላለች ። ነገር ግን ከዘ ጠኝ ዓመታት በላይ በእልቅና ልትቆይ አትችልም ።

ሰብሰባ በሚያደርጉበት ጊዜ እያንዳንዳቸው በሳምንቱ ውስጥ የፈጸ ሙትን ኃጢአት ተንበርክከው በገሃድ ይናዘዛሉ ። የተቀሩት በገዳዩ ተወ ያይተውበት የመሰላቸውን ቅጣት ይወስኑባታል ።

ወደ ገዳሙ እንግዳ ሲመጣ እንግዳውን የምታነጋግር እመምኔቷ ብቻ ነች ። የተቀሩት መነኩሲቶች አልፎ አልፎ ቤተሰባቸውን ካልሆነ

@OLDBOOKSPDF

በስተቀር ማንንም ለማነጋገር አይፈቀድላቸውም ። ለዚሁም ዘመድዮው ወንድ ከሆኑ ሊያነጋገሩት አይችሉም ።

መነኩሲቶቹ በከፍተኛ «ዲሲፕሊን» ሥር እንደሚኖሩ ሁሉ በገዳሙ ውስጥ በአዳሪነት የሚማሩት ልጃገረዶችም እንዲሁ ጥብቅ ቁጥጥር አለባ ቸው ። ሲንጫጩ ፣ ሲሳሳቁ ፣ ሲሯሯጡ የሚታዩት በዕረፍት ጊዜአቸው ብቻ ነው ።

ልጃገረዶቹ የድሎት ኑሮ አይኖሩም ። ምግባቸው እስከዚህም የሚ ጥም አይደለም ። ማብር ቤት ውስጥ ሲሆኑ ቀን ተራ ገብተው ከመሐከላ ቸው አንዲ መጽሐፍ ስታነብቡላቸው የተቀሩት በጸጥታ እየበሉ ያዳም ጪታል ።

ገና ቫልጣ ከገቨር ክትትል ሊማምለጥ ሲል ግድግዳ ቧጥጦ በጣራው አልፎ ከምድረግቢው የዘለቀበት ሥፍራ ይሽው ከመነኮን መቃብር የማይሻል ገዳም ነበር ። ከመንግሥተ ሰማያት የወረዱ የመሰሰው መንፈሳዊ ዜማ የመነኩሲቶቹ ዜማ ነበር ። ትልቅ አዳራሽ መስሎ የታየው ቤት ቤተ ክርስቲያኑ ነበር ። በዚያ ውስጥ አስከሬን መስላ ንጣፍ ድንጋይ ሳይ መስቀልያ ተነጥፋ የታየችው መንፈሳዊ ተጋድሎ በማድረግ ሳይ የነበረች መነኩሲት ነበረች ።

— 2 —

ያን ቀን ሴሊት ገን ቫልጣና ፎሽላቫ እሳት እየጮቱ ራታቸውን ቀማ ምስው ወይን ጠጃቸውን ካጣጣሙ በኋላ ጉዝጓዝ አንጥፈው ተኙ ። ገን ቫልጣ ዓይኑን ከመክደኑ በፊት «ከአሁን ወዲያ የምኖረው ከዚህ ሥፍራ ነው» ሲል ፎሽላቫ ሰማው ።

ሁለቱም በየአእምሮአቸው ሃሳብ ይዘው ስለነበረ በቀላሉ እንቅልፍ ለመተኛት አልቻሉም ።

«ከዚህ ብወጣ እነገቨር ያገኙኛል— ይይዙኛል ። ከዚህ የተሻለ መደበቂያ ሥፍራ ከቶም አላገኝም..... ገቨር ከዚህ መጥቶ ይይዘኛል ማለት ዘበት ነው.....» እያለ ሲያሰላስል ቆየ ገን ቫልጣ ። ለሱ መስለው እንጂ ይህ ገዳም ለማንኛውም ወንድ በጥብቅ የተከለከለ በመሆኑ እሱ ከዚያ ውስጥ መገኘቱ ቢታወቅ ከመታሠር ሊያድነው የሚችል ሁኔታ አልነበረም።

ፎሽላቫ በበኩሉ ይህንን ያውቅ ነበርና ፤ «ሙሴ ማድሌን ከዚህ ከተከለከለ በታ ሊገቡ እንዴት ቻሉ..... ሰዚሁም ሴት ልጅ ይዘው ለመሆኑ ከወዴት መጡ.....?» እያለ ሲያሰላስል ቆየ ።

@OLDBOOKSPDF

ፎሽልቫ በዚህ ገጸም ውስጥ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ስለኤም ሱር ኤም አንዳችም የሰማው ነገር አልነበረም ። በከተማው ስለሆነው ሁሉ አልሰማም ። ስለሆነም በእሱ ዓይን ማድሌን የድሮው የተከበረ ከን ቲባ ነበር ። ነገር ግን ከንግግሩ እንደተረዳው ምናልባት ማድሌን ከስሮ ይሆናል..... ባለዕዳዎቹም ተከታትለውት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አደረ በት ። ወይ ደሞ ቢፖሊቲካ ጉዳይ ተጠርጥሮ በመደበት ላይ ይሆናል ሲልም አሰበ። «ያም ሆነ ያም ሆነ ሙሴ ማድሌን ሕይወቴን ያዳኑልኝ ሰው ናቸው» አለ ፎሽላቫ በሃሳቡ ፤ «እሁን ደሞ እኔ ብድር የምመልስበት ዕድል አግኝ ቻለሁ ። ያኔ ጋሪዬ ተደፍቶብኝ ሳጣጥር ሳለሁ ሙሴ ማድሌን ሰሕይወታ ቸው ሳይሰስ እኔን ለማዳን ከጋሪው ሥር ጉበቱው ጋሪውን ወደ ላይ አን ስተው እንዳዳኑኝ ልረሳው አልችልም ።»

ቀጠለ ማነብነቡን ፤ «ሌሱስ ይሁን..... እኔን እንደረዱኝ በተራዬ ውሊታ ለመመለስ ዝግጁ ነኝ ። ነገር ግን..... የሚሆን እንኳ ኢይመስለኝም..... ብቻ..... በስርቆት ወንጀል የሚፈለጉ ቢሆንስ.....? ልረዳቸው ዝግጁ ነኝ ወይ? ነፍሰ ገዳይ ቢሆኑስ.....? እንዳልሁት የማይመስል ነገር ነው ። ግን ቢሆኑስ.....? ልረዳቸው ዝግጁ ነኝ ወይ? አዎን..... በምንም ነገር ቢፈለጉ ልረዳቸው ዝግጁ ነኝ» ሲል ወሰነ በሃሳቡ ።

ሴሊቱ ሊነጋጋ ሲል ፎሽለቫ ዓይኑን ከፍቶ ቢመለከት ግን ቫልጣ ከያረበት ተኝቶ ጉዝጓዝ ላይ ተቀምጦ አየው ። ከዚት ግን ገና ከእንቅልፉ አልነቃችም ።

ፎሽለቫም ከመኝታው ተነስቶ ቁጭ አለና ፤ «ሙሴ ማድሌን.....» አለው ፤ «ከሁሉ በፊት የምነግሮት አለኝ..... መጠንቀቅ ያሻል..... እርስዎም ሆኑ ልጅቷ ከዚህ ክፍል ወጭ እንዳትታዩ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋል..... አለዚያ ሁላችንም አለተልን ማለት ነው.....!»

«እወነት?»

«እወነት!» አለውና ቀጠለ ፎሽለቫ ፤ «ብቻ ጥሩ ጊዜ ነው የመጡት ሙሴ ማድሌን ። ወይንስ ክፉ ጊዜ ነው ልበ—ል? ለማንኛውም ከመነኩሲቶቹ አንደኛዋ በጠና ታምማለች ። ሌሎቹ መነኩሲቶች መላ ሃሳባቸውን በታመመቷ ላይ ስለጣሉ ሃሳባቸውን ወደኛ የሚመልሱ አይመስለኝም ። በአሁን ሰዓት እንኳ እየጸለዩላት ናቸው ። ስለዚህ ለዛሬ አንዳችም የሚያስፈራን ነገር አይኖርም ። የነገውን ግን አላወቅም.....!»

«ይህ ቦታ በጣም ሰዋራ ስለሆነ ማንም የሚያየኝ አይመስለኝም ።»

«መነኩሲቶቹ እንኳ ከዚህ ደርሰው አያውቁም ።»
«ሴላ ማን ሊመጣ ይችላል ታዲያ?»
«ልጃገረዶቹ ናቸዋ!»
«ልጃገረዶችም አሉ እንዴ?»

@OLDBOOKSPDF

ፎሽለሻ መልስ ሲሰጠው አፉን ሲከፍት የገዳሙ ደወል አንድ ጊዜ ብቻ ጂ አለ ።

«መነኩሲቷ ሞታለች..... ደወሉ የዚህ ምልክት ነው ።» አለው ፎሽለሻ ።

ከአንድ ደቂቃ በኋላ ደወሉ ለሁለተኛ ጊዜ ጂ አለ ።

«ደወሉ መደውሉን ይቀጥላል ሙሴ ማድሌን» አለው ፎሽላቫ ። «እስከ ሀያ አራት ሰዓት ድረስ በየደቂቃው ጂ ማለቱን ይቀጥላል ። ከሀያ አራት ሰዓት በኋላ የመነኩሲቷ አስከሬን ከቤተ ክርስቲያኑ ይወሰዳል» አለውና ሃሳቡን ቀደም ብለው ሲያወሩት ወደነበረው ጉዳይ አዙሮ ፤ «አዩ ሙሴ ማድሌን .....ልጃገረዶቹ በዕረፍት ሰዓታቸው ኳስ ይጫወታሉ ። ኳሳቸው ወደዚህ ተንከባልሎ ቢመጣ መልሰው ሊወስዱት ከዚህ መም ጣታቸው አይቀርም ። እንዚህ መላእክት የመሰሉ ልጃገረዶች ዋዛ አይ ምሰሉዎት » አለው ።

«ማን አልከኝ?»

«ልጃገረዶቹ ። የእርስዎን እዚህ መኖር በቀላሉ ሊያውቁ ይችላሉ ። ካዩዎትም 'እዚህ ወንድ አለ!' ብለው መጮሃቸው አይቀርም ። ለዛሬ እንኳ ምንም የሚያሰጋዎት ነገር የለም ። ሃሬ የጨዋታ ሰዓት አይኖራቸውም ። ቀኑ መሉ ጸሎት ነው ። ደውሉን ሰምተውታል..... አይደለም እንዴ፤ እና በየደቂቃው ጂ ሲል ውሉ ያድራል ።»

«ጎበዞኛል አባ ፎሽለሻ ። እዚህ ተማሪዎች አሉ ብለሽኛል» አለና በልቡ «ከዚች እዚህ ልትማር ትችላለች.....» ሲል አሰበ ።

«አዎ..... ልጃገረዶች አሉ ። ብቻ እርስዎን ያዩዎት እንደ ሆነ ቂ..... ቂ..... ብለው መጮሃቸው አይቀርም ። ይህ ጉዳም ሲወጉዎት በጥሩም የተከሰከሰ ነው ። እኔም በጉልበቴ ላይ ታጭዶ አስሬ የሞሀለረው እንዳይጠጣኝ ነው ።»

ሞን ቫልገር ከባሰ የሃሳብ ጥልቀት ውስጥ ገባ ። «ይህ ጉዳም ተስማሚ መደበቂያ ነው» ሲል በልቡ አሰበና ድምጹን ከፍ አድርጎ ፤ «ችግሩ ግን እዚህ መቆየቱ ነው» አለ ።

«ችግሩ እዚህ መቆየቱ አይደለም» አለው ፎሽለሻ ፤ «ችግሩ ከዚህ መወጣቱ ነው»

«መወጣት.....?»

«አዎን ሙሴ ማድሌን ። ወደዚህ ተመልሶ ለመግባት በመጀመሪያ ከዚህ መውጣት ያሻል ።»

የቤተክርስቲያኑ ደወል እንደገና ጂ አለኪል ጠበቀና ቀጠለ ፤ «ለመሆኑ በየት አድርገው ገቡ ሙሴ ማድሌን ? ከሰማይ ወርደው እንደሆነ እንጂ በወይት አድርገው እንደገቡ ለማወቅ ተስኖኛል ። መነኩ

@OLDBOOKSPDF

ሲቶቹ እንደሆኑ ማንኛውም ሰው በበር እንኚ በሌላ ዘዴ እንዲገባ አይ ፈቅዱለትም ።»

በዚህ ጊዜ ለየት ያለ የደወል ድምጽ ሰሙ ።

«እሻ!» አለ ፎሽለቫ ፣ «ይህ ደግ መንኩሲቶቹን የሚጠራ ደወል ነው..... ለስብሰባ ። ከመሐከላቸው አንዱ ስትሞት ሁልጊዜም ቢሆን ስብሰባ ይጠራሉ» አለና «ለማንኛውም ሙሴ ሚድሴን..... በገበቡት መንገድ ለመውጣት አይችሉም ወይ መቼም እንዴት አድርገው ሰመጣ ባት እንደቻሉ እንቆቅልሽ ሆኖብኛል ።»

የጣን ቫልጣ ፊት ጎረጣ ። በመጣበት የመወጣቱ ሃሳብ ተፈፈው ። የጣቪር ሰዎች እንደኋውሬ እንደሚያድኑት ያወቃል ። ጣቪርና ፖሊሱቹ አሱን ፍለጋ አካባቢውን ሲያስሱ በዓይኑ ሐሊናው ታየው ።

«በመጣህበት ለመወጣት አይቻለኝም አባ ፎሽለቫ ። ቅድም እን ዳልከው ከሰማይ ነው የመረድኩት ።»

«እሱንማ አልጠረጥርም! እግዚአብሐር ከመሬት አንስቶ ወደሰ ማይ አወጣቶዎት ፣ በደመብ ተመልከቶዎት ፣ ከዚያ በኋላ መልሶ ወደ ምድር ለቅቆዎት መሆን አለበት! ብቻ እንደመሰለኝ ወደታች ሲለቅዎት በወንዶች ጎዳም እንጂ በሌቶች ጎዳም እንዲያርፉ አልነበረም ። በስህ ተት ነው ከዚህ ያረፉት» አለና የበተከርስቲያኑ ደወል አውንም እንደገና ለወጥ ብሎ መደወሉን ሰምቶ ፣ «ይቸኛው ደግ ሌላ ምልክት ነው» አለው ፣ «ተሳሳኪው ወደ ማዘጋጀ በት ሐዲ አስክሬን መርማሪወን ሐኪም እንዲ ጠራ ምልክት መስጠቱ ነው ። ሐኪመን ለመጥራት የተቻኮሉ መሰለኝ» ብሎ ሃሳቡን እንደገና ወደ ዋናው ጉዳይ በመመለስ ፣ «ልጅቷ እስካሁን አልነቃችም እንዴ? ስመሦኑ ስሚ ማን ነወላ» ሲል ጠየቀው ።

«ከዜት ትባላለች ።»
«ልጅም ነች.....? ወይንስ ኢያቷ ነምትባ»
«ነች ።»

«አሷን ከዚህ ማስወጣት እስከዚህም አስቸጋሪ አይሆንም ሙሴ ሚድሴን ። የወይን ፍሬ የምይዝበት አንድ ቅርጫት አለኝ ። በወይን ፍሬ ፈንታ እሷን ቅርጫቱ ውስጥ አድርጌ ፣ በላይዋ ላይም አንዳች ነገር ጣል አድርጌባት በጀርባዬ ተሸክሚአት ብወጣ በረኛው የሚጠረጥረኝ አይመ ስለኝም ። ነገር ግን ትንፍሽ እንዳትል ያስፈልጋል ። ትንፍሽ እንዳትልም እርስዎ ያስጠነቅቋታል ። ከዚያ በኋላ ሰው ዘንድ ይዤአት እሔዳለሁ ። አንዲት ጆሮዋ የማይሰማላት ፣ የፍራፍሬ ሻጭ የሆነች ወዳጅ አለችኝ ። እሷ ዘንድ ይዤአት እሔዳለሁ ። እርስዎን ከዚያ ሆና ትጠበቅዎታለች ። ከዚያም በኋላ አብራችው ወደዚህ እንድትገቡ ዘዴ እፈልጋለሁ ። ብቻ..... እርስዎ ከዚህ እንዴት አድርገው ሊወጡ ይችላሉ ሙሴ ሚድሴን?»

@OLDBOOKSPDF

«ማንም እንዲያየኝ አልፈልግም አባ ፎሽፈሻ ። ቁም ነገሩ ከዚህ ላይ ነው ። እና እኔንም በድብቅ ለማስወጣት ዘዴ ፈልግ ።»

ፎሽለሻ መላ ጠፍቶት ጅሮውን ያክክ ጀመር ። ከዚያም በኋላ የደ ወሱን ዲዲታ እንደገና ሰማና ፤ «ሐኪሙ መጥቶ ፣ የመነኩሲቷን አስከሬን መርምሮ ፣ መሞቷን አረጋግጦ መሔዱ ነው» አለው ፎሽለሻ ፤ «ይህ ከተረ ጋገጠ በኃላ መንግሥት አንድ የሬሳ ሳጥን ይልካል ። ቀጥሎም መነኩ ሲቶቹ የማጅን አስከሬን ይገንዙታል ። አስከሬኑ ከተገነዘ በኋላ የኔ ሥራ ይቀጥላል ። የሬሳ ሳጥኑን ዘግቼ ምስማር እመታበታለሁ ። ከአጎክልቦ ኛነት ተግባሬ አንዱ ይኸው ነው ። ከዚያ በኋላ አስከሬኑ በቤተክርስቲያኑ ታችኛው አዳራሽ ይቆያል ። የሬሳ ሳጥኑን ከሚያመጡ ሠራተኞችና ከእኔ በስተቀር ከዚያ ሥፍራ የሚደርስ ሴላ ሰው የለም ። በመጨረሻም መን ግሥት የሚልካቸው ሠራተኞች መጥተው አስክሬኑን ይወስዱታል ።»

የጸሐይ ጨረር በክዜት ፊት ላይ አርፏል ። ክዜት አፏን ሳጉሽ ከፈት አድርጋ ተኝታለች ። ዣን ቫልጃ ፎሽለሻ የሚናገረውን መስማት ትቶ አተኩሮ ተመለከታት ።

ቀጠለ ፎሽለሻ ፤ «መቃብሩ የሚቆፈረው በሾዣራር መካነ መቃብር ነው ። የቆየና ያረጀ በመሆኑ ሳይዘጋ አይቀርም ይባላል ። መነኩሲቶቹ ሲሞቱ ግን አሁንም በሆን በሴሊት ተመስደው የሚቀበሩት ከዚያ ነው ። ግንኮ..... ከትናንት ጀምሮ ሰንት ነገር ደረሰ አማሆይ ክሩሲፈክስዮ አረፈች ..... ሙሴ ማድሌንም.....»

«ተቀብሯል» አለው ዣን ቫልጃ ተሽቀዳድሞ ።

«ለዘለቄታው እዚሁ የሚኖሩ ቢሆን ኖሮ በእርግጥም አንደተቀ በሩ በቆጠርሀት ነበር!»

ደወሉ አሁንም ዲ ዲ አለ ። ፎሽለሻ የደወሉን ድንጋ ጥርት አድርጎ ስሊያውቀው ቃጭሉን ከተንጠለጠለበት አውርዶ ጉልበቱ ላይ ያስ ረው ጀመር ። «አሁን የተደወለው እኔን ለመጥራት ነው» ሲል ገለጸለት ሲዝን ቫልጃ ፤ «አመምኔቷ ይፈልጉኛል ። ሙሴ ማድሌን..... ከዚህ ንቅ ንቅ ሳይሉ ይጠብቁኝ ። ከራበዎት ዳቦና አይብ እንዲሁም ወይን ጠጅ አለ ።»

ፎሽለሻ ይህንኑ ብሎ በእንካሣ እግሩ እየተጣደፈ ሲሔድ ዣን ቫልጃ ባለበት ሆኖ ተመለከተው ። አስር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከተጠራበት ቦታ ደርሶ በሩን አንኳኳው ። ጣቢያ ተባለ ። አመምኔቷ ሊጠብቁት ነበሩ ።

@OLDBOOKSPDF

አመምኔቷ ኢኖሳንስ ይባላሉ ። ፊታቸው ከብዶ ይታያል ።
ፎሽለቫ አንገቱን ቀለስ አድርጎ ሰላምታ ሰጣቸውና ከክፍሉ በር አጠገብ ቆመ ።

«አስጠርቼሃለሁ» አሉት ።
«መጣሁኮ እማሆይ» አላቸው ።
«አንድ የምነግርህ አለኝ ።»
«እኔም የምነግርሽ አለኝ እማሆይ ።»
«ኧ.....?»
«አንድ የምለምንሽ ነገር አለኝ ።»
«ግገረኛ!»

ፎሽለቫ ሥራውን በሚገባ ስለሚያከናውን መነኩሲቶቹ በእሱ ላይ እምነት አላቸው ። እሱን የሚተካ ደህና ሠራተኛ በቀላሉ ማግኘት እንደማይችሉም ይገምታሉ ።

ፎሽለቫ ልመናው ይፈጸምለት ዘንድ ስሏቸው ሁኔታ ለእመምኔቷ በዝርዝር ያስረዳቸው ጀመር ። ስለዕድሜው ፣ ስለሕመሙ ፣ ሥራው እየከበደ ስለመሔዱ ፣ የእጅከለቱ ዐቃ በጣም ሰፌ ስለመሆኑ ፣ እየሩ ሲቀዘቅዝ ሐሳቡን በኬሻ መሸፈን እንዳስቸገረ ፣ ይህንና የመሳሰለውን ፣ በሰፈው ከዘረዘረላቸው በኋላ «እና አንድ ወንድም አለኝ» ሲል ቀጠለ ፣ «በዕድሜ ገፋ ያለ ነው ። እና ቢፈቱድልኝ ይህ ወንድሜ እዚህ መጥቶ ሥራ ሊያግዘኝ ይችላል ። ከኔ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ስለሚችል ተፈልጎ የማይገኝ ዓይነት አትክልተኛ ነው ። እሱ መጥቶ እንዲያግዘኝ ካልተፈቀደልኝ በስተቀር በጤናዬ ምክንያት ሥራዬን ለቅቄ መሔድ ይኖርብኛል ። መጥቶ እንዲያግዘኝ ከተፈቀደልኝ ግን ሴት ልጁን ሜምር ይዞ ይመጣል ። ሴት ልጁ ትንሽ ልጅ ነች ። በመንፈሳዊ ትምህርት አየተ ክብካቤች ለማደግ የምትችል ነች ። ግን ያው ቃል! ምናልባት አንድ ቀን አሏም መነኩሲት የመሆን ዕድል ታገኝ ይሆናል እማሆይ ።»

እመምኔቷ በዝምታ ካዳመጡት በኋላ መቁጠሪያቸውን በጣትና በጣታቸው መሐከል እያጥለሰለሱ ፣ «እሰቲ ጠንከር ያለ የብረት ዘንግ ፈልግልኝ » አሉት ለልመናው መልስ በመስጠት ፈንታ ።

«ለምን የሚሆን እማሆይ?»
«አንደ ግንባሽ የሚያገለግል የብረት ዘንግ ።»
«አሽ እማሆይ.....አፈልጋለሁ ።»

እመምኔቷ ሴላ ቃል ሳይተነፍሱ ፎሽለቫን እዘያው ትተውት ቀጥሎ ወዳለው የስብሰባ አዳራሽ አመሩ ።

@OLDBOOKSPDF

ሩብ ሰዓት ካለፈ በኋላ እመምኒቷ ተመልሰው መጥተው መንበራቸው ላይ ቁጭ አሉ ።

«አባ ፎቫ.....» አሉት ። መነኩሲቶቹ ፎቨለቫን «ፎቫ» ብለው ባጭሩ ነው የሚጠሩት ።»

«አቤት እማሆይ»
«በተክርስቲያኑ ውስጥ ያለውን ፤ ዜማ የሚዜምበትን ቦታ ታውቀው የለ?»

«ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ አይቼዋለሁ እማሆይ ።»
«በዚያ አካባቢ መነሳት ያለበት አንድ ድንጋይ አለ ።»
«ድንጋይ.....?»
«አዎ ። ከመቅደሱ አጠገብ ያለው ጎላጭ ድንጋይ ።»
«የሞሻው ከዳን?»
«አዎን ።»
«አሁኑ ከባድ ነው እማሆይ ። አስሩ ሰማንሰት ሁለት ሰው..... ሁለት መንድ ያሻዋል ።

«እማሆይ አሳስቢዮ ያማሁላል ። አሳቻው ከመንድ ያላነሰ ጉልበተ አሳቸው ።»

«ሴት ምንም ጉልበተኛ ብትሆን ከመንድ አሁል ሉትሆን አትችል እማሆይ ። መንድ አጋሽ ነው የሚያስፈልገኝ ።»

«ከዚህ ቦታ ሴት አንቺ የሚያግዝህ ወንድ የለም ። እማሆይ አሳንሲዮ ያማሁላል ። ግንኛውም ሰው የአትመጣ ያህል ከፈጻ ከዚያ በላይ አይፈለ ግበትም ።»

«አሁን እወነት ነው ።»
«ዜና ማንሻ ታግኛለህ?»
«አፈልጋለሁ እማሆይ ።»

«ጎላጭ ድንጋዩ ላይ ቀለበት አለበት..... ለማንሳት አንዲያመች ታስቦ የተሠራ»

«ዋሻው ከተከፈተ በኋላስ?»
«ከተከፈተ በኋላማ ተመልሶ ይዘጋል ።»
«በታ ይዝው ነወ?»
«አይደለም ።»
«ምን እንደሚደረግ ይዘሙኛ እማሆይ ።»
«አየህ ፎቫ..... በእንተ ላይ እምነት አለኝ ።»

@OLDBOOKSPDF

«ያዘዙኝን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ እማሆይ ።»
«እና ለማንም አንዳትናገር ያሻል ። ዋሻውን ከከፈትከው በኋላ ከዚያ ውስጥ የምትጨምረው ነገር አለ ።»

«ምን እንደሆነ ቢነግሩኝ እማሆይ.....»

«አየህ.....ዛሬ ጠዋት እማሆይ ከሩሲፊክሲዮ አርፈዋል ። አስከሬናቸው ከቤተክርስቲያኑ ገቦ ወዳለው የሙታን ክፍል ተወስዷል ። ካለአንተ በስተቀር ማንም ወንድ ከዚያ ክፍል ለመግባት አይፈቀድለትም ። ይህንን ልብ አድርግ ። ከሙታን ክፍል ሌላ ወንድ ይገባና.....! የማይሆን ነው! እማሆይ ከሩሲፊክሲዮ በሕይወት ሳሉ ብዙ ሰዎች ወደ እውነተኛው ኃይማኖት እንዲመለሱ አድርገዋል ። ከሞቱም በኋላ ተዓምር ይሠሩ ይሆናል ። ማን ያውቃል!»

«ይሠሩ ይሆናል!»
«የእማሆይ ከሩሲፊክሲዮ አሟሟት ያማረ ሆኗል ለማለት እችላለሁ ። ሕይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ ጎሊናቸውን ሳይስቱ ቆይተዋል ። እኛን አኑጋግረውናል ። የመጨረሻ ኑዛዜአቸውንም አሰምተውናል ። እማሆይ ከሩሲፊክሲዮ የተቀደሱ መንክሲት ነበሩ ።»

«አዎ..... እንደርስዎ የተቀደሱ እማሆይ ።»

«ባለፉት ሀያ ዓመታት በፊሳ ሳጥን ውስጥ እንጂ በሌላ ተኝተው አያውቁም ። አሁንም በዚያው ሳጥን ይቀበራሉ አባ ፎሻ ።»

«ይገባል እማሆይ ።»

«እና አስከሬናቸውን ወደ ውስጥ በምታሰገባበት ጊዜ አራት እማሆዮች ይረዱሃል ።»

«ከምን ውስጥ?»
«ከዋሻው ውስጥ ።»
«የትኛው ዋሻ?»
«ከመቅደሱ ሥር ካለው ዋሻ ።»
ፎሽለሻ በዚህ ጊዜ ደንግጥ አለ ።
«ከመቅደሱ ሥር ካለው ዋሻ ነው ያሉኝ እማሆይ?»
«አዎን።»
«ነገር ግን .....»
«የብረት በንግ ፈልግ ብዬሃለሁ ።»
«አዎን ብለውኛል ። ብቻ.....»

«የብረት በንጉን ካመጣህ በኋላ በቀለበቱ ውስጥ አስገብተህ ድንጋዩን ፈንቅለህ ታነሳዋለህ ።»

«ብቻ.....»

@OLDBOOKSPDF

«የሙታን ኑዛዜ መፈጸም አለበት አባ ፎሻ ። እማሆይ ክሩሲፊክሲዮ በሕይወት ሳሉ በመቅደሱ ሥር ባለው የተቀደሰ ዋሻ ውስጥ እንዲቀበሩ ተናዝዘዋል ። »

«ግንኮ ክልክል ነው እማሆይ ።»

«በሰዎች ዘንድ ክልክል ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ክልክል አይደለም ።»

«ወሬው የተሰማ እንደሆነስ እማሆይ?»

«ስለዚህ ጉዳይ እንዳችም ቃል እንደማትተነፍስ ተስሩ አለኝ አባ ፎሻ ። በአንተ ላይ እምነት አለኝ ።»

«እኔማ ምን ቆርጠኝ እማሆይ!»

«ጥባዔ ጠርተን ተነጋግረንበታል ። ከሰምምነትም ደርሰናል ። እማሆይ ክሩሲፊክሲዮ በፈቀዱት ቦታ ፡ ለሀያ ዓመታት ይተኙበት በነበረ የሬሳ ሳጥን እንዲቀበሩ ወስነናል ።»

«እሱስ ይሁን እማሆይ ። ነገር ግን የጨና ጥቢቃው ክፍል ወይም የፖሊሱ ክፍል አለዚያም ማዘጋጃ ቤቱ ቢሰማ ....?»

«በኑዛዜአቸው መሠረት መፈጸም አለበት አባ ፎሻ ። ደግም በአንተ ላይ እምነት አለን ።»

«እሺ ይሁን እማሆይ ። ታማኝ ነኝ ። ጥዱም ታማኝ ።»

«የሬሳ ሳጥኑን ዘግተህ ምስማር ትመታበታለህ ። እማሆየኙ ተሸክመው ወደ ቤተክርስቲያኑ ይወስዱታል ። ከዚያ በኋላ የሙታን ጸሎት ይደረጋል ። ቀጥሎም እኛ ወደየክፍላችን እንመለሳለን ። ከምሽቱ አምስት ሰዓት እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የብረት ዘንጉን ይዘህ ትመጣለህ ። የሚደረገው ሁሉ በምስጢር መሆን አለበት ።»

«ማንሻው ዘግማ ቢያንስ ስድስት ጫማ ርዝመት እንዲኖረው ያሻል እማሆይ ።»

«እና ከየት ታመጣዋለህ?»

«ከአትክልቱ ቦታ አላጣም ።»

«ከሰዓቲቱ ስድስት ሰዓት ከመሆኑ በፊት እንድታመጣው ያሻል ። ይህንን እንዳትዘነጋ ።»

@OLDBOOKSPDF

«አማሆይ.....»

«አቡሃ»

«ከእሁን ወዲያ የዚህ ዓይነት ሥራ የሚሠራ ሰው ካስፈለገዎት ከሠንደሚ የተሻለ ሰው ኩቶም አያገኙም ።»

«ሥራውን በተቻለ ፍጥነት እንድታከናውነው አባ ፎቫ ።»

«ላፋጥነው አልችልም አማሆይ ። ጤነኛ ሰው አይደለሁም ። ደሞም እንከሳለሁ ። ለዚህ ነው ረዳት ያሻኛል የምለው ።»

«ምንከስ ኃጢአት አይደለም ። እንዲያውም ጽድቅ ሳይሆን ይቀርና ለማንኛውም ሥራው ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት በፊት መጠናቀቅ አለበት ።»

«ዮተቻለኝን አደርጋለሁ አማሆይ ። የሬሳ ሳጥኑን ዘግቼ ምስማር እመታበታለሁ ። በአምስት ሰዓት ማንሻወን ሆነን ይገር እመጣለሁ ። ከተመደቡት አማሆዮች ጋር ዋሻውን ከፍተን አስክሬኑን እዚያ ውስጥ እንጨምረዋለን ። ዋሻውን መልሰን እንዘጋዋለን ። የሬለጉት ይሽው ነው አማሆይ..... አይደለም እንዴ?»

«ይህ ብቻ አይደለም ።»

«እና ምን ተረፈ»

«ሴሴው የሬሳ ሳጥን አለ..... ከመንግሥት የሚላክው ።»

«እሱ ምን ያረጋል አማሆይ?»

«መቀበር አለበት ።»

«ባዶውን?»

«አዎን ። ነገር ግን የሬሳ ሳጥኑን አንስተው ከሬሳ ማጓጓዣ መኪና ውስጥ የሚያደርጉትና ከዚያም አውርደው የሚቀብሩት ሠራተኞች ሳጥኑ ባዶ መሆኑን እንዳያውቁ ያሻል ።»

«እንግዲያውስ አፈር አሞላዋለሁ አማሆይ ። አፈር ከሞላሁት ያስክሬኑ ያህል ይከብዳል ።»

«ጥሩ ሃሳብ! ሰውና አፈር ያው ናቸው አሉና አስናበቱት ። ፎቫ ለሻም ለመውጣት ወደ በሩ ሲሔድ እመምኔቷ ድምጻቸውን ትንሽ ከፍ አድርገው ፡ «መልካም ነው አባ ፎቫ..... ነገ ከቀብሩ ሥነ ሥርዓት በኋላ ወንድምሃን እዴ ዘንድ ይዘኸው ና..... ልጅንም እንዲያመጣት ንገረው» አሉት ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚች ከእንቅልፏ ነቅታ ጣን ቫልጣ የሚያስጠነቅቃትን በጥሞና ሰታዳምጠው ነበረች ። «ስሚኝ የኔዋ ከዚች..... ያ ቅርጫት ይታይሽል.....? አባ ፎሽለቫ በዚያ ቅርጫት ውስጥ አዝሎ ያወጣሽና ከአጎዲት ሴትዮ ቤት ያስቀምጥሻል ። እዚያ በምትቆይበት ጊዜ የተባልሽውን ሁሉ እሺ ብለሽ ፥ ታዛዥ ሆነሽ መፈጸም ይኖርብሻል ። ከዚያ በኋላ እኔ መጥቼ እወስድሽና ተመልሰን እዚሁ እንመጣለን ። ገባሽ?»

«ገባኝ አባዬ» ስትለው ፎሽለቫ ከነበረበት መጥቶ በሩን ከፍቶ ገባ ። ጣን ቫልጣም ፊቱን ወደሱ አዙሮ «አና.....?» ሲል ጠየቀው ።

«ነገራችን ስምሯል ። ይዝዎት እንድመጣ ተፈቅዶልኛል ። ብቻ ሙሴ ማድሌን.....በምን ዘዴ ከዚህ ሊወጡ እንደሚችሉ ቸግሮኛል» አለው ። ቀጥሎም ወንድም አለኝ ብሎ ለአመምኔቷ መናገሩን ፥ ወንድሙ ሴት ልጅ እንዳለው ፥ ወንድሙ ከእሱ ጋር አየኖረ ሥራ እንዳያገዘው መጠየቁን ፥ ወንድም የተባለው ጣን ቫልጣ ራሱ መሆኑን ፥ ሴት ልጁ የተባለችው ከዚች መሆኗን ፥ ሚጅ መነኩሲት ለሀያ ዓመታት በተኙበት ሳጥን ፥ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ባለው ዋሻ ውስጥ እንድትቀበር መናዘዟን ፥ በሕግ የተከለከለ መሆኑን ፥ የእሷ ጉዞ ግን መከበር ያለበት መሆኑን፤ ሌላ የሬሳ ሳጥን መኖሩንና ይህ የሬሳ ሳጥን ከቫገሪራር መካነ መቃብር ተወስዶ የሚቀበር መሆኑን ፥ በዝርዝር አጫወተው ።

«ሌላው የሬሳ ሳጥን ስትል ምን ማለትህ ነው፧ ሲል ጠየቀው ጣን ቫልጣ ።

«መንግሥት የሚልከው የሬሳ ሳጥን ነዋ!»
«መንግሥት የሚልከው.....? አልገባኝም ።»

«አየህ ሙሴ ማድሌን..... አንዲት መነኩሲት ስትሞት የማዘጋጇ ቤቱ ሐኪም, መጥቶ ሬሳዋን መረምር መሞቷን ከረጋገጠ በኋላ መንግሥት የሬሳ ሳጥን ይልክል ። ይህ በሆነም ማግሥት መንግሥት የሬሳ ማጓጓዣና ሠራተኞች ልኮ አስከሬኑን ወደ መካነ መቃብር እንዲወስዱት ያዝዛል ። እሁን ታዲያ ሠራተኞቹ መጥተው የሬሳ ሳጥኑን ማጓጓዣው ላይ ሲያወጡት ባዶ መሆኑን ቢያውቁ.....»

«ለምን ባዶ ይሆናል?»
«ሌላ አስከሬን የለማ!»
«ሕያው ሰው ለምን አትጨምርበትም!»
«ከወዴት ላምጣ?»
«እኔ አለሁ አይዶለም እንዴ?»
ፎሽለቫ ይህንን ሲሰማ ደንግጥ አለ ።

@OLDBOOKSPDF

«አርስዎ.....!»
«አዎ..... እሬን እዚያ ውስጥ ለምን አትጨምረኝም!»
«አባክዎን አይቀልዱ!»
«መች ቀለድሁ.....! ከዚህ ቦታ በድብቅ መወጣት እንዳለብኝ ረሳ ኸው እንዴ!»
«እሱንስ አልረሳሁም!»
«ለመሆኑ ሳጥኑ የት ነወሳ»
«እታች ነው..... አስከሬን ከሚቀመጥበት ክፍል» ።
«ማታ ሰው ሁሉ ሲተኛ ከዚያ ክፍል ወስደህ ልትደብቀኝ አት ችልም!»

«ከሬሳ መርማሪው ሐኪምና ከእኔ በስተቀር ማንም ሰው ከዚያ እንዳይገባ ከለከል ነው ። ነገር ግን ከሱ አጠገብ ለቀብር ሥነ ሥርዓት የምገለገልባቸውን መሣሪያዎች የሚስቀምጥበት ሌላ ክፍል አለ ። ቁልፉም በእጄ ይገኛል ።»
«ነገ የሬሳ ማጓጓዣው የሚመጣው በስንት ሰዓት ነው ለመሆኑ?»

«ከሰዓት በኋላ..... በግምት በ፱ ሰዓት ። የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ጊዜው ከመምሸቱ በፊት መፈጸም አለበት ።»
«እንዴት ከሆነ ዛሬ ሌሊትና ነገ ማጓጓዣው እስኪመጣ ድረስ በአል ከው ቦታ ቁጭቤ ብቀይ ይሻላል ። ብዙ ይርበኝ ይሆናል ። ምግብ እንዴት ላገኝ እችላለሁ?»

«የሚበላ ነገር እኔ አመጣልዎታለሁ ።»
«እና ነገ በስምንት ሰዓት መጥተህ እሬሳ ሳጥኑ ውስጥ አስገብተኸኝ፣ ክዳኑን በላዬ ላይ አድርገህ ምስማር ትመታበታለህ!»

ፎሽለሻ ጉዳዩ አልዋጥ ብሎት ጫንዴት ይታሳል.....? ይሽንን ማድረግ እንዴት ይታሳል ሙሴ ማድሴን!» ሲል ጠየቀው ።

«ምኑ ነው የማይታለጠግ የሬሳ ሳጥኑን ከድነህ ምስማር ትመታበታለህ ። አሉት..... ይሽው ነው»

ግን ቫልሆ ጉዳዩን በጣም አቅሎ ነው ያየው ። በሕይወቱ በጣም ስለተሰቃየና እስር ቤት በነበረበትም ወቅት ከዚያ አምልጦ ለመውጣት ያልሞከረው ዘዴ ስላለነበረ ሬሳ ሳጥን ውስጥ ተኝቶበት የመጓዝን ሃሳብ እስከዚህም አላሰጨነቀውም ። ለማምለጥ የቆረጠ ሰው ለደቂቃው የማይታለው መስናክል የለምና ።

«ግንኮ..... እንዴት አድርገው ይተነፍሳሉ ሙሴ ማድሴን?»

«ምን ችግር አለወሳ መብሻ ካለህ የላጥኑን ክዳን እዚህም እዚያም ትብሳሳዋለህ ። ደሞም ክዳኑን ምስማር በምትመታበት ጊዜ ያለልክ ኩታ ጥለቀው ። በዚህ ዘዴ አየር ለማግኘት እችላለሁ ።»

@OLDBOOKSPDF

«አቡስ ይሁን ። ብቻ..... ድንገት በያስነጥሶትስ.....? ወይም ደሞ ቢያ ስሎት.....?»

«ለማምለጥ የፈለገ ሰው አያስነጥሰውም! አያስለወምም! ይልቁንስ የሚያሳስበኝ ነገር ካለ በመቃብሩ ቦታ የሚኖረው ሁኔታ ነው ።»

«አቡ እንኳ ምንም የሚያሳስብ አይደለም ። ጉድጓድ ቆፋሪውን አውቀዋለሁ ። እንዲያውም ወዳጄ ነው ። ሽማግሌ..... የጥንት ሰው! እና እዚያ የሚሆነውን በቅድሚያ ልነግሮት እችላለሁ ። የመካነ መቃብሩ በር ከመዘጋቱ አርባ አምስት ደቂቃ በፊት ማጓጓጥውና ሽኝዎቹ ከዚያ ይደርሳሉ ። እኔም ከዚያ እገኛለሁ ፣ ተግባሬ ነውና ። መዶሻ ፣ መሮና መቆ ንጠጫ መሣርያ ይገዜ አሐዳለሁ ። ማጓጓጥው ከመቃብሩ አፍ ሲደርስ ሠራ ተኞቹ በራሳ ሳጥኑ ዙርያ ገመድ ያስሩበትና ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ያወርዱ ታል ። አብረው የሚመጡት ካህን ጸሎት አድርገው ፣ በራክ ሰጥተው ፣ ጠበል ረጭተው ወደመጡበት ይመለሳሉ ። የማዘጋጃ ቤቱ ሠራተኞችም ግዳጃቸው አስከሬኑን ጉድጓድ ውስጥ አስከመጨመር ድረስ ስለሆነ ከዚያ በኋላ ወደመጡበት ይመለሳሉ ። ከዚያ የምንቀረው ጉድጓድ ቆፋ ሪውና እኔ ብቻ ነን ። ጉድጓድ ቆፋሪው ሜስቲዬን ይባላል ። ወዳጄ ነው ብዬዎታለሁ ። መጠጥ ይወዳል ። በዚያን ወቅት ሰክሮ አገኘው ይሆናል ። በደሀና ጊዜው ከሆነም 'የመቃብሩ አፈር ከመመለሱ በፊት ትንሽ ጉን ጨት እንበል' ብዬው ይገርው አሐዳለሁ ። ሲመለከረ ረጅም ጊዜ የሚ ያስፈልገው ሰው አይደለም ። ሲሰክር እዚያው ትቼው ወደመካነ መቃብሩ ተመልሼ ሳጥኑን ከፍቼ እስወጣዎታለሁ ። በቅድሚያ ሰክሮ ካገኘሁት ደሞ «በል ሂድና እረፍ..... አራሩን እኔ እመልሰዋለሁ» ብዬ እርስዎን ከሳ ጥኑ አወጣዎታለሁ ። ከዚህ በላይ ችግር የለውም ።»

«ጨብጠኝ!» አለው ጣን ቫልጣ በጣም ደስ ብሎት ። ፎሽለቫም በጠውና «ቢቃ.....! ሁሉም ነገር ተሳካ ማለት ነው!» አለው ።

«መሳካት አለበት! አለዚያማ.....!»

— 6 —

በማግሥቱ ምሽት አካባቢ ላይ የሬሳ ማጓጓጥው ወደ ሽገርራር መካነ መቃብር ያዘግም ጀመር ። የማዘጋጃ ቤቱ ሠራተኞች በማጓጓጥው ግራና ቀኝ ሆነው ይራመዳሉ ። ካህኑና የካህኑ ረዳት የሆነ ልጅ ጋሪ ላይ ሆነው ከኋላ ይከተላሉ ። ፎሽለቫም የቀን ሙያተኛ ልብስ ለብሶ ፣ መሣ ሪያዎቹን ይዞ ከበስተኋላ ሆኖ ቀና ደፋ ይላል ።

በዚያን ጊዜ የፓሪስ መካነ መቃብሮች ጸሐይ ስትጠልቅ ይዘጉ ነበር ። መቃብር ቆፋሪው ከዚያ በፊት ከመካነ መቃብሩ መውጣት ነበረበት ።

@OLDBOOKSPDF

በሆነ ምክንያት በስዓቱ ሳይወጣ ቢቀር ግን ሌላ የመውጫ ዘዴ ነበረው ። ወደበሩ ሔዶ ለበረኛው የመታወቂያ ወረቀቱን ያሳያል ። በረኛውም ያስ ወጣዋል ። መቃብር ቆፋሪው የመታወቂያ ወረቀቱን ሳይዝ ቢገኝ ግን በረኛው የ15 ፍራንክ መቀጫ ያስከፍለው ነበር ። ይሽወም የዘመኑ ደም ብና ሥርዓት ነበር ።

የፌሳ ማጓጓዣው ወደመካነ መቃብሩ በሚያዘግምበት ጊዜ የፎሽ ለቫ ፊት በራ ብሎ ይታይ ነበር ። አሱና ዣን ቫልዣ ያወጡት እቅድ አን ዳችም መሰናክል አላገኘውም ። በተነጋገሩት መሠረት ከዜትን በቅርጫ ቱ ውስጥ አድርጎ ፣ በጀርባው አዝሎ አወጥቶ ለፍራፍሬ ሻጪ ሴት አስረ ክባት ። ዣን ቫልዣም ድምጹን አጥፍቶ በሬሳ ሳጥኑ ውስጥ ሆኖ በመጓጓዝ ላይ ነበር ።

ማጓጓዣው ከመካነ መቃብሩ መግቢያ በር ሲደርስ ቆም አለ ። ከማዘጋጃ ቤቱ ሠራተኞች አንደኛው ወደ በረኛው ሐድ ብሎ አስክሬን ለመቅበር መምጣታቸውን ተናግሮ እንዲገቡ እንዲፈቀድላቸው ጠየቀው ። ይህም የዘመኑ ደምብና ሥርዓት ነበር ።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ማንኑቱ ያልታወቀ አንድ ሰውዬ ከመጓጓዣው በስተጀርባ መጥቶ ከፎሽለቫ አጠገብ ቆመ ። ሰውዬው የቀን መያተኛ ይመስላል ። ጥብቆ ለብሷል ደማ ተሸክሚል ።

ያልጠበቀው ሰው በመሆኑ በዓይኑ ቃኘወና «ማነህ አንተ?» ሲል ጠየቀው ፎሽለቫ ።

«አኔ.....? አኔማ መቃብር ቆፋሪው ነኝ» ሲል መለሰለት ሰውዬው ።

የፎሽለቫ ፊት በድንገት ልውጥወጥ አለ ፣ ውስጣዊ ስሜቱ ተና ጋበት ።

«መቃብር ቆፋሪው ነ—ኝ?»
«አዎን ። መቃብር ቆፋሪው ነኝ ።»
«አንተ ?»
«አዎን እኔ ።»
«መቃብር ቆፋሪው ሚስቲዬን እንጂ እንተ ኤይደለህም..... ከዚህ በፊት አይቼህም አላወቅ ።»
«አሱማ ነበር ።»
«ነበ——ርን»
«አሱት ሞቷል ።»

ፎሽለቫ የባሰውን ክው አለ ። የሚናገረው ጠፍቶት ትንሽ ከቆየ በኋላ «ሊሆን ኤይችልም!» አለው ።

@OLDBOOKSPDF

ሠሆኗል እንጂ!»

«ሊሆን አይችልም ብዬ‌ገለሁ ሰውዬ!»

«እኔ ደሞ ሆኗል ነው የምልህ በሱ ፈንታ እኔ ተተክቻለሁ ። ግሪ ቢዩ እባላለሁ ።»

ፎሽለቫ ግሪቢዬን አጥብቆ ተመለከተው ። «ወየ ጉድ! ስንት ያል ታስበ ነገር ይደርሳል! እና ሽማግሌው ሜስቶዬን ሞቷል ነው የምትሰኝ! ምንኛ የሚያሳዝን ዜና ነው! ሜስቲዬን በጣም ደግ ሰው ነበር ። እንተም ደግ ሰው እንደሆንክ ተስፋ አለኝ ። ደግ ሰው ከሆንክ ከአንድ ቦታ ጉራ ብለን ጉንጨት ብንል ደስ ይለኛል» አለው ።

«እኔ መጠጥ አልወድም» ሲለው ግንጓጉጦው እንደገና መንቀሳቀስ ጀመረ ። ግሪቢዬና ፎሽለቫም ቀረት ብለው ተከተሉት ።

«ስማኝ መዳጀ.....» አለው ፎሽለቫ ፣ « እኔም እንዳንተው መቃብር ቆፋሪ ኑኝ..... የገዳሙ መቃብር ቆፋሪ ።»

«ተመሳሳይ ሥራ እንሠራለን ማለት ነዋ!»

«ነው ። እናም እኔና እንተ ብንተዋወቅ መልክም አይመስልህም?»

«ይሽው ተዋውቀናልኮ!»

«አብረው ሳይጠጡ በሚገባ መተዋወቅ የት አለና! ካንድ ቦታ ጉራ ብለን ጉንጨት እንበል ብዬሃለሁ ። እምቢ አሻፈኝ ።»

«ከሁሉም ነገር ግዳጅ መቅደም አለበት ። ደሞም የሰባት ልጆች አባት ኑኝ ። ታዲያ ልጆቼን ላሳድግ ወይንስ ጠጪ ልሁን ?»

የፈሳ ማጓጓጎው ከዋናው መንገድ ተገንጥሎ በጠባብ መንገድ ይጓዝ ጀመር ። ጉድጓዱ ከኮቆፈረበት ሥፍራ ለመድረስ ምንም ያህል አልተረፈውም ነበር ።

«ጥሩ ወይን ጠጅ ካለበት ነው አንሒድ የምልህ» አለው ፎሽለቫ ።

«እኔኮ ሎሚሽም ቢሆን የተማርኩ ሰው ኑኝ» አለው ግሪቢዬ ፣ «አስከ አራተኛ ክፍል ድረስ ተምሬአለሁ ። አባቴ እንዲያውም ሥነ ጽሑፍ እንድ ማርለት ፈቃዱ ነበር ። ነገር ግን ሳይሆን ቀረ ። የሆነ ሆኖ ደራሲ ስመሆን ባልበቃም የሕዝብ ዶክዳቤ ጸሐፊ ስመሆን በቅቻለሁ ።»

«እንጂስ ከሆነ መቃብር ቆፋሪ አይደለህማ! »

«መቃብር ቆፋሪ መሆን የሕዝብ ዶክዳቤ ጸሐፊ ከመሆን አያግድም ። የሕዝብ ዶክዳቤ ጸሐፊ መሆንም መቃብር ቆፋሪ ከመሆን አያግድም»

«ለማንኛውም አብረን ብንጠጣ ይበልጥ እንተዋወቃለን እንጂ ጉዳት የለበትም ።»

@OLDBOOKSPDF

ፎሽለቫ አብረን እንጠጣ አለው እንጂ ሂሳቡን ማን እንደሚከፍል አልገለጸለትም ። በተለምዶ ከሜስቲዬን ጋር አብረው በሚጠጡበት ወቅት እንጠጣ ብሎ ሃሳብ የሚያቀርበው ፎሽለቫ ፣ ሂሳብ ከፋዩ ግን ሜስቲዬን ነበር ።

«ሰውነ ለመናር መብላት አለበት» አለው ግሪቢዬ ፤ ዉለዚህም ብዬ ሁለት ዓይነት ሥራ እሠራለሁ ። ጠዋት ጠዋት የሕዝብ ደብዳቤ እጽፋለሁ ። ከሰዓት በኋላም መቃብር አቆፍራለሁ ። መተዳደርያዬ ይኸው ነው ።»

የሬሳ ማጓጓጓው ገፍቶ ሔዶ ከመቃብሩ ሥፍራ ደረሰ ። ፎሽለቫ ከከባድ ስጋት ላይ ወደቀ ። ክፉኛም አላበው ። «ምን ባደርግ ይሻለኛል!» ሲልም አሰበ ፤ ጭንቅ ብሎት ።

— 7 —

ገን ቫልዣ ሳጥኑ ውስጥ ሆኖ ፣ እንደአስከሬን ጸጥ ብሎ የሚሆነውን ሁሉ በስሜቱና በጆሮው ሲከታተል ነበር ። የማዘጋጃ ቤቱ ሠራተኞች ከአስከሬን ማቆያው ክፍል እንስተው፣ ማንጓጓጓው ላይ ሲጭኑት ፣ ማንጓጓጓው ከመካነ መቃብሩ በር ደርሶ ቆም ሲል ፣ እንደገና ተንቀሳቅሶ ሔዶ ከመቃብሩ ቦታ ደርሶ ቆም ሲል ፣ ቀጥሎም ሠራተኞቹ ሳጥኑ ላይ ገመድ ሲያስሩበት ፣ አስረውም ከመንጓጓጓው እንስተው ጉድጓድ ውስጥ ሲጨምሩት ፣ ይህንን ሁሉ አወቀል ። ከዚያ በኋላ ግን ጭንቅላቱ ዞረበት ። ይኸም የሆነው ሳጥኑን ጉድጓድ ውስጥ ሲጨምሩት እግሩን በማስቀደም ፊንታ ዘቅዝቀው ጫንቅላቱን በማስቀደማቸው ምክንያት ነበር ። ሳጥኑን አስተካክለው ክስቀመጡት በኋላ ግን ጭንቅላቱ ደህና ሆነለት ። ቀጥሎም ካህኑና ረዳቱ ልጅ በላቲን ቋንቋ ጸሎት ሲያደርጉለት ሰማቸው ። ሳጥኑ ላይ ጠበል ሲረጩበትም ፤ «ከአሁን ወዲያ ሳጥኑ ውስጥ ብዙ አለቆይም..... ቂሱ ሥርዓተ ቀብሩን ፈጽመው ይሔዳሉ..... ፎሽለቫም ሜስቲዬንን ሊያጠጣው ይዘት ይሔዳል..... ካስከረው በኋላ ብቻውን መጥቶ ሳጥኑን ከፍቶልኝ እወጣለሁ..... ይህ ሁሉ ከአንድ ሰዓት በላይ የሚወስድ አይመ ስለኝም » እያለ ያስብ ጀመር ።

ቂሱና ረዳቱ ልጅ ሥርዓቱን ፈጽመው ሔዱ ። ከዚያ በኋላ ግን ቫልዣ እንደነገሩድንድ የሚሙህ ነገር ሰማ ። ጉድጓድ ቆፋሪው በአካፋው አፈር ገቧ አንስቶ ሳጥኑ ላይ ሲዘረግፈው ነበር ። ለሁለተኛ ጊዜ አፈር ገቧ አንስቶ ሲዘረግፍበት ከመጮንፈሻው ብሶት አንዱ ዝግት አለ ። ጉድጓድ ቆፋሪው ለምስተኛና ለአራተኛ ጊዜ አፈር ገቦ አንስቶ ሳጥኑ ላይ ሲዘረግፍበት ጫናው ሰለበዛበት ግን ቫልዣ ሕሊናውን ሳተ ።

@OLDBOOKSPDF

ጉድጓድ ቆፋሪው አፈሩን በሚመልስበት ጊዜ ፎሽለሻ ዝም ብሎ አልተመለከተውም ። ወይን ጠጅ ልጋብዝህ ፥ አፈር የመመለሱ ሥራ እስከ ዚህም የሚያጣድፍ አይደለም እያለ ሲወተውተውና ሲያባብለው ቆየ ። ጉድጓድ ቆፋሪው ግን አልሰማ ብሎ ለአምስተኛ ጊዜ አፈር ሲመነቅ ገመን በስ ሲል የሰደርያው ኪስ ክፍት አለ ። ፎሽለሻ በኪሱ ውስጥ ምን እንዳለ አስተውሎ ወደሰውዬው ጀርባ ዞሮ ሰውዬው ልብ ሳይል ከኪሱ ውስጥ የነበረውን የመታወቂያ ወረቀቱን ቀስ ብሎ አውጥቶ ወሰደበት ፤

«በነገራችን ላይ.....» አለው ፤« የመታወቂያ ወረቀትህን ይዘህ ልሞጥ ተሃልህ?»

«የምን የመታወቂያ ወረቀት ነው ደሞ?»
«ጀምበሯኮ በመጥለቅ ላይ ነች ።»
«ትጥለቃ ታዲያ!»

«ጀምበር እንዲጠለቅሽ ወዲያውኑ የመነነ መታበሩ መውጫ በር እንደሚዘጋ አታውቅም?»

«እንደሚዘጋ.....?» ብሎ ኪሱን ይደባብስ ገባ ። የመታወቂያ ወረቀቱን ሊያገኘው አልቻለም ። «አቤት አረስቼው መጣሁ መሰለኝ!»

«የመታወቂያ ወረቀትህን ካልያዝክ 15 ፍራንክ መቀጫ መክፈል ይኖርብሃል..... የማይቀርልህ ዕዳ ነው ።»

አሰሪ አምስት ፍራንክ መክፈል ስመታበር ቆፋሪው ቅሉል ነገር ባለመሆኑ በስጨትጨት አለ ። አካፋውን መሬት ላይ አስተምጠ ከሃሳብ ውስጥ ገባ ።

«አይዞህ.....!» አለው ፎሽለሻ ፤ «ለሥራው አዲስ ስለሆነክ ምን መደረግ እንዳለበት የምታውቅ አልመሰለኝም ። እንደምታየው ጊዜው መሸ ትሸት ብሏል ። ከአምስት ዶቂቃ በኋላ ጀምበሯ መጥለቋ አይቀርም ። አንተም ብትሆን በአምስት ዶቂቃ ውስጥ አፈሩን መልሰህ ለመጨረስ እንደማትችል ግልጽ ነው ።»

«እና....?»

«ምክሬን ትሰማ እንደሆነ በሩ ከመዘጋቱ በፊት ፈጥነህ ብትወጣ ይሻልሃል» አለውና ፤ «ለመሆኑ የት ነው የምትኖረው....? ቤተሀ ሩቅ ነው?» ሲል ጠየቀው ።

«እስከዚህም ሩቅ አይደለም ። ከዚህ አሰራ አምስት ዶቂቃ ያህል ቢያስኬድ እንኗ ከዚያ አያልፍም ። በቁጥር 87 ሕንጻ ውስጥ ነው የምኖረው..... በቮገራር ጐዳና ።»

@OLDBOOKSPDF

«እንግዲያውስ ከዚህ ሩጠህ ለመውጣት በቂ ጊዜ አለህ ። እቤትህ ደርሰህ የመታወቂያ ወረቀትህን ለማምጣት ትችላለህ ። እሱን ከያዝህ ለመግባትም ሆነ ተመልሰህ ለመውጣት የሚያግድህ ኢይኖርም ። የ15 ጥራንክም መቅጫ ይተርልሃል ። ስለዚህ በርረህ ሔደህ መታወቂያህን ይዘህ ና ። እስከዚያ ድረስ አስከሬኑን እኔ እጠብቅልሀለሁ ። ከዚያም በኋላ አፈሩን መልሰህ ተገናኝተህ ለመወጣት ትችላለህ ።»

«ባለወለታዬ ነህ!» አለው ከእንጀቱ ።
«በልቅ ፈጥነህ ሒድ!»

መታብር ቆሌሪው ደስታውን ለመግለጽ ያህል ጨበጠውና እግሬ አውጪኝ ይሮጥ ጀመር ። ፎሽለቫም ወደ ጉድጓዱ አፍ ጠጋ ብሎ ፤ «ሙሴ ማድሌን!» ሲል ተጣራ ፤ ዝቅ ባለ ድምጽ ።

መልስ የለም ።

ፎሽለቫ ደንግጥ ብሎ ፥ ከጉድጓዱ አፍ ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ጎበዶ የገጠን ቫልዣ ራስ ወዳለበት ሦሮ ፤ «አለሰሙኝም እንዴ ሙሴ ማድሌን?» አለው ።

አሁንም መልስ የለም ።

ፎሽለቫ በጣም ተደናግጦ መድሻውንና መሮውን አወጣቱ የላጉን ክዳን ለመንቀል ይታገል ጀመር ። ክዳኑን ሲያነሳው የገጠ ቫልዣ ሬት ገር ጥሏል ።ዓይኖቹ ተከደንዋል ። ሙሴ ስውኑቱ ለጥ ፥ ጸጥ ብሏል ።

«ወይኔ! ሞተዋል!» አለ ፎሽለቫ ራሱ ሲራስ ፤ «ሕይወታቸውን አድናለሁ ብዬ.....!»

ፎሽለቫ ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር ። «ጥፋቱ የሚስቲዬን ነው ። ሚስ ቲዬን ለምን ሞተ? ባልታሰበ ሰዓት ማን መታት አለው? ለመሴ ማድሌን ጥቃ ምክንያቱ እሱ ነው!» ብሎ እንደገና «ሙሴ ማድሌን! መሴ ማድ ሌን!» ሲል ተጣራ ። መልስ ግን አላገኘም ።

«ከአሁን ወዲያ መላ ነገሩ አልቋል ። ምን ዓይነት ትርጉም የለሽ ጉድ ነው? አዬ ፈጣሪዬ! በቃ ሞተዋል? ነገሩ አለቀ? እና ትንሿን ኮዜት ምን ላደርጋት ነኝ? ፍራፍሬ ሻጪስ ምን ትል ይሆን?» ሲል አነበነበና እን ደገና ይጣራ ጀመር ፤ «ሙሴ ማድሌን! መሴ ማድሌን! አየር አጥተው ነው የሞቱት ። ተድሞውንም ቢሆን ፈርቼላቸው ነበር! እሳቸው ግን አልሰማ አሉኝ ። እንዴት ያለ ጉድ ነው! ወይ ፈጣና ! ወይ ደጉ ሰዉ!»

ፎሽለቫ ጸጉሩን ይነጭ ገባ ። «ሙሴ ማድሌን! መሴ ከንቲባ!»

ጭጭ.....ጭጭ ።

@OLDBOOKSPDF

በዚህ ጊዜ ከመካነ መቃብሩ መግቢያ በር በኩል ድምጽ ሰማ ። በሩ በመዘጋት ላይ ነበር ። ቀጥሎም ዓይኑን ወደ ጣን ቫልገ መልሶ አተኩሮ አየው ። ከበራት የባሰ ድንጋጤ ወረረው ፤ የጣን ቫልገ ዓይኖች ተከፍተው አፍጥጠውበት ነበርና ። አስከሬን ማየት ያስደነግጣል ። የሞተው አስከሬን እንደገና ነፍስ ዘርቶ ከሞት ሲነሳ ማየት ደሞ ይበልጥ ያስደነግጣል ። ፎሽለቫም እንደሐውልት ባለበት ደርቆ ቀረ ።

«ተኝቼ ነበር» አለው ጣን ቫልገ ፤ ከተኛበት ቀና ብሎ ።
«ወይ ወላዲተ አምላክ! እንዴት አስደነገጠኝ ሙሴ ማድሌን!»

ጣን ቫልገ ሕሊናውን ስቶ ነበር እንጂ ሕይወቱ አላለፈም ነበር ። ሳጥኑ ተከፍቶ ቀዝቃዛ አየር ሲመታው ሕሊናው ነቃ ።

«እና እውነት አልሞተም! » አለው ፎሽለቫ ዓይኑን ሰማመን ቸግሮት ፤ «ጣጠራዎት.....! ብጠራዎት.....! ብጠራዎት.....! ሲሰሙኝ ነው! ብቻ እንኳን ነቁ ። እኔስ እጎዲያው አየር አጥተው ታፍነው ሞቱ ብዬ.....! ሳይነቁ ቢቀሩ ኖሮ ሳላብድ አልተርፍም ነበር ። በእውነት ጨርቄን ጥዬ ነበር የምሐደው! ለመሆኑ ሞተው ቢቀሩ ኖሮ..... ልጅዎን ምን ልላት ኖሯል? ፍራፍሬ ሻጯስ ብትሆን እውነቱን ብነግራት ታምነኝ ኖሯል? በጭራም.....!»

«ጣርድ ብርድ ብሎኛል» አለው ጣን ቫልገ ።

«ከዚህ ቦታ ፈጥነን መወጣት አለብን» አሰኖ ፎሽለቫ ከኪሱ አልኮል ያለበት ቅል አወጣው ፤ «አስቲ እፍም ያርየቡት» አለው ። ጣን ቫልገ ብራንዲውን ተጎንጭቶ ጉርጉጭ ሲያደርገው ሰውነቱ ሙሉ በሙሉ ነቃ ። ከሬሳ ሳጥኑም ወጥቶ ክዳኑን መልሶ በመዝጋትና አፈር በመመለሱ ሥራ ፎሽለቫን ያግዘው ገባ ።

ባደመን ሳጥን ከቀበሩት በኋላ ፎሽለቫ ጣን ቫልገርን አያየ ፤ «አንተ ሐድ..... እኔ አካራውን እይዛለሁ ። እርስዎ ዶማውን ይያዙሁ አለው ።

የሬሳ ማጓጓዣው በመጣበት መንገድ ወደ በሩ አቅጣጫ አመሩ ። ከዚያ ሲደርሱም ፎሽለቫ የግሪቢዬን የመታወቂያ ወረቀት አውጥቶ ወረቀቱ ከሚጣልበት ቀዳዳ ውስጥ ጨመረው ። በረኛው ይህንን ሲያይ የበር መክፈቻውን ገመድ ጉተት አደረገው ። በሩ ሲከፈት ጣን ቫልገርና ፎሽለቫ ወጥተው ሔዱ ።

«መጨረሻው አማረም እይዶል!» አለውና ፎሽለቫ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ከቫገርራር ጐዳና ሲደርሱ ፤ «የኔ ዓይን በቅጡ ስለማያይልኝ ቁጥር 87 የተጻፈበትን ቤት ፈልገው ያመልክቱኝ» አለው ፎሽለቫ ። የግሪ ቢዬን ቤት በመፈለግ ላይ ነበር ። ጊዜው ደንገዝገዝ ብሏል ።

@OLDBOOKSPDF

ሠቲጥር ለማንያ ሰባትማ ይሽወና» አለው ጐን ቫልጐ ።

«እንግዲያውስ ዶማወን ይስጡኝና እዚሁ ይጠብቁኝ ። በመንገድ ሞንም ስለሌለ አንዳችም የሚያሰጋ ነገር የለም ። አሁን እመለሳለሁ» ብሎት ቲጥር 87 ሕንጻ ውስጥ ገብቶ ወደላይኛው ፎቅ ወጥቶ በር አንኳኳ ።

«ማቢ! የሚል ድምጽ ሰማ ። የግሪቢዬ የራሱ ድምጽ ነበር ።

ክፍሉ መቀመጫ እንኳ የሌለው የድሃ መኖሪያ ነው ። በውስጡ ግን የሌለ ቅራቅምቦ የለም ፤ የዕቃ ማጐሪያ ሳጥን..... ከባያ የመሰለ የወሃ መጠጫ..... የሣር ፍራሽ ..... ሌላ ሌላም ቅራቅምቦ ።

በአንድ ጥግ በአሮጌ ምንጣፍ ቁራጭ ላይ አንዲት ኮሳሳ ሴትዮ በርካታ ልጆች ተከመልከለው በታል ።

ግሪቢዬ የመታወቂያ ወረቀቱን በሚፈልግበት ጊዜ የቤቱን ዕቃ አተረማምሶታል ። አገረሽርኮታል ። ቤተሰቡንም ሳያንጫጫው አልቀረም ።

«አካፋህንና ዶማህን ይዤልህ መጥቻለሁ» አለው ፎሽለቫ ። ግሪቢዬም በመገረም ዓይን አየውና «አንተ ነህ እንዴ!» አለው ።

«አዎን አኔው ነኝ ። ነገ ጠዋት ከመካነ መቃብሩ ብትሔድ የመታወቂያ ወረቀትህን በረኛው ዘንድ ታገኘዋለህ» አለው ።

«ምን ማለትህ ነወ?» አለው ግሪቢዬ

«የመታወቂያ ወረቀትህን መሬት ላይ ጥለኸው አገኘሁት ። አፈሩንም መልሼልሃለሁ ። አስከሬኑ ተቀብሯል ማለቴ ነው ። አስራ አምስት ፍራንክ መቀጫ ከመክፈልም ድነሃል» አለው ።

ግሪቢዬ ደስ ብሎት አመሰገነውና «በሌላ ጊዜ ሰንገናኝ መጠጥ አጋ ብዘሃለሁ» አለው ።

— 9 —

ጐን ቫልጐና ፎሽለቫ ተያይዘው ወደ ፍራፍሬ ሻጯ ቤት አመሩ ! ከዚትን ስመው ሰደድ ። ከቤት ያለፉትን ሀያ አራት ሰዓታት ያሳለፈችው ቢዝምታና በፍርሃት ነበር ። ጐን ቫልጐና ፎሽለቫ የት እንደሔዱና ስንት እንደሔዱ ፊጽሞ አታውቅም ። እነሱ ከሔዱ ጀምሮ አህል ውሃ አልቀመሰችም ። አልተኛችምም ። ፍራፍሬ ሻጯ ምን ሆነሻል በማለት የጥያቄ ናዳ ብታወርድባትም መልስ አልሰጠቻትም ።

@OLDBOOKSPDF

ከሀያ አራት ሰዓታት የመንፈስ ጭንቀት በኋላ ጐን ቫልገን መልሶ ስታገኘው ይህ ነው የሚይባለ ደስታ ተሰማት ።

ጐን ቫልገን ፥ ፎሽለቫና ኮዜት ከጥራጥሬ ቫጪ ቤት ወደ ጎዳሙ አመሩ። ከዚያ ደርሰው የግቢውን በር አንኳኩተው ከገቡ በኋላ ወደ እመምኔቷ ዘንድ አቱ ። እመምኔቷ ሲጠባበቋቸው ነበሩ ፤ ከአንዲት ሴላ መነኩሲት ጋር ሆነው ። ያሉበት ክፍል ጨለምለም ብሏል ። ለነገሩ ያህል ግን አንድ ደካማ ሻማ በርቷል ። እንደተለመደው መነኩሲዎቹ አቀርቅረው መሬት መሬቱን ነው የሚያዩት ። እመምኔቷ ከቀረቀሩበት ሆነው ለጐን ቫልገ ጥያቄ ይደረድሩለት ገቡ ፤

«ወንድምዬው አንተ ነህ ?»
«አዎን እማሆይ ።»

ተጠያቂው ጐን ቫልገ ቢሆንም በአፈቀላጤነት መልስ የሚሰጠው ፎሽለቫ ነበር ።
«ስምህ ማን ይባላል?»
«ኡልቲም ፎሽለቫ ።»

ፎሽለቫ በእርግጥም ኡልቲም ፎሽለቫ የተባለ ወንድም ነበረው ። ነገር ግን ሞቷል ።

«ከወዴት ነው የመጣኸውና»
«ሞንፐኪኘ..... ከአሚዬን ቅርብ ያለው ።»
«ዕድሜህ.....?
«ሳምሳ ዓመት ።»
«ሙያህ.....?»
«አትክልተኛ ።»
«ጥሩ ከርስቲያን ነህ?»
«አዎን..... እንደመላው ቤተሰቤ ።
«ይህች ልጅ ያንተ ልጅ ነች?»
«አዎን እማሆይ»
«እንተ የቧ አባት ነህ?»
«አያታ ነኝ ።»

አስካውን ድረስ ጐን ቫልገ አንድ ቃል እንኳ አልተነፈሰም ። መልሱን በሙሉ በአፈቀላጤነት የመለሰው ፎሽለቫ ነበር ።

እመምኔቷ ኮዜትን አስተውሰው ኡይዋትና ሃሳባቸውን ወደ ፎሽለቫ በመመለስ ፤ «አባ ፎቫ.....» አሉት ፤ «በጉልበት ላይ የሚታሠር ሌላ ታጭል ያሻል ። ከአሁን ጀምሮ ሁለት ስለሆናችሁ ሁለት ታጭል ያስፈልጋችኋል።»

@OLDBOOKSPDF

ከዚት የገዳሙን ኑሮ በቶሎ ተላመዷትው ። እንደገዳሙም ልጆች ትለብስ ጀመር ። ግን ቫልገ ከአነቴናርዲዬ ቤት ሲወስዳት የሰጣት ልብሶች ቢያረጁም ከበትቱነት ደረጃ አልደረሱም ነበር ። እነዚህን ልብሶች የግር ሹራበጅና ጫማዎቿ ሙምር ግን ቫልገ ወስዶ ሳጥን ውስጥ ቆለፈ ባቸው ።

ግን ቫልገ በበኩሉ የአትክልተኛነት ሥራው ፈጽሞ አላስቸገረ ውም ። ቀደም ብሎ የእርሻ ሙያ አውቀት ስለነበረው አትክልቱን በይበልጥ አለማው ። ብዙ ፍራፍሬም ይመረት ጀመር ።

ግን ቫልገ በፎሽለቫ ጎጆ ይኖር ስለነበረና ኮዜት በገዳሙ ውስጥ በአዳሪነት ትኖር ስለነበረ አንዴ ድሮ አብረው መኖራቸው ቀረ ። ይሁን እንጂ በየቀኑ በዕረፍት ሰዓት ሔዳ እንድትጠይቀው ተፈቅዶላት በየቀኑም አንድ ሰዓት ያህል ገዚ ከሱ ጋር ታሳልፍ ነበር ።

ለግን ቫልገ የገዳሙ ኑሮ እንዲስር ቤት ኑሮ ነበር ። ግቬር አሠራም እንደሚከታተለው ስለሚያውቅ ለአትክልቱ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለመግዛት እንኳ ከገዳሙ ሊይወጣም ነበር ። ግዢ በሚያስ ፈልግበት ጊዜ ፎሽለቫ እያነከሰ ወጥቶ አስፈላጊውን ሁሉ ይገዛ ነበር ።

ግን ቫልገ በገዳሙ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ አቡነ ሚሪዬልን ሳያ ስታውሳቸው አልቀረም ። ሳያስታውሳቸውም ሊቀር ሊይችልም ነበር ። እንደአጋጣሚ ሆኖ የእግዚአብሔር ቤት ሁለት ጊዜ በክፉ ወቅቱ መጠ ጊያ ሰጠው ። መጀመሪያ ፣ ሕብረተሰቡ ማደርያ ነጭነት ሲንከራተት በነበረ በት ሰዓት አቡነ ሚሪዬል ቤት ለእንግዳ ብሊው ተቀበሉት ። ሁለተኛም ፣ ግቬር እንደዱር አውሬ ያሳድደው በነበረበት ሰዓት የጥቂ— ግስጥ ገዳም መጠጊያ ሰጠው ።

በዚህ ሁኔታ ዓመታት አለፉ ። ከዚትም እያደገች ሔደች ።

@OLDBOOKSPDF

ክፍል ሦስት

ማሪያ

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አንድ

ፓሪስ የወለደው

— 1 —

ዕድሜው ከሰባት አስከ አስራ ሦስት ሊመት ይደርሳል ። ቤት የለውም ። በረንዳ ያድራል ። በልክ የተሰፋ ልብስ የለውም ። ቁጥድም ጊዜ የአባቱ የንቤረ አሮጌ ሱሪ ይታጠቃል ፤ አስከተረከዙ የሚደርስ ። ለአባቱ ሞንቅላት ልክ የሆነ ባርኔጣም ይደፋል ። ለሱ በጣም ስለሚሰፋበት ባርኔጣው ወርዶ ጆሮውን ይሸፍንዋል ። ምናልባት አንድ ቸሚገ ይኖረው ይሆናል ። መቀ የሪያ ግን የለውም ። ሚማም ሲኖረው ይችላል ፤ ሱሉ የወለቀ ።

የራሱ የሆነ የአኔጋዜር ፊሊጥ አለው ። ሞንክልም አይጠፋውም ። ቡርሂዎቹን ይጠላል ። ንግግሩ ሁሉ የባስኔ ነው ። ሙንግድ ለመግንድ ሲኤትን ይውላል ። ያገኘውን ሥራ ይሠራል ። ጋሪ ጥራ ካሉት ጋሪ ይጠራል ። ይላላካል ። ከዚህም ሥራው ቢሳቢስቲ ያገኛል ። መሸት ሲል ለት ትያትር ለማየት ክትያትር ቤት ይገባል ። ትያትር ማየት ፥ ማጨ ብጨብ ታሳቅ ደስታው ነው ። ይሁን እንጂ ርካሽ የሆነን የሚያስቅ ካልሆነ በስተቀር ቁም ነገር ያዘለ ትያትር አያስደስተውም ። የህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሉትም ። የሚያስፈልጉና ዋጋ ቢስ የሆኑ ነገሮች ግን ሞልተውታል ።

ዘፈን ይወዳል ። ይዘፋፍናል ። ያቭጫል ፣ ነጻ ሆኖ ተደስቶ ይኖራል ። ልቡም ንጹህ ነው ፣ ልጅ ነውና ።

ብቻውን አይደለም ይህ ፓሪስ የፈጠረው ያራዳ ልጅ ። ጓደኞች አሉት ..... እሱን የመሰሉ ። ሁሉም አድፈው ይታያሉ ። ጸጉራቸው የተጎ ጨበረረ ፣ ልብሳቸው የተቦጫጨቀ ፣ አቧራ የለበሱ ናቸው..... የድሆች ልጆች ። ከትንሽ ጉድጓድ ዘርያ ሆነው ብዬ ኢምንከባለሉ ይጫወታሉ ። በቤሳቢስቲ ይጣላሉ ። አሮጌ የአግር ሹራብ ወይም ሌላ አርባና የሌለው ነገር ሲሸጡ ይታያሉ ። ዘፈናቸው ብልግና የበዛበት ነው ። ከመሐከላቸው

@OLDBOOKSPDF

ሴት ልጆችም አለባቸው ። በየጊዜው ፖሊሶች ኢያፈሱ ይወስዷቸዋል ። ነገር ግን እነሱ በፖሊሶች ሲታፈሱ ሌሎች ያራዳ ልጆች ይፈጠራሉ— ፓሪስ ይወልዳቸዋል ።

— 2 —

ጣን ቫልጣና ኮዜት በፐቲ—ፒክፑ ጐዳና ባለው ገዳም መኖር በጀመሩ በስምንተኛው ወይም በዘጠነኛው ዓመት የአስራ አንድ ወይም የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ በታምፕል ጐዳናና በሻቶ—ደ አካባቢ ይታይ ጀመር ። ልጁ የአራዳ ልጆች ወይም ስድ— አደሳች ከሚባሉት አንዱ ነበር ። የአዋቂ ሰው ሱሪና የሴት ሸሚዝ ይለብሳል ። ወላጆች ቢኖሩትም እንዚሀን ልብሶች የሰጡት ሌሎች መጽዋቾች ናቸው ። አባቱ ለልጁ ደንታ የለውም ። እናቱም አሳውደውም ።

ይህ ልጅ አንዱ በረንዳ አዳሪዎች ሁሉ ግድ የለሽ ሆኖ ይኖራል ። ሲያመሸው ይሰርቃል ። ወሮበላ ሲሉት በሳቅ ያሳልፈዋል ። ሴባ ሲሉት ግን ይቆጣል ። መጠሊያ የለውም ። ዳቦ የለውም ። የሚሞቀው እሳት የለውም ። የሚያፈቅረው የለውም ። ይህም ሆኖ የነጻነት ኑሮ ስለሚኖር በመከፋት ፋንታ ተደስቶ ይኖራል ።

ወላጆቹ ወልደው የጣሉት ቢሆንም አልፎ አልፎ ሲያስታውሳቸው ፤ «አዎ .... እናቴ ዘንድ መሔድ አለብኝ» ይላል ራሱ ለራሱ ። ወላጆቹ የሚኖሩት በቁጥር 50—52 ፥ ይህም ማለት በጎርቦ ማረፊያ ቤት ነበር ። ልጁም በየሁለት ወይም በየሦስት ወር የአራዳ ኑሮውን አቋርጦ እነሱ ዘንድ ይሔዳል ።

የጎርቦ ማረፊያ ቤት ቀደም ባለው ጊዜ ፤ « የሚከራዩ ክፍሎች » የሚል ማስታወቂያ ይበዛበት ነበር ። አሁን ግን ክፍሎቹ በርክት ባሉ ተከራዮች ተይዘዋል ። ተከራዮቹ ዝምድና የላቸውም ። አይተዋወቁም ። በዝቅተኛ የህብረተሰብ መደብ የሚገኙም ናቸው ።

ጣን ቫልጣ በጎርቦ ማረፊያ ቤት በነበረበት ዘመን በዚያ የነበረችው አሮጊት ሞታ በቦታዋ ሌላ አሮጊት ተተክታለች ። ይህች አሮጊት ማዳም ቡጎ ትባላለች ።

ከተከራዮቹ መሐከል በጣም የደኸየ አንድ ቤተሰብ ይገኝበታል ። አራት የቤተሰብ አባላት አሉት ፤ አባትዬው ፣ እናትዬው እና ሁለት የደረሱ ልጆቻቸው ። አራቱም በአንድ ክፍል ውስጥ ይኖራሉ ።

አባትዬው ክፍሉን በተከራየበት ወቅት ስሙ ጐንድሬት መሆኑን ተናግሯል ። በተጨማሪም ፤ « የፖላንድ ወይም የኢጣሊያ አለዚያም

@OLDBOOKSPDF

የአስፓኛ ተወላጅ የሆነ ሰው እፈልጋለሁ የሚል ሰው ከመጣ ተፈላጊው እኔ ሳልሆን አልቀርም » ሲል ለማጸም ቡጎ ነግሯታል ።

ይህ ቤተሰብ በታምፕል ጐዳናና በሻቶ ደ ኢካባቢ የሚታየውና « ትንሹ ጋቭሮሽ » ተብሎ የሚጠራው ሕፃን ልጅ ቤተሰብ ነው ። ልጁ ወደ ቤተሰቡ በሚመለስበት ጊዜ የሞቀ አቀባበል አያገኝም ። ሁሉም ነገር ቀዝቅዞ ይጠብቀዋል ።

« ወዴት ነበርክ ? »ይሉታል ከነበረበት ሲመለስ ።
« ባቡር መንገድ » ሲል ይመልስላቸዋል ።

ተመልሶም ሲሄድ « ወዴት ነው የምትሄደው ? » ይሉታል ።

« ወደ ባቡር መንገድ » ሲል ይመልስላቸዋል ።
« እንግዲያው ምን ልትፈጥር መጥተህ ኖሯል ! » ትለዋለች እናቱ ፤ የኗ ሳይሆን የሌላ ሰው ልጅ እንደሆነ ሁሉ ። እሱን አትወደውም እንጂ ሴት ልጆቿን ትወዳቸዋለች እናቲቱ ።

የገርንድሬት ቤተሰብ የሚኖረው ከመኖሪያው በረንዳ ጣሪ ባለው የመጨረሻ ክፍል ሆኖ ከሱ ወዲህ ባለው ክፍል ማሪዩ የተባለው ወጣት ልጅ ይኖርበታል ።

@OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ ሁለት

ታላቁ ከበርቱ

— 1 —

የማሪዩ አያት ፥ ገርልኖርማ ከዘጠና ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው አሳ ውንት ነው ። በዚህ ዕድሜው ቀጥ ብሎ ይራመዳል ። ድምጹን ከፍ አድ ድርጎ ይናገራል ። በጉልህ ያያል ። ደረቅ መጠጥ ይጠጣል ። አንክት አድርጎ ይበላል ። ከሠላሳ ሁለት ጥርሶቹ አንዱ እንኳ እንኳን የለውም ። ሲያኑበብ ካልሆነ በስተቀር መነጽር አያደርግም ። « ባለቅት አስር ዓመታት ሴት ዘንድ አልቀረብኩም » ይላል እንጂ በተፈጥሮው ሐያጅ ነበር ።

ገርልኖርማ ማኛ የተባለች የቀድሞ ጎረዱ ሁለት ወንድ ልጆች ወልጇልሃለሁ በማለት ለልጆቹ ማሳደጊያ ገንዘብ ጠይቃው በወር 80 ፍራንክ ይከፍላት ነበር ። የመጀመሪያው ሕፃን የተወለደው ገርልኖርማ 84 ዓመት ዕድሜ በነበረው ጊዜ ነበር ። ገርልኖርማ ሁለት ጊዜ አግብቷል ። ቱባቶችም ነበሩት ።

ገርልኖርማ የባ ሕርይ ጥልቀት የለውም ። ለማናቸውም ነገር ይቻኮ ላል ። በቀላሉ ይቆጣል ። ያለበቂ ምክንያት ይናደዳል ። ሰው ሃሳቡን ሲቃ ረንበት ከዘራውን አንሰቶ ልማታ ይላል ፤ በተድሞ ዘመን ይደረግ እንደነ ነበረ ።

ታላቁ ከበርቴ ገርልኖርማ ከመጀመሪያ ሚስቱ ሴት ልጅ ወልዷል ። ሴት ልጁ ሳታግባ አምሳ ዓመት ሞላት ። ከሱው ጋር ትኖራለች ። አንደ ሕጻንም ልጅ ይቆጥራታል ። ከሁለተኛም ሚስቱ ሴላ ሴት ልጅ ወልዷል ። ይህችኛዋ ካገባች በኋላ ወንድ ልጅ ወልዳ ሞተች ። ልጇ ማሪዩ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

ገርልኖርማ ታላቅ ከበርቴ እንጂ የመሳፍንት ወገን ባይሆንም ውሎው ከመሳፍንት ጋር ነበር ። አስተሳሰቡም ከነሱ ጋር ይገጥም ነበር ።

በሳምንት ሁለት ቀን በማዳም ባሮን ዱ ቴ ቤት ይገኛል ። የማዳም ባሮን ዱ ቴ ቤት የመሳፍንትና የመኳንንት መሰባሰቢያና መናኸሪያ ከሆነ ጊዜው ውሎ አድሯል ። መሳፍንቱና መኳንንቱ በዚያ ተሰብስበው ሻያቸውን እየጠጡ ንጉሣዊ አገዛዝን የሚደግፍ ጨዋታ ይጫወታሉ ። የናፖሌዎንን ደጋፊዎች ያወግዛሉ ። ስለ አስቤት ዘመን አጥላልተው ያወጋሉ ። በአስተሳሰባቸው መዳ ዓመት ያህል ወደ ኋላ የቀሩ በመሆናቸው ያሉበትን ዘመን አያውቁትም።ምን ዓይነት ዘመን እንደሆነ አይገባቸውም።

ገርልኖርማ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ጨዋታ ለመሳተፍ ወደ ማዳም ባሮን ዱ ቴ በሳ በሚሔድበት ጊዜ ማሪዩ ተከትሎት ይሔዳል ። ማሪዩ ከአያቱና ከአክስቱ ጋር ነው የሚኖረው ። ስለዓለም የሚያውቀውም ነገር ቢኖር አስተሳሰባቸው ወደ ኋላ ከቀረው ከእነዚህ የፊውዳል ወገን አባሎች ፣ ማለት ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ የሚሰማው ብቻ ነበር ።

ማርዩ ከአያቱና ከአክስቱ ጋር የሚኖረው አባት ስለሌለው አልነበረም ። አባቱ በህይወት አለ ። በቬርኖ ከተማ የአበባ አትክልት እያለማ ይኖራል ።

ስሙ ፖሚርሲ ይባላል ። በግንባሩና በጉንጩ የጀግንነት ምልክት፣ ይህም ማለት በጦር ሜዳ ሲዋጋ በሰይፍ ተመትቶ ስለነበረ ጠባሳ አለበት ። ገርልኖርማ አማቹን አይወደውም።እሱ የቡርቦን ሥርወ መንግሥት ደጋፊ ሆኖ ሳለ ፖሚርሲ የናፖሌዎን ደጋፊ በመሆኑና ናፖሌዎንን ተከትሎ ሔዶ በብዙ ጦር ሜዳዎች በመዋጋቱ ምክንያት እንደወንበዴ ይቆጥረዋል ። ማሪዩ ከአባቱ ጋር እንዳይኖር ያደረገውም ገርልኖርማ ነው ። «ማሪዩ ከአንተ ጋር ከኖረ ከእኔም ሆነ ከአክስቱ አንዳችም ነገር አይወርስም» ብሎ ስላስጠነቀቀው ማሪዩ ውርስ አልባ እንዳይሆን በመፍራት ልጁ ከአያቱና ከአክስቱ ጋር እንዲኖር ፈቀደ ። ፖሚርሲ ልጁን በጣም ይወደዋል ። ነገር ግን በገሐድ ሊያየው እንኳ ገርልኖርማ አይፈቅድለትም ። በዚህ ምክንያት አልፎ አልፎ ብቻ በድብቅ ወደ ፓሪስ ከተማ እየመጣ ማሪዩና አክስቱ ከሚያዘወትሩት ቤተክርስቲያን እየሄደ አዩኝ አላዩኝ እያለ በሩቅ ሆኖ ልጁን አይቶ ይመለሳል ።

ቀደም ብሎ ፖሚርሲ በቦር ሜዳ በፈጸመው ጀብዱ ምክንያት ከናፖሌዎን ቦናፓርት የኮሎኔልነት ማዕረግ ተቀብሎ ነበር ። የሌጊዮ ዶነር (የክብር ሠራዊት) አባልም ነበር ። ነገር ግን ናፖሌዎን ከስልጣን ወርዶ የንጉሥ አገዛዝ እንደገና ሲመሠረት የመኰንንነት ማዕረጉ ሳይጸናለት ቀረ ።

@OLDBOOKSPDF

ማሪዩ ፖሚርሲ አደግ ሲል እንደ ሌሎች ልጆች ሁሉ ትምህርት ቤት ገባ ። ቆይቶም ኮሌጅ ገብቶ የህግ ትምህርቱን ይከታተል ጀመር ።

በ1827 ዓ. ም. ማሪዩ የአሰራ ስባት አመት ወጣት ነበር ። በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሳለ አንድ ቀን ወደ ቤቱ ሲመለስ አያቱ ገርልኖርማ አንድ ደብዳቤ ይዞ ጠበቀው ።

«ማሪዩ .....» አለው አያቱ ፤ « ነገ ወደ ቬርኖ መሬድ ሳይኖርብህ አይቀርም መስለኝ ። »

« ቬርኖ ..... ? ለምን ? »

« አባትህን ለመጠየቅ ። »

ማርዩ ደስ አልልህ አለው ። ያልጠበቀው ሆነበት ። አባት እንዳለው ቢያውቅም ስለ አባቱ የሚያውቀው ነገር አልነበረም ። አባቱ ይወደኛል ብሎ ያሰበበትም ጊዜ የለም ። በዚህም ምክንያት እሱ ራሱ አባቱን አይወደውም ነበር ።

« አባትህ የታመመ ይመስለኛል » አለው አያቱ ቀጠል አድርጎ ፤ « ሔደህ እንድትጠይቀው ይፈልጋል ። እና ነገ ጠዋት ተነስተህ ብትሔድ መልካም ነው ። ከኛጋ፡ በ12ሰዓት ተነስቶ ወደ ሚታ ጊዜ ከቬርኖ የሚደርስ የሕዝብ ማመላለሻ አለ ። በእሱ ተሳፍረህ ብትሔድ ... አባትህ በአ ስቸኳይ ነው የሚፈልግህ »

ይህንኑ ብሎ ደብዳቤውን ጨረማምዶ ኪሱ ውስጥ ጨመረው ። ማሪዩ በዚያው ቀን ምሽት ተሳፍሮ ቢጓዝ ኖሮ በማግሥቱ ጠዋት ሲደ ርስ ይችል ነበር ፤ በሴሊት የሚጓዝ የሕዝብ ማመላለሻ ነበርና ። ነገር ግን ገርልኖርማም ሆነ ማሪዩ በዚህኛው መጓጓዣ ለመጠቀም ፍላጎት አልነበራቸውም ።

በማግሥቱ ማሪዩ ማልዶ ተነስቶ በሕዝብ ማመላለሻ ተጉዞ ወደ ማታ ጊዜ ከቬርኖ ደረሰ ። ለዓይን ያዝ ማለት ስለጀመረ የከተማው ነዋሪዎች መብራት የሚያበሩበት ወቅት ነበር ። ማሪዩ የአባቱን ቤት አጠ ያይቆ ደረሰበት ። መጥሪያውን ሲደውለው አንዲት ሴትዮ የበራ ሩሞስ ይዛ መጥታ በሩን ከፈተችለት ።

«የመ.ሲ ገርሸር ፖሚርሲ መኖሪያ ቤት ነው ? » ሲል ጠየቃት ።

ሴትዮዋ መልስ ሳትሰጠው ዝም ብላ ቆመች ፤ ሐውልት እንደሠነፃ ሁሉ ።

«የመ.ሴ ፖሚርሲ ቤት ነው ወይስ አይደለም ? »

@OLDBOOKSPDF

በመናገር ፈንታ ራሷን ላይና ታች ነቀነቀችለት፤ « ነው» እንደማለት ።

« ላነጋግረው እችላለሁ ? »

አሁንም በመናገር ፈንታ አራስዋን ቀንና ግራ ነቀነቀችበት ፤« አይ ሆንም እንደማለት ።

« ልጄ ነኝ ..... አስጠርቶኛ ነው የመጣሁት » አላት ማሪዩ ።

ሴትዮዋ ስሜቷን መቆጣጠር አቅቷት ታለቅስ ጀመር ። በእጅ ምልክትም እንዲገባ ጋበዘችው ።

ክፍሉ ውስጥ ጧፍ በርቶበታል ። አንድ ሰውዬ ቀጥ ብሎ ቆሞ ይታ ያል ። ሐኪም ነው ። ሌላ ሰውዬ ተንበርክኳል ። ቄስ ነው ። ሦስተኛው ወለሉ ላይ ለጥ ብሏል ። አይንቀሳቀስም ። በድን ሆኖ የተኛው ኮሎኔሉ ነበር ..... የማሪዩ አባት ።

ጉርሻ ፖሜርሲ ከሦስት ቀናት በፊት የአንጎል ትኩሳት ያዘው ። በሽታው ከመጀመሪያው ሰላሳፈራው ልጁ መጥቶ እንዲጠይቀው ለገርል ኖርማ ደብዳቤ ጻፈለት ። በዚያው መሐል በሽታው እየተባባሰበት ሐደ ። ማሪዩ ከቬርኖ በደረሰበት ቀን ኮሎኔሉ ሲቃብር ዋለ ። ገረዱ ፤ ስማሪዩ በር የከፈተችለት ሴትዮ ፣ ዝም ብሎ እንዲተኛ ሙከራ ብታደርግም እሱ ከመኝታው ተነስቶ ፤ « ልጄ አይመጣም ..... እሱ ሐኒ አየዋለሁ ! » ብሎ ይጮህ ጀመር ። ይህንን ብሎም ከመኝታ ቤቱ ወጥቶ ቀጥሎ ወደ ነበረው አንስተኛ ክፍል ሲገባ በአፍጢሙ ተደፋ ። ተመልሶ አልተነሳም ። ህይወቱ በዚያች ቅጽበት አለፌች ።

ከዚያ በኋላ ነው ሐኪሙና ቄሱ ተጠርተው የመጡት ። ሐኪሙ በጊዜ አልመጣም ። ማሪዩም ዘግይቶ ነው የደረሰው ።

በኮሎኔሉ ሳይን ያልደረቀ እንባ ነበረበት ፤ ልጁ በጊዜ ሳይደርስለት በመቅረቱ ያነባው የጸጸት እንባ ።

ማሪዩ የአባቱን አስከሬን ፤ በማምባሩ ላይ ያለውን የጀግንነት ምልክት ሙምር አተኩሮ ተመለከተው ። ኮሎኔሉ አባቱ እንደነበረና የደረሰውም በአስከሬኑ መሆኑን ሲገነዘብ እጅግ በጣም ቀፈፈው ።

ክፍሉ ይከብዳል ። ሠራተኛዋ ጥጉን ይዛ ታነባለች ። ቄሱ ይጸልያል ። ሐኪሙም እንባውን ይጠራርጋል ። አስከሬኑ ራሱ የሚያስቅስ ይመስላል ።

ሐኪሙ ቄሱና ሠራተኛዋ አንድም ቃል ሳይተነፍሱ ማሪዩን ተመለከቱ ት ። ለቤቱ እንግዳ እሱ ብቻ ነበር ። ማሪዩም በራሱ ሁኔታ አፈረበት ። ባርኔ ጣውን በእጁ ይዞ ቆሞ ነበር ። በሀዘን ምክንያት ባርኔጣውን በእጁ ይዞ ለማቆየት ያልቻለ ለማስመሰል ለቀቅ ሲያደርገው ባርኔጣው ወለሉ ላይ

@OLDBOOKSPDF